# መራሔ ድኅነት

ከብርሃኑ ጎበና

አዲስ አበባ ፲፱፻፺ ዓ.ም

© ብርሃኑ ጎበና ፲፱፻፺
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

**መታሰቢያነቱ**

ለቤተ ክርስቲያን ብርሃን የሆኑ አያሌ መምህራንን በትምህርታቸው ለወለዱና ቀናዒነት የተሞላ ሃይማኖት በፍቅርም ትጋት እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ሲያስተምሩ ለነበሩ፡- በኋላም የአቡነ ሰሌዳ ላይ የተማሩትን ሃይማኖት ምሥጢር ለቀረጹ ለብፁዕ አቡነ እንድርያስ ሊቀ ጳጳስ መታሰቢያ ትሁንልኝ።



ብፁዕ አቡነ እንድርያስ የጎንደር ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩ

# ማውጫ


መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፰
ማስገንዘቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲
ያለ ሥራ እንደው በጸጋው መዳን ይቻላልን?

**ምዕራፍ አንድ**

ለመዳን ምን ያስፈልጋል? . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፱

- ምሥጢረ ሥላሴ . . . . . . . . . . . . . . . . . ፳
- ምሥጢረ ሥጋዌ . . . . . . . . . . . . . . . . . ፳፫
  - የአብ የባሕርይ ልጁ መሆኑን ማመን . . . . . . . ፳፫
  - የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር መሆኑን ማመን . ፳፬
  - የተዋሃደው የድንግል ማርያምን ሥጋና ነፍስ መሆኑን ማመን . . . . . . . . . . . . . . . . . ፳፯
  - ትንሣኤውን ያለ ጥርጥር ማመን . . . . . . . . ፳፯
  - ያረገው በሥጋው መሆኑን ማመን . . . . . . . ፳፰
  - ሲመጣ በሥጋ ማርያም መሆኑን ማመን . . . . . ፳፱

**ምዕራፍ ሁለት**

ምሥጢረ – ጥምቀት . . . . . . . . . . . . . . . . . ፴፩

- የጥምቀት አስፈላጊነት . . . . . . . . . . . . . ፴፩
- የጥምቀት ምሳሌ በብሉይ ኪዳን . . . . . . . . . ፴፪
- አጥማቂው ማን ነው? . . . . . . . . . . . . . ፴፰
- የጥምቀት አፈጻጸም . . . . . . . . . . . . . . ፴፱
- የሕፃናት ጥምቀት . . . . . . . . . . . . . . ፵፪
- በማን ስም ልንጠመቅ ይገባናል? . . . . . . . . ፵፭
- ጥምቀት አንዲት ናት . . . . . . . . . . . . . ፵፯
- ለምን በውኃ እንጠመቃለን? . . . . . . . . . . ፵፯
- የጌታ ጥምቀት . . . . . . . . . . . . . . . . ፵፱
- ጌታ ለምን በዮርዳኖስ ተጠመቀ? . . . . . . . . ፶
- በጥምቀት ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎች የተሰጠ መልስ . . . . ፶፩

ምሥጢረ ቁርባን . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፶፰

- የቁርባን ትርጉም . . . . . . . . . . . . . . . ፶፰
- በብሉይ ኪዳን የምሥጢረ ቁርባን ምሳሌ . . . . . . ፶፱
- ምሥጢረ ቁርባን መቼ ተጀመረ? . . . . . . . . . ፷፪
- የኅብስቱና የወይኑ መለወጥ . . . . . . . . . . ፷፫
- በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ . . . . . . . ፷፯
- የሚታይ አገልግሎት ለመሥዋዕት የሚሆነው ኅብስት አዘገጃጀት . . . . . . . . . . . . . . . ፷፯
- ለመሥዋዕት የሚገባ ወይን . . . . . . . . . . . ፷፯
- ከቁርባን በፊት ሊደረግ የሚገባ . . . . . . . . . ፷፰
- ለመቁረብ የሚያበቁና የማያበቁ ሁኔታዎች . . . . . ፷፱
- የአቀራረብ ሥርዓት . . . . . . . . . . . . . . ፸
- ከቁርባን በኋላ የሚደረግ ጥንቃቄ . . . . . . . . ፸
- የሚቆርቡ እነማን ናቸው? . . . . . . . . . . . ፸፩

ምሥጢረ ሜሮን . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፸፪

- ሜሮን ምንድር ነው? . . . . . . . . . . . . . ፸፪
- አመሠራረቱ . . . . . . . . . . . . . . . . . ፸፪
  - በዘመነ ብሉይ . . . . . . . . . . . . . . ፸፪
  - በዘመነ ሐዲስ . . . . . . . . . . . . . . ፸፬
- የሜሮን ጥቅም . . . . . . . . . . . . . . . . ፸፯
- የሜሮን አቀባብ . . . . . . . . . . . . . . . ፸፯
- የሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ . . . . . . . ፸፰

ምሥጢረ ቀንዲል . . . . . . . . . . . . . . . . . ፸፱

- የቀንዲልና የሜሮን ልዩነት . . . . . . . . . . ፹
- የቀንዲል አፈጻጸም . . . . . . . . . . . . . ፹

ምሥጢረ ንስሐ . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፹፩
ምሥጢረ ተክሊል . . . . . . . . . . . . . . . . . ፹፪

- ጋብቻ መቼ ተጀመረ? . . . . . . . . . . . . . ፹፭
- ጋብቻ ቅዱስ ነው . . . . . . . . . . . . . . ፹፭

- የጋብቻ ዓላማ . . . . . . . . . . . . . . . . ፹፯
- ቅድመ ጋብቻ ሊጤኑ የሚገባቸው ነገሮች . . . . . . ፹፯
- ሥርዓተ ተክሊል . . . . . . . . . . . . . . ፹፯
- ድኅረ ጋብቻ . . . . . . . . . . . . . . . ፹፰
- መፋታት ይቻላልን? . . . . . . . . . . . . . ፹፰
- ድጋሚ ጋብቻ ይፈቀዳልን? . . . . . . . . . . ፹፱

ምሥጢረ ክህነት . . . . . . . . . . . . . . . . ፺
- የክህነት ትርጉም . . . . . . . . . . . . . ፺
- በዘመን ብሉይ . . . . . . . . . . . . . . . ፺፩
- በዘመን ሐዲስ . . . . . . . . . . . . . . . ፺፫
- የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ . . . . . . . . . . . ፺፭
- ሢመተ ክህነት . . . . . . . . . . . . . . . ፺፯
- አገልግሎታቸው . . . . . . . . . . . . . . ፻
- ኃጢአትን ለካህን መናገር እንደሚገባ . . . . . . . ፻፪
- በካህን እጅ መባረክ ይገባል? . . . . . . . . . . ፻፫
- ማእድን በካህን እጅ ማስባረክ . . . . . . . . . ፻፬
- ሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን መቼ ተቀበሉ? . . . . . ፻፭
- ግዴታቸውን የማይፈጽሙ ካህናት . . . . . . . . ፻፭
- ከክህነት የሚሽሩ ምክንያቶች . . . . . . . . . . ፻፯

ምዕራፍ ሦስት

መንፈሳዊ ተጋድሎ . . . . . . . . . . . . . . . ፻፯
- ጾም . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፻፰
- ጾም በአዋጅ ወይስ በስውር? . . . . . . . . . . ፻፲
    - የአዋጅ ጾም . . . . . . . . . . . . . ፻፲
    - የግል ጾም . . . . . . . . . . . . . . ፻፲፩
- የተወሰነ የጾም ወቅት ሊኖር ይገባልን? . . . . . . ፻፲፩
- ከምን ልንጾም ይገባል? . . . . . . . . . . . . ፻፲፫
- ጸሎት . . . . . . . . . . . . . . . . . ፻፲፬
- ምን ብለን እንጸልይ . . . . . . . . . . . . . ፻፲፬
- ሰባቱ የጸሎት ጊዜያት . . . . . . . . . . . . ፻፲፭
- በቅዱሳን ስም መጸለይ ይገባልን? . . . . . . . . ፻፲፯
- የመንፈሳዊ ተጋድሎ ጥቅም . . . . . . . . . . . ፻፲፰
- ዝግጅት ከሰው ድል ከእግዚአብሔር . . . . . . . . ፻፳፩
- መንፈሳዊ ተጋድሎ በየትኛው አኗኗር? . . . . . . . ፻፳፪

ምዕራፍ አራት

የምግባር አስፈላጊነት . . . . . . . . . . . . . . ፻፳፭
- በክፉ አድራጊዎች ላይ ይፈረድባቸዋል . . . . . . . ፻፳፭
- መልካሙም ሆነ ክፉ ሥራችን ይከተለናል . . . . . . ፻፳፰
- የሃይማኖት መግለጫ ምግባር ነው . . . . . . . . ፻፳፱
- ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ መልካም ሥራን ያደርጋል . . . . . . . . . . . . . . . . ፻፳፱
- ሃይማኖት በምግባር ፍጹም ይሆናል . . . . . . . . ፻፴
- በጎ ሥራ የሚሠሩ በብርሃን ይመለለሳሉ . . . . . . . ፻፴፩
- ማጠቃለያ . . . . . . . . . . . . . . . . ፻፴፪

ምዕራፍ አምስት
- መጽደቃችንን በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን? . . ፻፴፪

# መግቢያ

ከተመሠረተችበት ዕለት አንስቶ በውጊያ ላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ ድል ታደርጋለች እንጂ ተሸንፋ አታውቅም። ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ ቤተ ክርስቲያን በገለጸበት ድርሳኑ «ሰውን ብትታገልና ብትዋጋ ታሸንፈዋለህ ወይም ያሸንፍሃል። ቤተክርስቲያንን ግን ለማሸነፍ አይቻልም ቤተክርስቲያን ሁል ጊዜ ትዋጋለች ተሸንፋ ግን አታውቅም። ዲያብሎስ ዝናሩን አራገፈ፣ ቀስቱን ጨረሰ ቤተ ክርስቲያንን ግን አልጎዳትም።» ብሏል።

ርቱዕነ አንደበት የሆኑ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መናፍቃንን በቃልም ሆነ በጽሑፍ ሲዋጉ ኖረዋል። የአበውን አሠረ ፍኖት የተከተለ ይህ ትውልድም የአባቶቹን አደራ ተቀብሎ በግብር ሊመስላቸው ይገባል።

ውጊያው መልኩን ቀይሯል እንጂ አልቆመም። አጽራረ ቤተ ክርስቲያንም መልካቸውን እየቀያየሩ በክርስቶስ ዐፀደ ወይን በቤተ ክርስቲያን ላይ የኑፋቄ እንክርዳዳቸውን እየዘሩ ነው።

የግብር አባታቸው ዲያብሎስም የትእቢት ዝናሩን አስታጥቆ መምህረ ትህትና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አብነት ባደረጉ ትሁታን ላይ አዝምቱአቸዋል። የዲያብሎስ ደቀ መዛሙርት ራሳቸውን የእውነት ደቀ መዛሙርት አስመስለው ምእመኑን ወደ ጥፋት ገደል እየወረወሩት ነው።

«የክርስቶስ የሆኑ ሥጋን ከክፉ መሻቱ ጋር ሰቀሉ» በማለት የቤተ ክርስቲያን የአጥቢያ ኮከብ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረው እውነተኛ ክርስቲያኖች የሥጋን ፈቃድ የማይከተሉ፣ ሥጋቸውን በተለያዩ መንፈሳዊ ተጋድሎዎች እየጎሰሙ ለነፍሳቸው የሚያስገዙ ናቸው።

በወንጌል ስም የሚነግዱ አስመሳይ መምህራን ግን «በጸጋው ድነሃልና ሕግ መጠበቅ ተጋድሎ ማድረግ አያስፈልግም» እያሉ ትእዛዘ እግዚአብሔር እንዲጣስ መንፈሳዊ ተጋድሎ እንዲናቅ ሽንጣቸውን ገትረው ያስተምራሉ።



እነዚህ የጥፋት መልእክተኞች የትውልዱን ሥነ ልቡና ወይም የሥጋ ፈቃድ እየተከተሉ ከገድል ከትሩፋት ራሱን እንዲያገል፣ ደካማነቱን አውቆ ወደ ፈጣሪው እንዳይቀርብ በንስሐ ሕይወትም እንዳይኖር በምጽድቅ ገመድ እጅና እግሩን ገርኝተው አስረው የዲያብሎስ መፈንጫ እያደረጉት ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ላካትት የሞከርኩት አንድ ሰው «የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ማድረግ እንደሚገባው» ሲሆን ለዚህም መንስኤ የሆኑኝ «በጸጋው ድነናል» የሚሉ የአፍ አርበኞች የዲያብሎስ ምርኮኞች ናቸው። የነዚህ መናፍቃን የስህተት ትምህርት እንደ ሰደድ እሳት እየተያያዘ በብዙ ምእመናን ልቡና ከመዛመቱ በፊት ባጭሩ ሊቀጭ እንደሚገባ በማመንና እንዲሁም ክርስቲያኑ ወገኔ የእነዚህን መናፍቃን ትምህርት ይመክትበት ዘንድ ይህን መጽሐፍ ላዘጋጅ በቅቻለሁ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሰፊ ትንታኔ የሚያስፈልጋቸው ምሥጢረ ሥላሴና ምሥጢረ ሥጋዌ በአጭሩ ቀርበዋል። ይህ የሆነበት ምክንያት የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ከላይ የተጠቀሱትን ምሥጢራት «ፍኖተ ጽድቅ» በሚለው መጽሐፌ በስፋትና በዝርዝር ያቀረብኳቸው በመሆኑ ነው። ስለዚህ በስፋትና በጥልቀት ለመረዳት የሚፈልግ ሰው ይህን መጽሐፍና በዚህ ርእስ የተጻፉትን ሌሎች መጻሕፍትን መመልከት ይችላል።

የአባቶቻችን የተባረከች በረከታቸው፣ ድል የምታደርግ ረድኤታቸው፣ ጥርጥር የሌለባት ሃይማኖታቸው ከእኛ ጋር ትሁን! አሜን!

## ማስገንዘቢያ

# ያለ ሥራ እንደው በጸጋው መዳን ይቻላልን?

የዘመኑ ፍጻሜ የደረሰበት ይህ ትውልድ ሕይወት የሚገኝበት መጽሐፍ ቅዱስን በራሱ አንድምታ እንደ ገዛ ፈቃዱ፣ እንደ ሥጋ አምሮቱ እየተረጎመ በጥፋት ጎዳና እየነጎደ ነው። አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ መዘው ጉንጭ አልፋ ክርክር የሚይዙ፣ ሳያውቁ አውቀናል–ሳይበቁም በቅተናል የሚሉ መሳሐትያን መከሰት ከጀመሩ ዘመናት አልፈዋል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ እነዚህ ቢጽ ሐሳውያን (መናፍቃን) ሲያስተምር «በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ፣ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያ ጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ። እንግዲህ እናንተ፣ ወዳጆች ሆይ፣ ይህን አስቀድማችሁ ስለምታውቁ፣ በዓመፀ ኞቹ ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ» ብሏል። ፪ጴጥ.፫፥፲፮–፲፰።

እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በራስ ስሜት ተመርቶ መተርጎም እንደማይቻል ሲያስገነዝብ «ይህን በመጀመሪያ እወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ትን ቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና። ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።» ፪ጴጥ.፩፥፳።

በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ቃል እግዚአብሔር ለጸሐፍቱ ምስጢሩን ገልጦ ያጻፋቸው በመሆኑ የቃሉን ትርጉም ለመረዳት የመንፈስ ቅዱስ እገዛ ያሻል። አለበለዚያ በራስ ስሜት ተመርቶ ቃሉን እተረጉማለሁ ማለት ወደ ጥፋት ገደል ራስን መወርወር ነው።

ንዋየ ኅሩይ (ምርጥ ዕቃዩ) የተባለ ቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ቅዱስን በጥሬ ንባብ ብቻ መረዳት እንደማይቻል ሲያስረዳ «ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል» ብሏል። ፪ቆሮ.፫፥፮። በዚህ



ትምህርቱም በመንፈስ ቅዱስ ተርጓሚነት የተገለጸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምሥጢር ማወቅ የዘላለም ሕይወትን እንደሚያስገኝ አስረድቷል።

ዳሩ ግን ከብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ መካከል አንዱን ለይቶ በማውጣት ብቸኛው የመዳን መንገድ በዚህ ጥቅስ ላይ የተጻፈውን መፈጸም ብቻ ነው ብሎ ጥቅሱንም በተሳሳተ መንገድ አዛብቶ ተርጉሞ የሚያስተምር ሰው እርሱም ጠፍቶ ሌሎችንም ያጠፋል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው እውነትን ወደማወቅም አይደርስም። እንደ ጋሪ ፈረስ በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚያይ ነውና።

የእግዚአብሔር ቃል አንዱ ከአንዱ የሚጋጭ ሳይሆን ሁሉም አንድ ሀሳብን አንድ መንገድን የሚጠቁሙ ናቸው። መጻሕፍት እርስ በርሳቸው የሚጋጩ መስለው የሚታዩት ትርጉማቸውን ካለማወቅ የተነሳ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፣ ትርጉምና ምሥጢር ያለው ስለሆነ ንባቡን ካነበቡ በኋላ ትርጉሙንና ምሥጢሩን መርዳት ያሻል። ንባቡ እርስ በርሱ የሚጣላ ቢመስልም ትርጉምና ምሥጢር ግን ያስታርቀዋል። የመናፍቃን ትልቁ ችግራቸውም መጽሐፍ ቅዱስን በንባብ ብቻ ለመረዳት መሞከራቸው ነው።

አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በጥሬ ንባቡ ወስዶ መመሪያ ማድረግ ምን ያህል ሰውን እንደሚጎዳ በሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል።

ሕገ እግዚአብሔርን አምዘግዝገው በመጣል በእምነት ብቻ እንድናለን የሚሉ ክፍሎች ለዚህ ለተሳሳተ አመለካከታቸው መሠረት የሚያደርጉት «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰዎችህም ትድናላችሁ» የሚለውን ጥቅስ ነው። የሐዋ.፲፮፥፴፩።

እነዚህ ክፍሎች ይህን ቃል በተሳሳተ መልኩ ስለ ተረዱት በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተገለጸውን ለመረዳት እንዳይችሉ አእምሮአቸውን ወስነውታል። እንደ ሥጋ ፈቃዳቸው የሚመላለሱ በመሆናቸው ለምግባር ቦታ አይሰጡትም። «ምግባር ለጽድቅ አይጠቅምም» ባዮች ናቸውና።

ዳሩ ግን «ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ። እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞችን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን?

ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው» ለሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት የዝሆን ጆሮ ይስጠን ብለዋል። ያዕ.፪፥፳፮።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህች ምድር በሥጋ ተገልጦ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ አንድ ሰው ወደ እርሱ ቀርቦ «መምህር ሆይ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ? አለው። እርሱም ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ አለው። እርሱም:- የትኞቹን አለው። ኢየሱስም አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፣ አባትህንና እናትህን አክብር፣ ባልንጀራህንም እንደራስህ ውደድ አለው»። ማቴ.፲፱፥፲፮–፳።

እንግዲህ ምን እንላለን? ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት ሕግጋትን ትእዛዛትን ጠብቁ እያለ እነርሱ አይደለም የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት እምነት ብቻ ነው የሚያስፈልገው ሊሉ ይችላሉ? በየትኛው ሥልጣናቸው። በየትኛው መብታቸው?

እኛስ ልዑለ ባሕርይ አምላክ የተናገረውን አክብረን በመያዝ ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በመልካም ሥራውም ይጸድቃል እንላለን። እንዲህ ስንል ግን ሰው ሕግን በመጠበቁ ብቻ ይድናል ማለታችን እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። «የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው» የሚለውን የሐዋርያውን መልእክት እናስተውላለን። ሮሜ.፫፥፳።

እንደ ቸርነቱ ብዛት በእምነት ሆነው ሕጉን የሚጠብቁ፣ ትእዛዙንም የሚያከብሩ ለመንግሥቱ ይበቃሉ። ጌታ፣ ሐዋርያትና ነቢያትም ያስተማሩን ይህንን ነው።

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ሁሉም ባንድነት ተስተካክለው የበደሉበትን ያን የኦሪት ዘመን ወደ ኋላ መለስ ብሎ በመቃኘት ሁሉችም ከአባታቸው ከአዳም የተነሳ የኃጢአት ባሪያዎች ሆነው ሲኖሩ ሳለ የሰው ፍቅር አስገድዶት፣ የተበደለውን በደል ሳይመለከት፤ የሰው ልጅ በስሕተቱ ምክንያት አጥቶት የነበረውን ክብር መልሶ ሊያጎናጽፈው ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛ ሆኖ በመልዕልተ መስቀል



ዋለ፣ ብሎ ይህን የቤዛነቱን ሥራ በአድናቆት ሲገልጽ እንዲህ አለ «ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል። በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።» ሮሜ.፫፥፳፫።

ቀደም ተብሎ እንደ ተገለጠው ሐዋርያው ‹በዘመነ ኦሪት አይሁዳዊ፣ አሕዛብ ሳይባል ሁሉም በአንድነት ተስተካክለው በድለው ስለ ነበር ከእግዚአብሔር ጸጋ በታች ነበሩ። ጌታም በቸርነቱ ብዛት እገሌ ወእገሌ ሳይል ከአዳም ጀምሮ እስከ እርሱ መሰቀል ድረስ በሲኦል ይማቅቁ የነበሩትን የሰው ልጆች ያለ ዋጋ በነፃ (በጸጋው) ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ ቤዛ ሆኖ አድኑአቸዋል።› ለማለት ነው የፈለገው። ነገር ግን «... የተናገረውን መልካም ሥራ አያስፈልግም፣ በሕግ አይጸደቅም፣ ሕግን ሻሩ፣ በተጋድሎ አይደለም። የእግዚአብሔር መንግሥት የምትወረሰው እንደው በነፃ ያለ ምንም ሥራ ያለ ምንም ተጋድሎ ነው።» በማለት ከላይ የተጠቀሰውን ጥቅስ እየጠቀሱ ስተው የሚያሳስቱ ሰዎች ምንኛ የክርስ.መንፈስ መጫወቻ እንደሆኑ ሊረዱት ይገባቸዋል።

ከጌታ የተማሩ፣ ለሁሉ ነገር ፈትአውራሪ የሆኑት ቅዱሳን ሐዋርያት «ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል» በማለት የእግዚአብሔር መንግስት በዋዛ በፈዛዛ እንደማትገኝ አስገንዝበዋል። የሐዋ.፲፬፥፳፪። የዘመናችን ሐሳውያን ደግሞ እንደው ያለ ምንም ተጋድሎ እጅህንና እግርህን አጣምረህ ተዘልለህ «ኢየሱስ ጌታ ነው» እያልክ በየመንደሩ በየመንገዱ ከጮህክ ትድናለህ እያሉ ሰውን በቁሙ አጃጅለውት በየመጠጥ ቤቱ ሳይቀር ፎካሪ አቅራሪ አድርገውታል።

በእርግጥ በማቅራራት ብዛት የሚዳን ቢሆን ኖሮ እኛም በመሰልናቸው ነበር። ዳሩ ግን የእግዚአብሔር መንግሥት ሐዋርያት እንዳስተማሩት መች በዋዛ የምትገኝ ሆነችና። «ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመፀኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው?» ተባለ እንጂ መቼ በነፃ ይገባባታል ተባለ? ፩ጴጥ.፬፥፲፰።

‹ከመጠምጠም መማር ይቅደም› እንደ ተባለው አስቀድመው ቢማሩ ኖሮ የጥቅስ ጭራ ይዘው በመሮጥ የዋሁን ምእመን እናሳውቅህ በማለት ወደ ባሰ የጥፋት ማጥ ባልጨመሩት ነበር። ከላይ እንደተገለጠው

መጽሐፍ ቅዱስን ከመደርደሪያ አንስቶ ተጠየቅ የሚሉት ሳይሆን ከመምህራን በመጠየቅ ቀደምት ቅዱሳን አበው በመንፈስ እግዚአብሔር ተመርተው የጻፉአቸውን መጻሕፍት በማመሳከር የሚረዱት ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን ራስን በየዋህነት ለአምላክ በማስገዛት ጭምር ነው።

በተጨማሪም የአንድን ጥቅስ ሐሳብ ለመረዳት ከፍ ብሎ የጥቅሱን መነሻ ዝቅ ብሎ የጥቅሱን መቋጫ ማገናዘብ ያስፈልጋል። ይህንንም በሚከተለው ጥቅስ ማስገንዘብ ይቻላል።

«ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው? እርሱ ቀርቷአል። በየትኛው ሕግ ነው? በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም፤ በእምነት ሕግ ነው እንጂ። ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና»። ሮሜ.፫፥፳፯።

ይህን ብቻ ይዘን ሕግ አያስፈልግም በእምነት ብቻ እንጸድቃለን እንበልን? በፍጹም። ሐዋርያው በመልእክቱ ምን ለማለት እንደፈለገ የጥቅሱን መደምደሚያ እንመልከት። «እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለን? አይደለም፤ ሕግን እናጸናለን እንጂ»። ሮሜ.፫፥፴፩። ስለዚህ ሐዋርያው ሕግን ሽሮ እንዳላስተማረ በጥቅሱ መደምደሚያ ላይ አስገንዝቧል።

ለዚህም ነው አንድን ጥቅስ ከሌላ ጥቅስ ጋር ማቀራኘትና ሐሳቡን መረዳት አስፈላጊ ነው የተባለው። ይህ እንዲህ ከሆነ ቅዱስ ጳውሎስ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት ምንድር ነው?

በሕገ ኦሪት በግዝረት ይመኩ የነበሩ አይሁድ የሚድኑት በመገዘራቸውና በኦሪት ሕግ ሳይሆን ፍጹም በሆነችው በሕገ ወንጌል እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ መሆኑን በማመን ሲሆን አሕዛብም በሕገ ኦሪት ባለመኖራቸው ቈላፋን (ያልተገረዙ) መሆናቸው ከእግዚአብሔር መንግስት ውጭ እንደማያደርጋቸው ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን፣ በሕገ ወንጌል በመመላለስ እንደሚድኑ ሊገልጽላቸው ስለፈለገ «ሰው ያለ ሕግ ሥራ (ያለ ኦሪት ሕግ) በእምነት (በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት በማመን) እንዲጸድቁ (እንዲድኑ) እንቆጥራለንና» ብሎ አስተማረ።

በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑትም በሕገ ወንጌል (በወንጌል ሕግ) መመራት ይገባቸዋል። ሐዋርያው



እንዳስገነዘበን «በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉም» ሮሜ.፪፥፲፫።

የአሕዛቡ መምህር ቅዱስ ጳውሎስ አሕዛብ በሕገ ኦሪት ባለመኖራቸውና ባለመገረዛቸው የተነሳ ከጌታ ማዳን ውጭ እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን እንዳይቆጥሩ የጌታ ማዳን ሕገ ኦሪትን በመጠበቅ ወይም በመገረዝ የተደረገ ሳይሆን በቸርነቱ በጸጋው ብዛት የተደረገ መሆኑን ለማስገንዘብ ደግሞ ደጋግሞ የጌታን የቸርነቱንና የጸጋውን ብዛት ያወሳላቸው ነበር።

ከጥንት ጀምሮ የእግዚአብሔር ማዳን ለሰዎች ይደረግላቸው የነበረው ስለ ሥራቸው ብቻ አልነበረም። ስለ ቸርነቱም እንጂ። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ በምሳሌ ሲገልጥ «አብርሃም በሥራው ከብሮስ ቢሆን በተመሰገነ ነበር። ከእግዚአብሔር የተደረገለት ነው ባልተባለም ነበር። መጽሐፍ አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት እንደምን ይላል።

ያገለገለስ ዋጋው እንደሚገባው እንጂ በለጋስነት እንደሰጡት ሆኖ አይቆጠርበትም። ያላገለገለ ግን ኃጢአተኛውን በሚያጸድቅ ካመነ ማመኑ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል።» ሮሜ.፬፥፬–፭።

በዚህ አገላለጹ እግዚአብሔርን ማገልገል አያስፈልግም ምግባርም አያሻኝም ብሎ ያመፀን አመፀኛ እግዚአብሔር ግን ይምረኛል ብሎ በማመኑ በአንደበቱም በመመስከሩ ይጸድቃል ማለት ነው? እንዲህማ እንዳንል በሌላ ቦታ «እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣል» በማለት ሥራቸው መጥፎ የሆኑ ሰዎች ፍጻሜ ምን እንደሆነ አስረድቷል። ሮሜ.፩፥፲፰

የኦሪትን ሕግ (ግዝረትን) ሳይፈጽሙ አሕዛብ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች ሊሆኑ እንደሚችሉ ያስተላለፈው መልእክት እንደሆነ ቀጥሎ ባለው መልእክት እንገነዘባለን። «እንግዲህ ምን ሠርተው ራሳቸውን ያስመሰግናሉ የተገዘረ ብቻ ራሱን ብዑዕ (ጻድቅ) ያሰኛልን ያልተገዘረሳ ራሱን ጻድቅ የሚያሰኝበት መንገድ የለውምን መጽሐፍ አብርሃም ከበረ ራሱንም አስመሰገነ ይል የለምን። አብርሃም

ምን ጊዜ ከበረ ተገዝሮ ነውን ወይስ ሳይገዘር፤ ተገዝሮ አይደለም ሳይገዘር ነው እንጂ።...ያን ጊዜ ሳይገዘር እግዚአብሔር አብርሃምን በሃይማኖት እንደ አከበረው በርሱ ላይ ይታወቅ ዘንድ ሳይገዘሩ ለሚያምኑ ሁሉ አባት ሊሆን አብርሃም በሃይማኖት እንደ ከበረ እነሱም በሃይማኖት እንደሚከብሩ ያውቁ ዘንድ» ሮሜ.፬፥፱–፲፩።

እንግዲህ የመልእክቱ ጭብጥ በኦሪቱ ሕግ መሠረት ላልተገረዙት አሕዛብ በማመናቸው የእግዚአብሔር ጸጋ እንደሚደርሳቸው ለማስረዳት መሆኑን እንረዳለን።

በሕገ ኦሪት ለተገዘሩትም ሆነ በአሕዛብነት ለነበሩ «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም» በማለት የእግዚአብሔር የቸርነቱን ስፋት ገልጡአል። ኤፌ.፪፥፰።

በኃጢአት ጎስቁሎ የነበረውን ሰብእናችን በደሙ አጥቦ አንጽቶ በሐዲስ ተፈጥሮ የፈጠረን በመልካም ምግባር በቅድስና ሕይወት እንድንመላለስ መሆኑን ሲያስገነዝበንም «እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» አለ። ኤፌ.፪፥፲።

ባለመታዘዝ የተነሳ አጥተነው የነበረውን የልጅነት ጸጋ ጌታችን ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ በእኛ በደል እርሱ መከራን ተቀብሎ ያስመለሰልን አመፀኞች እንድንሆን ነውን? ለእግዚአብሔር ቃል የማይታዘዙ ሁሉ አመፀኞች ናቸውና።

ነፍስን እንደሚጎስሙ ቅዱሳን በከንቱ እንደ ተጋደሉ አድርገህ የምታወራ የቃል አርበኛ «በጌታ በማመኔ እንዲያው በጸጋው እድናለሁ» በሚል ከንቱ ትዕቢት ታጅለህ መኖርህን አቁመህ ሕይወት ለሚገኝበት መንፈሳዊ ተጋድሎ ቅና። «መልካም እነርሱ ከአለማመን የተነሣ ተሰበሩ አንተም ከእምነት የተነሣ ቆመሃል። ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ። እግዚአብሔር እንደ ተፈጥሩት ለነበሩት



ቅርንጫፎች የራራላቸው ካልሆነ ለአንተ ደግሞ አይራራልህምና። እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነቱንና ጭከናውን ተመልከት። ጭከናው በወደቁት ላይ ነው። በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው። ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ» ሮሜ.፲፩፥፳–፳፪።

ባለቤቱም እንዲህ ይልሃል «በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር። እንዲሁ ለብ ስላልህ ከአፌ ልተፋህ ነው» ራእይ.፫፥፲፭–፲፮።

እናስ «ልትድን ትወዳለህን?» ዮሐ.፭፥፮።

መልስህ «አዎን» ከሆነ አእምሮህን ከትዕቢት ነፃ አድርገህ፤ ዕዝነ ልቡናህን ለዓለም ጫጫታ ዘግተህ፤ በአንቃእድዎ ኅሊና በሰቂለ ልቡና ሆነህ ይህን ጥያቄ ጠይቅ።

## እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?

የመቄዶንያ መዲና በምትሆን በፊልጵስዮስ የምዋርተኝነት መንፈስ ያደረባት አንዲት ብላቴና ቅዱስ ጳውሎስንና ሲላስን «እሊህ ሰዎች የልዑል እግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው። ድኅነት የምታገኙበትን ነገር ያስተምሯችኋል» እያለች ብዙ ቀን ከቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ ኋላ እየተከተለች ትጮህ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስም ወደ ኋላ ተመልሶ ያደረባትን ጸላኤ ሠናይ «ከሷ ትወጣ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዝሃለሁ» አለው። ያን ጊዜ ርኩስ መንፈስ ተለይቷት ሄደ።

ይህቺ ብላቴና ለጌቶችዋ በጥንቆላ ከምታገኘው ሁሉ ግብር ታገባላቸው ነበርና ከሰይጣን እሥራት ተፈታ ባዩአት ጊዜ ከእንግዲህ የምታገባላቸው ግብር እንደ ተቋረጠ አውቀው በቅዱስ ጳውሎስና በሲላስ ላይ ሕዝቡን አስተባበሩ። አስደበደቡአቸውም። በኋላም ወደ ወኅኒ ጣሉአቸው። የወኅኒ ጠባቂውም እንዳያመልጡ እግራቸውን ከግንድ ጋር አሠረው።

መንፈቀ ለሊት ላይ ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ በተመስጦ ሲዘምሩ በጸሎትም እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ሳለ ድንገት የወኅኒውን መሠረት

ያናወጠ ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ሆነ። የወኅኒው ደጆችም ተከፈቱ። የሁሉም እሥራት ተፈታ። የወኅኒው ጠባቂ በሮቹ ተከፍተው ባየ ጊዜ እስረኞቹ ሁሉ ያመለጡ መስሎት ራሱን ሊያጠፋ ሰይፉን መዘዘ። ቅዱስ ጳውሎስ ግን በታላቅ ድምፅ «ሁላችን ከዚህ አለንና በራስህ ክፉ ነገር አታድርግ» በማለት አጽናናው።

የወኅኒ ጠባቂው መብራት ለምና ወደ ውስጥ ሮጠ፣ እየተንቀጠቀጠም ከቅዱስ ጳውሎስና ከሲላስ ፊት ተደፋ። ወደ ውጭም አውጥቶ «ጌቶች ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» ሲል ጠየቃቸው?

ይህ ጥያቄ ዛሬም የብዙዎች ጥያቄ ነው። ከዘላለም ጥፋት ለመዳን የሚሹ ወገኖች ሁሉ የሚያቀርቡት ጥያቄ ነው። በእርግጥም ነፍሳቸውን ለማዳን የሚሮጡ ሰዎች ሁሉ «እንድን ዘንድ ምን ማድረግ ይኖርብናል?» ለሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት አለባቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ የዘላለም ድኅነት የሚያገኝበት መንገድ ምን እንደሆነ በግልጽ ያስተምራል። «ዛቲ መጽሐፍ መራሒተ ድኅነት ይእቲ» ይህች መጽሐፍ ለመዳን ምን ማድረግ እንደሚገባ የምትመራ ናት።



ምዕራፍ አንድ

# ለመዳን ምን ያስፈልጋል?

የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ሃይማኖትን ከምግባር ምግባርን ከሃይማኖት አስተባብሮ መያዝ ያስፈልጋል። «ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ (ምግባር)የተለየ እምነት የሞተ ነው» እንዲል። ያዕ.፪፥፳፮።

ሃይማኖት መሠረት፣ ምግባር ጣሪያ ግድግዳ ነው። ቤት ያለ መሠረት አይጸናም፣ ድኅነትም ያለ ሃይማኖት አይገኝም። ቤት ያለ ጣሪያ ግድግዳ – ለመኖሪያነት አያገለግልም፣ ሃይማኖትም ያለ ምግባር ለድኅነት አያበቃም።

## ሃይማኖት ማለት ምን ማለት ነው?

ሃይማኖት ሥርወ ቃሉ ግዕዝ ሲሆን ትርጉሙም ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ ጽኑ ተስፋ በልብ በረቂቅ ሐሳብ የሚሳል ማለት ነው።*

ሃይማኖት ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ መንገድና የሰውና የእግዚአብሔር ግንኙነት ነው። ይህም ግንኙነት በእግዚአብሔር የተጀመረው አስቀድሞ በመፍጠር እንደዚሁም የሰው ልጅ አጥፍቶ በተደበቀ ጊዜ የጥሪ ድምፅ በማሰማት ነው። በመሆኑም ሃይማኖት ፍኖተ እግዚአብሔር (ዴሬክ ያህዌ) የእግዚአብሔር መንገድ ይባላል። (ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ከተዘጋጀ የትምህርት ሽት የተወሰደ)

በጎ ምግባር ብቻውን ያለ ሃይማኖት ለድኅነት አያበቃም። ምክንያቱም «ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልምና።» ዕብ.፲፩፥፮።

ሃይማኖት አንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተሰጠ የእግዚአብሔር በረከት እንጂ ሰዎች በገዛ ስሜታቸው ተመርተው የሚደነግጉት የመተዳደሪያ ደንብ አይደለም። ይሁዳ መል. ቁጥር ፫።

* ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ ፫፻፱

ሃይማኖት አቻና አኳያ የሌላት አንዲት ናት። ኤፌ.፬፥፭። የሐሰት ምንጭ ዲያብሎስ ግን ብዙ የሐሰት መንገዶችን ፈጥሮ «ሃይማኖት» የሚል ስያሜ አጎናጽፎ ሰዎችን ያስታል። ሰውን የሚወድ ፋጎፉጎ አምላክ እግዚአብሔር ግን የአዳም ዘር በአንድ ልብ በአንድ መንፈስ ያመልከው፣ ወደ ዘላለማዊቱም ርስት መንግስተ ሰማይ ይገባ ዘንድ አንድ መንገድ ብቻ አዘጋጅቶለታል። «በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም፣ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደ ሆነች እወቁ፣ በእርስዋም ላይ ሂዱ፣ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፣ እነርሱ ግን አንሄድበትም አሉ» ተብሎ እንደ ተጻፈው ዛሬ በዓለም የሚኖሩ ሰዎች እግዚአብሔር የመሠረታትን ሃይማኖት ትተው በራሳቸው የሥጋ ፈቃድ የፈለሰፉትን መንገድ ተከትለዋል። ኤር.፮፥፲፮።

እውነተኛዋና ቀጥተኛዋ ሃይማኖት ተቀዳሚ ተከታይ የሌላት የዘላለም ሕይወት የሚገኝባት የጸጋና የጽድቅ ምንጭ ናት። መሥራችዋም ልዑለ ባሕርይ አምላክ እግዚአብሔር ነው። በነቢያት ተነግራለች፣ አዕማደ ምድር በተባሉ ሐዋርያት ተሰብካለች።

ለዘላለማዊ ድኅነት የምታበቃ ይህችው እውነተኛዋ ሃይማኖትም የሚከተለውን ትምህርት ታስተምራለች።

## ምሥጢረ ሥላሴ

የሚታዩትንና የማይታዩትን፣ ረቂቁንና ግዙፉን የፈጠረ አምላክ አንድ ሲሆን ሦስት፣ ሦስት ሲሆን አንድ ነው። ይህ የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት የእውነተኛዋና የቀጥተኛይቱ ሃይማኖት አንዱ መታወቂያ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የዘላለማዊውን አምላክ አንድነትና ሦስትነት በግልጽ አስተምሯል።

እግዚአብሔር አንድ ነው ሲባል በአካል ሳይሆን በመለኮታዊ ባሕርይው ነው። እነዚህም መፍጠር፣ መግዛት፣ መፍረድ፣ ሕልውና የመሳሰሉትን የሚጠቀልል ነው። ለዚሁም «እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው» ተብሎ ተጽፏል። ዘዳ.፮፥፬።



እንዲሁም «እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ዘፍ.፩፥፩ «አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትኸ ሰማያትም የእጅህ ሥራዎች ናቸው» መዝ.፻፪፥፳፭። ተብሎ ተገልጾአል።

ስለ ልዩ ሦስትነቱም መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስገነዝብ:-

- «እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንፍጠር» ዘፍ.፩፥፳፮።
- «እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» ዘፍ.፫፥፳፪። ከእኛ የሚለው ሦስትነትን የሚያመለክት ነው።
- «እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት፣ ዓይኑንም አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ» ዘፍ.፲፰፥፩–፪።
- «አንዱም ለአንዱ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ለክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር»

  አንዱ አብ ቅዱስ ነው፤ አንዱ ወልድ ቅዱስ ነው፤ አንዱ መንፈስ ቅዱስም ቅዱስ ነው።

- «ያዕቆብ ሆይ የጠራሁህም እስራኤል ሆይ ስማኝ እኔ ነኝ፣ እኔ ፊተኛው ነኝ፣ እኔም ኋለኛው ነኝ። (አልፋና ኦሜጋ ማን ነው? እግዚአብሔር አይደለምን) እጄም ምድርን መሥርታለች ቀኜም ሰማያትን ዘርግታለች በጠራኋቸው ጊዜ በአንድነት ይቆማሉ …ወደ እኔ ቅረቡ ይህንም ስሙ እኔ ከጥንት ጀምሬ በስውር አልተናገርሁም፣ ከሆነበት ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነበርሁ (ይህን የሚለው ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ ነው) አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል» ኢሳ.፵፰፥፲፪–፲፮።

  ተላኪ እግዚአብሔር ወልድ ልከውኛል ያላቸው እግዚአብሔር አብና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ናቸው።

- «…ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ» ማቴ.፫፥፲፮–፲፯።

  ተጠማቂ ወልድ፣ በርግብ አምሳል የወረደ መንፈስ ቅዱስ፣ ከሰማይ ሆኖ የምወደው ልጄ ያለ አብ።

- «በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ» ማቴ.፳፰፥፲፱።
- «መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፣ የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል፣ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ነው።»
- «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው» ዮሐ.፲፬፥፲፭–፲፯።

እኔም:- ያለው ጌታችን፣ አብን ብሎ የባሕርይ አባቱን አጽናኝ ብሎ መንፈስ ቅዱስን ገልጾልናል። ሦስትነታቸው በዚህ ግልጽ ሆኑዋል።

- «ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል» ዮሐ.፲፭፥፳፮።

መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሠረጸ እንጂ ከወልድ አለመሆኑን ራሱ ባለቤቱ አስገንዝቦናል።

- «በሰማይ የሚመሰክሩ ሦስት ናቸው። እነርሱም አብ፣ ልጅም (ወልድ) መንፈስ ቅዱስም ናቸው። እነዚህ ሦስቱም አንድ ናቸው» ፩ዮሐ.፭፥፯።**

ቀጥተኛዋና እውነተኛዋ ሃይማኖት እግዚአብሔር አንድ ሲሆን ሦስት ሦስት ሲሆን አንድ ብላ ታምናለች።

አንድነቱ:- በመለኮት፣ በሕልውና፣ በፈቃድ፣ በመፍረድ...

ሦስትነቱ:- በስም – (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ)

በግብር – አብ ወላዲ (አባት)፣ ወልድ ተወላዲ (ልጅ) መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ (ከአብ የወጣ)

በአካል:- ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክ ፍጹም አካል አላቸው ብሎ ማመን ነው።

---

* በ፲፱፻፺፪ ዓ.ም የታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ

* King James Version



## ምሥጢረ ሥጋዌ

በፈታሒነት አንጻር መሐሪነት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ ርኅሩኅ አምላካችን በጥፋቱ ከገነት ተባሮ በመንጸፈ ደይን ወድቆ ይማቅቅ የነበረውን የሰውን ልጅ ወደ ቀደመ ቦታው ይመልሰው፣ የተገፈፈውንም ጸጋ መልሶ ያለብሰው ዘንድ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ስለ ሰው ልጅ ቤዛ የሆነበት ይህ የማዳን ሥራ ምሥጢረ ሥጋዌ በመባል ይታወቃል።

ሰዎች ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ያገኙ ዘንድ በሥጋ የተገለጠውን የእግዚአብሔርነት ምሥጢር ያለ አንዳች ጥርጥር አምነው መቀበል ይኖርባቸዋል።

«በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፣ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል» ዮሐ.፫፥፲፰።

### በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን እንዴት ነው?

### ሀ. የአብ የባሕርይ ልጁ መሆኑን ማመን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ ማርያም ብቻ ሳይሆን ወልደ አብም ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ይህን በግልጥ ያስተምረናል።

- «የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መጣ፣ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን። እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፣ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ፩ዮሐ.፭፥፳።
- «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» ማቴ.፲፯፥፭። እግዚአብሔር አብ ስለ ባሕርይ ልጁ ስለ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሰከረው ምስክርነት። ይህንን ምስክርነት የሰማ ቅዱስ ጴጥሮስም «ከገናናው ክብር:- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ድምፅ እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋር ሳለን ይህን ድምፅ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን» ብሏል። ፪ጴጥ.፩፥፲፯–፲፰።
- «ልጁ ያለው ሕይወት አለው። የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም» ፩ዮሐ.፭፥፲፪።

- «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን፣ ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ»። ገላ.፬፥፬።
- ጌታ «ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል?» የሚል ጥያቄ ለደቀ መዛሙርቱ ባቀረበ ጊዜ «አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሌሎችም ኤልያስ፣ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት» ጌታም መለሰ «እናንተስ እኔን ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ?» አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ» በዚህ እምነቱም ብፁዕ ተብሏል። ማቴ.፲፮፥፲፫።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ እንደሆነ የሚያምኑ ሁሉ ብፁዐን ይባላሉ።

ሐዋርያት በዓለም ዞረው ያስተማሩት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መሲሕነትና የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅነቱን ነው። የወልደ እግዚአብሔርን ሰው መሆን የማያምኑ የተወገዙ ናቸው።

## ለ. የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር መሆኑን ማመን

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የካዱ ከድኅነት መንገድ የወጡ ናቸው። እውነተኛና የዘላለምን ሕይወት የምታሰጥ ሃይማኖት ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ነው የምትል ናት።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርነት በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠ ነው።

- «ሕፃን ተወልዶልናል፤ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» ኢሳ.፱፥፮።
- ኃያል አምላክ ከእግዚአብሔር በስተቀር ማን አለ? የዘላለም አባትስ የሚባል ፍጡር ነውን? ሕፃን ሆኖ የተወለደው የክርስቶስን እግዚአብሔርነት በዚህ እንረዳለን።
- «ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ይላል» ራእይ.፩፥፰።

ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ለፍርድ የሚመጣው ክርስቶስም ሁሉን የሚገዛ የተባለው እግዚአብሔር በመሆኑ ነው።



- «እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ» ራእይ.፳፪፥፲፪።
- «እግዚአብሔር በዕልልታ፣ በመለከት ድምፅ ዐረገ» መዝ.፵፮(፵፯)፥፭።

ሐዋርያት እያዩት ስላረገው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ዳዊት ከእርገት ሺ ዘመን ቀደም ብሎ የዘመን ግድግዳ ሳይጋርደው በትንቢት መስተዋት ተመልክቶ የተናገረው ነው።

- «ከክብሩ ውበት ከጽዮን እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል»። መዝ.፵፱፥፪።

በግልጥ የሚመጣው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ነቢዩ በግልጥ የሚመጣውን ጌታ እግዚአብሔር ብሎ እንደጠራው እናስተውል። የሐዋ.፩፥፲፩

- «እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው» ፩ዮሐ.፭፥፳።
  እርሱ ያለው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው።
- ለስም አጠራሩ ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «እኔና አብ አንድ ነን» ብሏል። ዮሐ.፲፥፴። ፊሊጶስ አብን አሳየንና ይበቃናል ባለውም ጊዜ በባሕርይ አንድ መሆናቸውን ሲያስገነዝብ «አንተ ፊልጶስ ይህን ያህል ዘመን ከአንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን?...እኔን ያየ አብን አየ» ብሎታል። ዮሐ.፲፬፥፰–፲።
- «በመጀመሪያው ቃል ነበር። ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር። ያ ቃልም እግዚአብሔር ነው። ...ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ»። ዮሐ.፩፥፩:፲፬።
- «ክርስቶስ በሥጋ መጣ፣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው» ሮሜ.፱፥፭።

ከላይ እንደ ተገለጠው መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት በግልጥ አስረድቶናል። እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ እውነተኛውን አምላክ ከአብ አሳንሰው ፍጡር፣ መልአክ፣ ነቢይ፣ አማላጅ የሚሉ ሁሉ ከድኅነት መንገድ የወጡ ናቸው።

## ሐ. የተዋሐደው የድንግል ማርያምን ሥጋና ነፍስ መሆኑን ማመን

የዘላለም ሕይወት የሚገኝባት ሃይማኖት ናት። ይህችም ጌታ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ተዋሐደ ብላ የምታምን ናት። ቤተ ክርስቲያናችንም ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም አምላክን በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ጸንታ ወልዳለች ብላ ታምናለች ታስተምራለች። ይህንንም ዕብነ ማዕዘንት በተባለው በታላቁ በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኘው ትምህርት ነው።

- ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ጌታ ከአብርሃም ዘር ከሆነች ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ሰው እንደሆነ ሲያስረዳ «የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም። ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው» ዕብ.፪፥፲፮ ና ፲፯። ብሏል።
- ወንድሞቹን ሊመስል መባሉ የእኛን ሥጋ በመዋሃዱ አይደለምን?
- «የሃይማኖታችን ምሥጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው። እርሱም እግዚአብሔር ሰው ኾኖ የተገለጠ...» ፩ጢሞ.፫፥፲፮።

ሰው ኾነ መባሉ ከድንግል በነሣው ሥጋና ነፍስ ነው። ክብር ምሥጋና ይግባውና ራሱ ባለቤቱ «የሰው ልጅ» እያለ ስለ ራሱ መናገሩ የሰውን ሥጋና ነፍስ መዋሐዱን ለመግለጽ ነው።

ሥጋን ከሰማይ ይዞ የመጣ ከድንግልም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ሳይነሳ እንዲሁ ለማደሪያነት ብቻ የመረጣት ቢሆን ኖሮማ «የሰውን ልጅ ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም እንዴት ሊል ቻለ?» ዮሐ.፮፥፶፫።

- ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ንግሥተ አርያም ድንግል እመቤታችንን ሲያበስር «ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» ስለምን አላት? ሉቃ. ፩፥፴፭።

ኤልሳቤጥም «በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝታ «አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፣ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። የጌታዬ እናት» ብላ ልታመሰግናት እንዴት ቻለች? ሉቃ.፩፥፴፪።



ይህ ሁሉ እግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ በመዋሐዱ ነው።

- ነቢየ ልዑል ኢሳይያስም «ድንግል ትፀንሳለች፣ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» ኢሳ.፯፥፲፬ ብሏል።

አማኑኤል ስመ ሥጋዌ ነው። እግዚአብሔር ከሥጋችን ሥጋ ከነፍሳችን ነፍስ ነስቶ ሰው መሆኑን የሚያመለክት ነው።

ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ የምንላትም አምላክ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ በመወለዱ ነው።

የወልደ እግዚአብሔርን ሰው መሆን የሚጠራጠሩና የክርስቶስ ሥጋው አስቀድሞ የነበረ ከድንግል ማርያም ያልተወሰደ ነው የሚሉ ሁሉ ከሕይወት መንገድ የራቁና የእግዚአብሔርን ቸርነት የናቁ ናቸው። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ክርስቶስን የካዱ ናቸው። ትምህርታቸውም ከንቱና የዓለምን ተረት የተከተለ ነው።

## መ. ትንሣኤውን ያለ ጥርጥር ማመን

በሞቱ ሞታችንን እንዳጠፋልን፣ በትንሣኤው ትንሣኤያችንን አብሥሮልናል። ትንሣኤውም በገዛ ኃይሉና ሥልጣኑ የሆነ እንጂ አስነሺ ያስፈለገው አይደለም። ሲነሳም በሥጋው ነው። ይህን የማያምን ከቀጥተኛይቱና የዘላለምን ሕይወት ከምታሰጥ ሃይማኖት የወጣ ነው።

መላእክት ይህን መስክረዋል «እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንደምትሹ አውቃለሁና። ከዚህ ግን የለም እሱ እንደተናገረው ተነሥቶአል» ማቴ.፳፰፥፮። ጌታ የተናገረው ምን ነበር? «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፣ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ» የተናገረው ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ነበር። ዮሐ.፪፥፲፱–፳፪።

«...አትደንግጡ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ትፈልጋላችሁ ተነሥቶአል በዚህ የለም እነሆ እርሱን ያኖሩበት ስፍራ» ማር.፲፮፥፮።

ደቀ መዛሙርቱም የጌታን ሥጋ በመቃብር እንዳላገኙት ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ መስክረዋል «የጌታ ኢየሱስን ሥጋ አላገኙም... ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቶአል እንጂ

በዚህ የለም» የሚለውን ምሥክርነት ከመላእክት መስማታቸውን ተናግረዋል። ሉቃ.፳፬፥፮።

ክብር ምስጋና ይገባውና ልዑለ ባሕርይ አምላክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ከትንሣኤው በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ በዝግ ቤት ገብቶ «አትፍሩ እኔ ራሴ እንደሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው ይህንንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው» ሉቃ.፳፬፥፴፮—፴፱።

በዚህም በሥጋው እንደተነሣ ራሱ አስገንዝቦናል። ይህን ሁሉ ንቆ አቃሉ የክርስቶስ ሥጋው አልተነሳም መንፈሱ እንጂ የሚል የተረገመ ነው።

## ሠ. ያረገው በሥጋው መሆኑን ማመን

ሐዋርያት እያዩት በመርቀቅ ሳይሆን በመራቅ ወደ ሰማይ የወጣው ወልደ አብ ወልደ ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህንንም አስቀድሞ ባለቤቱ በዘመነ ስብከቱ «ወደ ሰማይ የወጣ የለም፤ ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በቀር። እርሱ በሰማይ የሚኖር ነው» ብሏል። ዮሐ.፫፥፲፫።

እጁን በመጫን ሐዋርያትን ከባረካቸው በኋላ ምድርን ለቆ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ እያለ በፍጹም ምስጋና ፈጽሞ ወደ አልተለየው ወደ ባሕርይ አባቱ ዐርጓል።

በሥጋና በነፍስ፤ በአጥንትና በደም፤ በሥርና በጅማት፤ በፀጉርና በጽሕም እንዳለ በጥንት አነዋወሩ ተቀመጠ። በሰማይ በምድርም ያሉት ረቂቁም ግዙፉም ሁሉም ተገዛለት። ፊልጵ.፪፥፲።

አምላክ የሰውን አካል የሰውን ባሕርይ ገንዘብ አድርጎ ሰው ሲሆን በሰው አካል በሰው ባሕርይ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ሲገለጥ ሰውም የአምላክን ገንዘብ ገንዘብ አድርጎ በየማን አብ፤ በዘባነ ኪሩብ የመላእክትን ምስጋና ለመቀበል በቃ።

ቅዱስ እስጢፋኖስ ከእርገቱ በኋላ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና «እነሆ የሰው ልጅን



በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ» ብሎ ተናግሯል። የሐዋ.፯፥፶፮። በአብ ቀኝ ቆሞ የታየው ከድንግል ማርያም በነሣው ሥጋ ነው።

በሰማይ ያሉ እልፍ አእላፋት ወትእልፊተ አእላፋት የሚሆኑ ሠራዊተ መላእክት ከቅድስት ድንግል ማርያም በነሣው ሥጋ በዘባነ ኪሩብ፤ በየማነ አብ ለተቀመጠው «የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል» በማለት ዘወትር ምስጋና እንደሚያቀርቡለት ተጽፏል። ራእይ.፭፥፲፪።

በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ «በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፤ ለበጉም ይሁን» እያሉ ያመሰግኑታል።

ለዓለም ሁሉ መስዋእት የሆነው ከድንግል ማርያም በነሣው ሥጋ ነው። የተዋሃደውን ሥጋ በመቃብር እንዳልተወው፤ በሥጋውም እንዳረገ፤ በአብ ቀኝ ተቀመጠ ክብርና ምሥጋናም ተቀበለ መባሉም ለሥጋ መሆኑን በዚህ እንገነዘባለን። ስለዚህ ሥጋ የባሕርይ አምላክ አልሆነም የሚሉ ሁሉ የጸጋና የሕይወት መገኛ ከሆነችው እውነተኛዋ ሃይማኖት የተለዩ ናቸው።

ከትንሣኤው በኋላ ጌታን ይለምናል፤ ያማልዳል የሚሉም የጌታን የባሕርይ አምላክነት ከማመን የወጡ ናቸው። እስከ መስቀል ድረስ ያደረገውን የማስታረቅ አገልግሎት የቤዛነት ሥራ የተዋራጅነት ምልክት አድርገው እርሱን ለማኝ፤ አብን ተለማኝ የሚያደርጉ መበላለጥ በሌለባቸው በሥላሴ ላይ መበላለጥን የፈጠሩ ናቸውና ከእውነተኛዋ መንገድ የወጡ ናቸው።

የጌታ የማስታረቁ አገልግሎት በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ተፈጽሟል። ዛሬ በዕለተ ዓርብ በፈጸመው የማስታረቅ አገልግሎት ነው ሰውን ሲያድን የሚኖረው። ይህ በዕለተ ዓርብ የተፈጸመው የማስታረቅ አገልግሎት እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ለሚነሱ ክርስቲያኖች እንደሚሰራም ሐዋርያት በተለያየ መልኩ ገልጸውታል። ዕብ.፯፥፳፭።

## ረ. ሲመጣ በሥጋ— ማርያም መሆኑን ማመን

የጌታን ዕርገቱን ትኩር ብለው ያስተውሉ ለነበሩት ቤተሰቦቹ መላእክት «የገሊላ ሰዎች ሆይ፤ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን

ቶግችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል» የሚል መልእክት አስተላልፈውላቸዋል። የሐዋ.፩፥፲፩።

ከዚህም የምንገነዘበው በሥጋ ማርያም ያረገው ጌታ ለፍርድ ተመልሶ የሚመጣውም በሥጋ ማርያም መሆኑን ነው። ከተዋሕዶ በኋላ መለያየት የለምና።

ምስጋና የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም ምጽአቱን አስመልክቶ ሲናገር «የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል» በማለት ከድንግል እናታችን በነሣው ሥጋ ዳግም ለፍርድ እንደሚመጣ አስረድቷል። የሰው ልጅ መባሉ ከእመቤታችን በነሣው ሥጋና ነፍስ ነው።

አቡቀለምሲስ የሚባል ዮሐንስ የጌታን ምጽአት ሲናገር «እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል፣ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል» ብሏል። ራእይ.፩፥፯። የተወጋው ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ የተዋሐደው ሥጋ አይደለምን? የሚመጣውም እርሱ ራሱ እንጂ ሌላ አይደለም።

ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት «ከክብሩ ውበት ከጽዮን እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል» በማለት ጌታ በሥጋ ማርያም በክበበ ትስብእት እንደሚመጣ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ተናግሯል። መዝ.፵፱(፶)፥፪።



ምዕራፍ ሁለት

# ምሥጢረ ጥምቀት

መጠመቅ ማለት መነከር፣ መዘፈቅ፣ ውኃ ውስጥ ገብቶ መውጣት ማለት ነው። ምሥጢረ ጥምቀት የሥላሴ ልጅነት የሚሰጥበት እና የኃጢአት ሥርየት የሚገኝበት ምሥጢር ነው።

## የጥምቀት አስፈላጊነት

፩. ድኅነት በጥምቀት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረን ያልተጠመቀ ሰው አይድንም። የተጠመቀ ግን እንደሚድን በመዋዕለ ትምህርቱ እንዲህ ሲል አስተምሯል «ያመነ የተጠመቀም ይድናል» ማር.፲፮፥፲፮። ያመነ ይድናል ብቻ አለማለቱን ማስተዋል ያስፈልጋል። ጥምቀት ለድኅነት ባያስፈልግ ኖሮ ጌታ «ያመነ የተጠመቀም ይድናል» ባላለ ነበር።

፪. በጥምቀት ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም እንወለዳለን።

ኒቆዲሞስ የተባለው የአይሁድ አለቃ በሌሊት ወደ ጌታ ዘንድ ሊማር በሄደ ጊዜ ጌታ «እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» አለው። ይህ የጌታ ትምህርት ለኒቆዲሞስ ስለ ረቀቀበትና ስለ ተቸገረ «ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?» የሚል ጥያቄ አቅርቦ ነበር።

ዳሩ ግን ዳግም ልደት «ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ» የሚገኝ መሆኑን ጌታችን እንዲህ ሲል አስተምሮታል

«እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም» ዮሐ.፫፥፫–፯።

ከጌታችን ትምህርት የምንገነዘበው በሚታይ ሥርዓት (በውኃ በሚደረገው ጥምቀት) አማካኝነት ከሥላሴ ልጅነት ካላገኘን በስተቀር

እንኳን መንግሥተ ሰማያት ልንገባ ልናያትም እንደማንችል ነው። ስለዚህ «ከውኃና ከመንፈስ መወለድ» ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው።

ምናልባት አንዳንድ ሰዎች «ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ» አለ እንጂ «መቼ ካልተጠመቀ» አለ ብለው ለመከራከር ይከጅሉ ይሆናል። ዳሩ ግን አስተዋይ አእምሮ ያለው ሰው «ከውኃና ከመንፈስ መወለድ» ማለት መጠመቅ ማለት እንደ ሆነ አይጠፋውም። ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ዳግም የምንወለደው በጥምቀት ነው። መወለድ ከእናት ማኅፀን መውጣት እንደ ሆነ ሕፃኑም ከውኃው ጠልቆ ይወጣልና።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጥምቀት የሚገኘውን ጸጋና ክብር ለቲቶ ሲገልጽለት «ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደድ በተገለጠ ጊዜ እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም» ብሏል። ቲቶ.፫፥፭።

«ለአዲስ ልደት በሚሆን መታጠብ» ማለቱ ጥምቀትን ማለቱ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። እንዲሁም ለኤፌሶን ሰዎች ቤተክርስቲያንን አስመልክቶ በጻፈው ክታቡ «...በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ...» በማለት በጥምቀት አማካኝነት ምእመናን መንጻታቸውንና መቀደሳቸውን አስተምሯል። ኤፌ.፭፥፳፮።

፫. በጥምቀት የኃጢአት ሥርየት ይገኛል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጌታን ከማሳደድ ተመልሶ የእርሱ ምርጥ ዕቃ ሊሆን በተጠራ ጊዜ ሐናንያ እንዲህ ብሎታል። «አሁንስ ለምን ትዘገያለህ? ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ። ከኃጢአትህም ታጠብ።» የሐዋ.፳፪፥፲፮። በዚህ መሠረት መጠመቁም ተገልጾአል። የሐዋ.፱፥፲፯–፲፰።

እንግዲህ ምን እንላለ? ታላቁ ሐዋርያ ከኃጢአቱ የነጻውና የተቀደሰው በእምነቱ ብቻ ሳይሆን አምኖ ጥምቀትን በመፈጸሙ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ኃጢአቱ የተወገደለት ሐዋርያ እንዲሆን በተጠራ ጊዜ ሳይሆን «የእግዚአብሔርን ስም እየጠራ በተጠመቀ» ጊዜ ነው። እርሱም ድኅነት የሚገኘው በጥምቀት መሆኑን እንዲህ ሲል ገልጾታል። «ከእናንተ አንዳንዶች እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤



ጸድቃችኋል» ፩ቆሮ.፮፥፲፩። በበዓለ ሃምሳ በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ልቡናቸው ከተመሰጠው አንዳንዶቹ «ምን እናድርግ?» ብለው ሊያደርጉት የሚገባቸውን ያሳውቃቸው ዘንድ በጠየቁት ጊዜ ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ የመለሰላቸው «ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁ ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ» የሚል መልስ ነው። ሐዋ.፪፥፴፯–፴፰።

እምነት መሠረት ነው። ፍጹም የሚሆነው ግን በጥምቀት ነው።

እምነት ብቻ በቂ ቢሆን ኖሮ «እመኑ ብቻ ኃጢአታችሁ ይሠረይላችኋል» ባላቸው እንዲጠመቁም ባላስገደዳቸው ነበር። በሃይማኖት ጸሎታችንም «ኃጢአት በሚሠረይባት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን» የምንለው በዚህ መሠረት ነው።

፬. በጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አብረን እንሞታለን ከእርሱም ጋር እንነሣለን። ማንኛውም ክርስቲያን በማናቸውም ነገር ክርስቶስን ሊመስል ይገባዋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔን ምሰሉ» ብሏልና። ስለዚህ ሞቱን በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል – ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን» ሮሜ.፮፥፭።

በጥምቀት ከጌታ ጋር አብረን ልንሞትና ልንቀበር ያስፈልጋል። እንዴት? ቅዱስ ጳውሎስ የዚህን መልስ እንዲህ ሲል ገልጾታል። «ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን» ሮሜ.፮፥፫–፬። ወደ ቆላስይስ ሰዎች በላከው መልእክቱም ላይ «በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር ሥራ በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ» ብሏል። ቆላ.፪፥፲፪።

ስለዚህ «ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን» ሮሜ.፮፥፰።

ቤተ ክርስቲያናችን በጥምቀት ከጌታ ጋር መቀበራችንን ለማረጋገጥ አጥማቂው ካህን ተጠማቂውን በተጠራቀመ (ለመጠመቅ በተሞላ) ውኃ ውስጥ መላ አካሉን በማጥለቅ ነው የሚያጠምቀው።

፩. በጥምቀት አዲስ ሕይወት ይገኛል

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲያረጋግጥ «እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን» ብሏል። ሮሜ.፮፥፬።

የቀደመው በኃጢአት ምክንያት ያደፈ ሰውነታችን የሚታደሰው፣ የሚቀደሰውና አዲስ ሕይወትን የምናገኘው በጥምቀት ነው።

፮. በጥምቀት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ እንሆናለን። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የገላትያ ክርስቲያኖችን ሲያስተምር «ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና» ገላ.፫፥፳፯። በጥምቀት በደሙ ከዋጀን ከፈጣሪያችን ጋር አንድ እንሆናለን። በተጠመቅን ጊዜ አዲሱን ሕይወት እንጎናጸፋለን፤ ፈጣሪውን መስሎ በተፈጠረው በቀድሞው ሰው በአዳም በደል ምክንያት አጥተነው የነበረውን ንጽሕናና ቅድስና እናገኛለን። እንግዲህ እግዚአብሔር ያደለውን አዲሱን ሰውነት የምንለብሰውና የክርስቶስ ተከታዮች የምንሆነው በጥምቀት ነው።

፯. በጥምቀት የቤተ ክርስቲያን አባል እንሆናለን። በዘመን አሪት የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመሆን መገረዝ ሃይማኖታዊ ግዴታ ነበር። አሕዛብ በቁልፈት፣ እስራኤል በግዝረት ይለዩ ነበርና። ለዚህም ነው የአብርሃም ልጆች ሁሉ በተወለዱ በስምንተኛው ቀን እንዲገረዙ ሕግ የወጣው። ግዝረት ደግሞ ሊመጣ ላለው ለጥምቀት ምሳሌ ነው። ቆላ.፪፥፲፩–፲፫።

ግዝረት ለሕዝበ እግዚአብሔር የአብርሃም የቃል ኪዳን ተሳታፊዎች የመሆናቸው መለያ ምልክት እንደሆነ ሁሉ፤ ጥምቀትም በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የጸጋው ግምጃ ቤት ከሆነች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ጸጋ ተካፋይ ያደርገዋል። ስለዚህ በጥምቀት የቤተ ክርስቲያን አባል መሆናችን ይረጋገጣል።

## የጥምቀት ምሳሌ በብሉይ ኪዳን

ኖኅና ቤተሰቡ ከጥፋት የዳኑባት መርከብ የአማናዊቱ ቤተክርስቲያን ምሳሌ መሆንዋ በመጽሐፍ ቅዱስ የተረጋገጠ ነው። ፈሪሃ እግዚአብሔር



በልቡናቸው ያደረገው ኖኅና ቤተሰቡ ከጥፋት ሲድኑ ለእግዚአብሔር ያልታዘዙትና የእግዚአብሔርን ድምፅ ያልሰሙት የኖኅ ዘመን ሰዎች በውኃ ጠፍተዋል። ይህም ለአማናዊው ጥምቀት ምሳሌነት እንዳለው ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ሲገልጽ (ሲያስተምር) «ጥቂቶች ማለትም ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ የእግዚአብሔር ትዕግስት በኖኅ ዘመን በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም። ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድናል። የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነው እንጂ» ፩ጴጥ.፫፥፳–፳፩።

ኖኅና ቤተሰቡ የዳኑባት መርከብ ምሳሌዋ በሆነው በአንዲቱ ቤተክርስቲያን የሚደረገው ጥምቀት ከፍዳ ያነጻናል፤ ከዲያብሎስ ቁራኝነትም ያላቅቀናል። ቅዱስ ጴጥሮስ ድኅነት በጥምቀት መሆኑን ሲገልጽ «ይህም ውኃ ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድናል» ብሏል።

ግዝረት – ግዝረት የእግዚአብሔር ሕዝብ መለያ ምልክት ነበር። ያልተገረዘ ሁሉ የአብርሃም ልጅ አይባልም ነበር። ከሕዝቡም ተለይቶ እንዲጠፋ እግዚአብሔር አዝዞ ነበር። ዘፍ.፲፯፥፲፬። እንደዚሁም ሁሉ «ከውኃና ከመንፈስ ያልተወለደ» ማለትም ያልተጠመቀ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም ጽኑ ፍዳ ወዳለበት ገሃነም ይወርዳል እንጂ! ምክንያትም መንግሥተ ሰማይ ካልገባ ያለው ምርጫ ገሃነም መጣል ነውና። ዮሐ.፫፥፫–፮።

ስለዚህ ግዝረት ለሕዝበ እግዚአብሔር ግዴታ እንደ ነበረ ሁሉ ጥምቀትም ለክርስቲያኖች ሊፈጽሙት የሚገባ ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው።

ግዝረት ሊመጣ ላለው ለጥምቀት ምሳሌው መሆኑን ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስረዳ «በክርስቶስ ገዛሪነት የኃጢአትን ሕዋስ ሰንኮፍ ቆርጦ በመጣል ሰው ሠራሽ ያይደለ ግዝረትን የተገዘራችሁበት፤ በጥምቀት ከእሱ ጋር ተቀብራችሁ ከሙታን ለይቶ ባስነሣው በእግዚአብሔር ረዳትነትም በሃይማኖት ከእሱ ጋር ለመኖር በእስዋ ተነሣችሁ» ብሏል። ቆላ.፪፥፲–፲፪።

ግዝረት ማለት ከአካል ላይ ሥጋን ቆርጦ መጣል እንደሆነ ሁሉ ጥምቀትም ሐዋርያው እንዳስተማረን የኃጢአትን ሰንኮፍ ከሕይወታችን

ቆርጦ መጣል (ማስወገድ) ነው። የብሉይ ኪዳን ግዝረት በሰው አማካኝነት የሚፈጸም እንደነበረው ሁሉ የኃጢአት ሥሩ ተቆርጦ ተመንግሎ የሚጣልባት ጥምቀት ደግሞ በካህናት አማካኝነት ትፈጸማለች። ዳሩ ግን የኃጢአትን ሰንኮፍ ቆርጦ ከሕይወታችን የሚያስወግደው (የሚጥለው) በስሙ አምነን የተጠመቅንበት መድኃኒተ ዓለም ክርስቶስ ነው።

አንድ ሰው ሲገረዝ ከአካሉ ደም ይፈሳል። እንደዚሁም ሁሉ በክርስቶስ ደም የተዋጀን ክርስቲያኖች ከኃጢአታችን የታጠብንበትን የጌታ ደም በጥምቀት እናገኘዋለን።

ግዝረት ከአንድ ጊዜ በላይ እንደማይሆንና ሊደገምም እንደማይችል ሁሉ ጥምቀትም የማትደገም፣ የማትከለስ አንዲት ናት። ሁለት ጊዜ መጠመቅ አይቻልም። ኤፌ.፬፥፭። መጠመቅ ከክርስቶስ ጋር በሞቱ መተባበር ነው። ሮሜ.፮፥፫። ጌታ የሞተው አንድ ጊዜ ነውና ጥምቀትም አንድ ጊዜ ነው።

በሰው እጅ ያልተደረገ በክርስቶስ ገዛሪነት የኃጢአት ሥር ተቆርጦ የሚወገድበት ግዝረት ጥምቀት ነው።

የእሥራኤል ባሕረ ኤርትራን ማቋረጥ ሌላው የጥምቀት ምሳሌ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን እንዲህ ሲል ገልጦታል «ወንድሞች ሆይ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ። ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ። ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ።» ፩ቆሮ.፲፥፩–፪።

እሥራኤል ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር እንደ ተጠመቁ እኛም አንድነታችን በደሙ ከኃጢአታችን ካጠበን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንዲሆን እንጠመቃለን።

እስራኤል ከዘመናት የባርነት ቀንበር የተላቀቁትና ነፃ የወጡት፣ የኤርትራን ባሕር ከኃይለኛው ከፈርዖንም እጅ የዳኑት የኤርትራን ባሕር ተሻግረው ነው። የኤርትራ ባሕር ለፈርዖንና ለሠራዊቱ ሞትን ሲያስከትልባቸው ለእስራኤል ግን ሕይወት፣ ደስታ፣ ነፃነትን አጎናጽፏቸዋል።



እኛም ለርኩሳን አጋንንት ከመገዛት፣ ከፍዳ፣ ከመርገምና ከዘላለም ሞት ነፃ የምንሆነው በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነን ስንጠመቅ ነው። የኤርትራ–ባሕር ለፈርዖንና ሠራዊቱ መጥፊያ እንደሆነ በጥምቀትም አጋንንት ድል ይመታሉ። ለዚህ ነው በሥርዓተ ጥምቀታችን ተጠማቂው ከተጠመቀ በኋላ ከምዕራብ (ሲዖል) ወደ ምሥራቅ (ገነት) የሚዞረው።

የሶርያ ንጉሥ ሠራዊት አለቃ ንዕማን ከለምጽ የዳነው በዮርዳኖስ ወንዝ ታጥቦ ነው። በነቢይ በታዘዘው መሠረት በዮርዳኖስ ውኃ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ በማለት ታጥቦ ሥጋው እንደገና እንደ ትንሽ ብላቴና ሥጋ ንጹሕ ሆኖ መመለሱን በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እናገኘዋለን። ፪ነገ.፭፥፫–፲፬።

እኛም ከኃጢአት ደዌ የምንነጻውና ያረጀው ሕይወታችን ሊታደስ የሚችለው በጥምቀት ነው። ስንጠመቅ የክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን እንዳጠበን ማረጋገጣችን ነውና።

ነቢየ እግዚአብሔር ሕዝቅኤል መንፈስ ቅዱስ ገልጦለት እንዲህ ብሏል «በውኃም አጠብሁሽ፤ ከደምሽም አጠራሁሽ፤ በዘይትም ቀባሁሽ» ሕዝ.፲፮፥፱።

ለጊዜው ይህ አነጋገር በኃጢአት ለተሞላችው ለኢየሩሳሌም የተነገረ ቢሆንም ፍጻሜው ግን በኃጢአት ለተበላሸው ለሰው ሁሉ ሕይወት የተነገረ መሆኑ የታወቀ ነው። «ባንቺ ዘንድ ባለፍሁና ባየሁሽ ጊዜ እነሆ ጊዜሽ የፍቅር ጊዜ ነበር። እኔም መጎናጸፊያዬን በላይሽ ዘረጋሁ። ኀፍረተ ሥጋሽንም ከደንሁ፤ ማልሁልሽም ከአንቺም ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። አንቺም ለእኔ ሆንሽ» ሕዝ.፲፮፥፰።

እግዚአብሔር በምሕረቱ ሰውን በጎበኘበት ወቅት በፍጹም ፍቅሩ ስቦ ነው የሰውን ልጅ ያቀረበው። ጌታችንም እርቃኑን በመሰቀል የእኛን ከኃጢአት መራቆት አስቀርቶልናል። የክብር የሕይወት መጎናጸፊያ አጎናጽፎናል። ስለ እኛ መከራን ተቀበለ የእርሱ አደረገን። «በውኃ አጠብሁሽ» የሚለው «ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ መወለድን» ያስረዳናል። ይኸውም በጥምቀት ነው። በጥምቀት ከዘላለም የኃጢአት ባርነት መላቀቃችንን ሲያስገነዝበን «ከደምሽም አጠራሁሽ» ብሏል።

በተጨማሪም ጥምቀት በቅብዐ ሜሮን ማኅተምነት እንደሚጸና «በዘይትም ቀባሁሽ» በማለት አረጋግጦልናል።

«አንቺም የእኔ ሆንሽ» እንዳለው ሁሉ ተጠማቂውም በጥምቀት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የፈጸመውን የቤዛነት ሥራ ሁሉ አግኝቶ የእርሱ ወገን መሆኑን ያስረዳል።

## አጥማቂው ማነው?

ሊያጠምቁ የሚገባቸው ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ሰዎች ማለትም ቄሳውስት ወይም ጳጳሳት መሆን እንዳለባቸው የቤተክርስቲያን ቀኖና ያዛል። ዳሩ ግን በክርስቶስ ያመነ ሁሉ ካህን ነውና ሊያጠምቅ ሥልጣን አለው የሚለው አመለካከት የተሳሳተ ነው። ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም የሚገባቸው ሥልጣነ ክህነት የተሰጣቸው ብቻ እንጂ ሥልጣነ ክህነት የሌላቸው ምእመናን ሊሆኑ አይገባም። አይሆንምም። ሥልጣነ ክህነት በሌለው ሰው የተደረገ ጥምቀት አማናዊ ጥምቀት አይደለም። ከሥላሴም ልጅነትን አያሰጥም። ምክንያቱም ጌታ አጥምቁ ብሎ የላካቸው ከሌላው ሁሉ መርጦ የሾማቸውን ሐዋርያቱን እንጂ ያመኑትን ሁሉ አይደለም። ማቴ.፳፰፥፲፱። ማር.፲፮፥፲፮።

ሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን ከጌታ መቀበላቸው በወንጌል ተመዝግቧል። «ይህንንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ» ይላል። ዮሐ.፳፥፳፪። ይህም ሥልጣነ ክህነት ለመሆኑ ማረጋገጫችን «ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል። የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው።» ዮሐ.፳፥፳፫። በማለት ልጅነትን ሳይሆን ሥልጣነ ክህነትን እንደሰጣቸው ቅዱስ ወንጌል ያስተምረናል። ምክንያቱም ልጅነት ኃጢአት ሊያስተሠርይ ከኃጢአት ሊፈታ ሊያስር አይችልምና ነው። ሥልጣነ ክህነት ግን ኃጢአትን ሊያስተሠርይ፣ ከኃጢአት ሊፈታና ሊያስር ይችላል።

ስለዚህ ለማጥመቅም ሆነ ሌሎችንም ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ለመፈጸም ሥልጣኑ ያላቸው ካህናት እንጂ ሌላው ምእመን አይደለም። በዚህም የተነሣ ቤተክርስቲያን በምእመናን የሚፈጸመውን ጥምቀት እውነተኛ ጥምቀት አድርጋ አትቀበለውም።



## የጥምቀት አፈጻጸሙ

ጥምቀት አጥመቀ (አጠመቀ) ካለው ግስ የወጣ ነው። ፍቺውም በግብር መንከር፣ መድፈቅ፣ መዝፈቅ ሲሆን በተገብሮ መነከር፣ መደፈቅ፣ መዘፈቅ መላ አካልን ውኃ ውስጥ ማስገባት ማለት ነው።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን የምታጠምቀው ከላይ እንደታተተው በትርጉሙ መሠረት ተጠማቂውን ውኃ ውስጥ በማጥለቅ ነው። ይህም ማለት ውኃው የተጠማቂውን መላ ሰውነት እስኪያለብስ ድረስ መላ አካሉን ውኃ ውስጥ በመድፈቅ ወይም ከራስ ጀምሮ በሰውነት ላይ በማፍሰስ ነው። ሥርዓተ ጥምቀቱ በዘፈቀደ የሚከናወን ሳይሆን ትርጉምና ምሳሌ ባለው ሥርዓትን በጠበቀ መልኩ ነው። በቅድሚያ ለማጥመቂያ በተዘጋጀው ውኃ ላይ ካህኑ መጽሐፈ ክርስትና (ጸሎተ ጥምቀት) ያደርስበታል። ጸሎተ ጥምቀቱን ካህኑ ሲጸልይ እጁን በተጠማቂው ላይ ጭኖ ነው።

የተጠማቂውን የክርስትና ስም ሲሰይምም እጁን በትእምርተ መስቀል በተጠማቂው ላይ አኑሮ «ይኩን ስምከ እገሌ» እያለ ስመ ጥምቀቱን ሦስት ጊዜ በመጥራት ነው።

በሚጠመቅበት ጊዜ ተጠማቂው ፊቱን ወደ ምዕራብ ይመልሳል። ወደ ምዕራብ የሚመልስበት ምክንያት አዳም ትእዛዘ እግዚአብሔርን ጥሶ ወደ ሲኦል መውረዱን ለማዘከር ነው። ሲኦል በምዕራብ ናትና።

በመቀጠል ተጠማቂው በውኃው አንገር መቆም ይኖርበታል። ይኸውም የሚያመለክተው አዳም አባታችን የድኅነትን ተስፋ መስማቱን ለማዘከር ነው። ምክንያቱም ድኅነት በጥምቀት ነውና ማር.፲፮፥፲፮።

ካህኑ ካጠመቀው በኋላ የተጠማቂውን እጁን ይዞ ወደ ምሥራቅ ፊቱን የሚመልስበት ምክንያት ጌታ በጥምቀት ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከሲኦል ወደ ገነት እንደመለሰን ለማስረዳት ነው። ምሥራቅ የገነት( ዘፍ.፪፥፰)፤ የእመቤታችን (ሕዝ.፵፬፥፩-፱)። ምሳሌ ጌታ የተሰቀለባት መድኀኒት የተገኘባት ናትና። «እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።» ዮሐ.፫፥፭።

ካህኑ በተጠማቂው ፊት ላይ «ንሣእ መንፈስ ቅዱሰ» ትርጉሙ «መንፈስ ቅዱስን ተቀበል» እያለ እፍ ይልበታል። ቀጥሎ ቅብዐ ሜሮን ይቀባዋል። ካህኑ ሜሮን ሲቀባ የተጠማቂውን ሰውነት ክፍል ክፍሉን እየለየ በትእምርተ መስቀል ሠላሳ ስድስት ሕዋሳቱን ይቀባዋል። በመጽሐፈ ጥምቀት እንደተገለጠው ካህኑ ሴቷን ካደገች በኋላ አምና የምትጠመቀውን ካንገቷ በላይ ያሉትን አካላቷን ይቀባል። ካንገቷ በታች ያሉት አካላቷን ዲያቆናዊት ሴት የካህኑን እጅ ይዛ ትቀባታለች። በጸሎተ ቡራኬና አንብሮተ እድ በተጠማቂው ላይ ይጸልያል። ከዚህ በኋላ ለክርስትና አባቱ ሲሰጠው አዲስ ልብስ ያለብሰዋል። ይህም አበሳው እንደ ተወገደለት መታደስን እንዳገኘ ያሳያል። ዘካ.፫፥፩–፭።

ጥምቀት በሚያጠልቅ ውኃ እንዲሆን የታዘዘበት ምክንያት የተጠማቂውን መላ አካል እንዲያጠልቀው ተብሎ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን «ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን»። ሮሜ.፮፥፴፩።

በጥምቀት ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረን መቀበራችንን ሐዋርያው አስገንዝቦናል። መቃብር ደግሞ መላ ሰውነትን የሚውጥ (የሚያለብስ) እንደ መሆኑ ከጌታ ጋር አብረን የመቀበራችንን ምሥጢር የሚገልጠው ጥምቀትም መላ አካላችንን ማለትም ከራስ ጠጉራችን እስከ እግር ጥፍራችን ድረስ የሚያጠልቅ (የሚያለብስ) ውኃ መሆን አለበት።

በተጨማሪም በጥምቀት ከእግዚአብሔር በጸጋ የምንወለድ በመሆኑ መላ አካላችን ውኃ ውስጥ ጠልቆ መውጣት ይኖርበታል። የሥን ፍጥረትን ሕግ ተከትለን ስንሄድ መወለድ ከተሰወረ ከማይታይ ጨለማ ከሆነ ክፍል ብርሃን ወደ ሆነ ዓለም መውጣት እንደሆነ ሁሉ በጥምቀትም ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተጎናጽፈን ብርሃን ለብሰን ከእግዚአብሔር የምንወለድ በመሆኑ ተጠማቂው መላ አካሉ ውኃ ውስጥ ጠልቆ መውጣት ይኖርበታል። ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ መወለዱን ለማረጋገጥ።



ካህኑ ተጠማቂውን በውኃው ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ የሚያደርግበት ምክንያቱ ምንድን ነው? ብሎ ለሚጠይቅ መልሱ እንደሚከተለው ተገልጿል።

ካህኑ ተጠማቂውን በውኃው ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያደረገ ማጥመቁ ምሳሌ አለው። ቀደም ተብሎ እንደ ተገለጠው መጥለቅ ወደ መቃብር የመውረድ ሲሆን መውጣት (ብቅ) ማለት ደግሞ የትንሣኤ ምሳሌ ነው። ይህ ግብር ሦስት ጊዜ መፈጸሙ ደግሞ የሥላሴ ምሳሌ ሲሆን ግብሩ ደግሞ አንድ ዓይነት መሆኑ የአንድነት ምሳሌ ነው። እንዲሁም በውኃው ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ማለቱ ክርስቶስ በከርሠ መቃብር ፫ መዓልት ፫ ሌሊት አድሮ የመነሣቱ ምሳሌ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም ጥምቀት ውኃ ውስጥ መላ አካልን በማጥለቅ መከናወን እንዳለበት ያስረዳል። ለዚህም እንደ ምሳሌነት አድርገን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀትና ቅዱስ ፊልጶስ ያጠመቀውን የኢትዮጵያ ንግሥት የሕንደኬን ጃንደረባ ልንወስድ እንችላለን። ጌታ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ መላ አካሉን ውኃ ውስጥ ጠልቆ በመውጣት እንደ ነበር ማስተዋል ይቻላል። ይህንንም ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ እንዲህ ሲል ገልጾታል። «ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ» ማቴ.፫፥፲፮። ማር.፩፥፲።

ሐዋርያው ፊልጶስም ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ባጠመቀበት ጊዜ ወደ ወንዝ አውርዶ መላ አካሉን ውኃ ውስጥ አጥልቆ እንዳጠመቀው «ከውኃ ከወጣ በኋላ» የሚለው አነጋገር ያስገነዝበናል። የሐዋ.፰፥፴፰–፴፱።

የጥምቀት ምሥጢራዊ ትርጉሙ ከክርስቶስ ጋር አብሮ መቀበር ማለት መሆኑን ከላይ ገልጸናል። መቃብር ደግሞ ሙሉ አካልን የሚውጥ እንጂ ከፊሉን ውጦ ሌላውን የሚያስቀር አይደለም። ሁሉም አካል በመሬት ውስጥ ይዋጣል። ከጌታችን ጋር አብረን መቀበራችንን ለማስመስከር ስንጠመቅም መላ አካላችን ውኃ ውስጥ ሊጠልቅ እንደሚገባውም ከላይ ተገልጾአል። ለዚህ ማጠናከሪያ የሚሆኑ ማስረጃዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ መጥቀስ ቢቻልም «ለጠቢብ ሰው አንዲት ቃል ትበቃለች» ስለተባለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች በላከው መልእክት ላይ ጥምቀትን አስመልክቶ የተናገረውን

በመጥቀስ ይህን ንዑስ ርእሳችንን እናጠቃልላለን። «በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ለይቶ በአስነሳው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ» ቆላ.፪፥፲፪። በተጨማሪም በጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የማጥመቂያ ገንዳዎች መገኘታቸው የመጠመቂያ ውኃ ሰውነትን ለማጥለቅ እንዲችል ሆኖ መዘጋጀት እንዳለበት ያስረዳል።

## የሕፃናት ጥምቀት

አንዳንድ ሰዎች የሕፃናትን ጥምቀት ሲነቅፉና ትክክለኛ ጥምቀትም እንዳልሆነ ሲናገሩ ይሰማሉ። ይህ ተራ ትችት ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለው ነው። እነዚህ ክፍሎች ራሳቸው ከአእምሮአቸው አመንጭተው ላስተማሩት ሐሰተኛ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ ያስተማረው አስመስለው ለማቅረብ ሲሞክሩም ይስተዋላሉ። ለምሳሌ ያህል «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» የሚለውን በመጥቀስ በመጀመሪያ እምነት ይቀድማል፤ ለማመን ደግሞ መማር፣ ማወቅ፣ ማገናዘብና አምኜአለሁ ተቀብያለሁ ሊባል ይገባል። ሕፃናት ግን የሚያውቁት ነገር ስለሌለ አላመኑም። ስለዚህ ያላመኑ ሕፃናትን ማጥመቅ ተገቢ አይደለም ይላሉ። ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን ወንዶችን በተወለዱ በ፵ ቀናቸው ሴቶችን በተወለዱ በ፹ ቀናቸው የምታጠምቀው መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጋ ነው።

ሀ. ሕፃናት የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኙ ወላጆቻቸውና ቤተ ክርስቲያን ይሻሉ። ያለ ጥምቀት ደግሞ ዘላለማዊ ሕይወት አይገኝም። ጌታ እንዳስተማረው «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» ዮሐ.፫፥፭። ስለዚህ ሕፃናት በወላጆቻቸው እምነት የተነሣ የወላጆቻቸውን እምነት የእነርሱ እምነት በማድረግ ገና በሕፃንነት ጊዜያቸው ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጭ እንዳይሆኑ ታጠምቃቸዋለች። ዳሩ ግን ሳይጠመቁ ቢሞቱ ጌታ እንደ ተናገረው መንግሥተ ሰማይን አያዩአትም። እንደ ጌታ ትምህርት የምንሄድ ከሆነ «ሰው» ብሎ ባጠቃላይ ሕፃናትን አዋቂዎችን ሁሉ ጨምሮ ተናገረ እንጂ «ከሕፃናት በስተቀር» አላለም። «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም።»



ለ. ሕፃናት በመጠመቃቸው የቤተ ክርስቲያን አባል ስለሚሆኑ የእግዚአብሔር ጸጋ ተከፋዮች ይሆናሉ፤ ገና ከሕፃንነታቸው ጀምሮ የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት ይለማመዳሉ። በዚህ ፈንታ ከሕፃንነታቸው ጊዜ ጀምረው ከእግዚአብሔር ጸጋ ተራቁተው የሚያድጉ ከሆነ ለመጥፎ ሕይወት ይዳረጋሉ።

ሐ. እንዲሁም ጌታችን «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ሲል በዚያን ዘመን ገና ወንጌል መሰበክ በጀመረበት ጊዜ ላሉት ሰዎች የተነገረ ሲሆን ከክህደታቸውና ከጥርጥራቸው ተመልሰው የሚመጡ ሁሉም አምነው መጠመቅ እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ነው። ሕፃናት የእግዚአብሔር ልጆች ሊሆኑ እንደሚገባ ጌታችን ሲገልጽ «ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተውአቸው አትከልክሏቸው መንግሥተ ሰማያት እንደ እነርሱ ላሉት ናትና» ብሏል። ማቴ.፲፱፥፲፬። በዚህ የጌታ ትምህርት መሠረት ቤተክርስቲያንም የመሪዋንና የመሥራችዋን የክርስቶስን ቃል መርሕ በማድረግ ወላጆች ልጆቻቸውን ታቅፈው ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዘው በመምጣት ተጠምቀው የእግዚአብሔር ልጆች የቤተ ክርስቲያን አባላት እንዲሆኑ ሲያደርጉ እርሷ ከልካይ አትሆንም። ጌታ ተውአቸው ይምጡ ልጅነትን፣ ጸጋን፣ በረከትን ያግኙ ብሏልና።

ሕፃናት ንጹሐን አእምሮ መሆናቸውን ጌታ ሲያስተምር «እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ መንግሥተ ሰማይ አትገቡም ብሏል።

መ. መጽሐፍ ቅዱስ ሕፃናት መጠመቃቸውን ያስተምረናል፤ የሚከተሉት ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው።

፩. በእሥር ቤቱ በተደረገው ተአምር የተደነቀውና ወደ ክርስትና እምነት የተሳበው የወኅኒ ጠባቂ ጳውሎስና ሲላስ ካስተማሩትና ካሳመኑት በኋላ ከነቤተሰቡ መጠመቁ ተገልጾአል። እንግዲህ የተሰበከውና ያመነው የወኅኒ ጠባቂው ሲሆን የተጠመቁት ግን ሕፃናትን ጨምሮ መላው ቤተሰቡ ነው። የሐዋ.፲፮፥፴፫።

፪. ልብዋን ጌታ የከፈተላትና ቃሉን አድምጣ ሕይወትዋን ለክርስቶስ የሰጠችው ልድያ ባመነች ጊዜ የተጠመቀችው ብቻዋን ሳይሆን ከመላው ቤተሰብዋ ጋር ነው። ከቤተሰቡ መካከል ሕፃናት መኖራቸውም የማይቀር ነው። የሐዋ.፲፮፥፲፭።

፫. ቅዱስ ጳውሎስ «የእስጢፋኖስንም ቤተሰቦች ደግሞ አጥምቄአለሁ» በማለት የእስጢፋኖስን መላ ቤተሰብ ማጥመቁን ገልጾአል። ፩ቆሮ.፩፥፲፮። እነዚህ የእስጢፋኖስ ቤተሰቦች ሁሉ ትላልቆች ብቻ ናቸውን? ሕፃናት የሉበትም ይሆን?

፬. በሐዋ.ሥራ ፪ ላይ እንደተገለጸው በበዓለ ሃምሳ ከ፫ሺህ ያላነሱ ሰዎች በጴጥሮስ ተሰበኩ። ከእነዚያ ውስጥ ብዙዎቹ መጠመቃቸው ተገልጾአል። የተጠመቁት ግን ዐዋቂዎች ብቻ መሆናቸውን የሚገልጽ የለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሕፃናትን ጥምቀት የሚነቅፍ ባንዱም ክፍል ተጽፎ አናገኝም።

እስከ አሁን እንደ ተገለጸው መጽሐፍ ቅዱስ የሕፃናትን ጥምቀት ያልነቀፈ ሲሆን በብሉይ ኪዳን የጥምቀት ምሳሌ የነበሩትን ስንመለከት ይበልጥ የሕፃናትን ጥምቀት ትክክለኛነት ያረጋግጥልናል።

ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ ነው። ሕፃናት በተወለዱ በስምንተኛው ቀን ይገረዙ ነበር። ዘፍ.፲፯፥፲፪። እንግዲህ ሕፃናቱ የሚገረዙት በወላጆቻቸው እምነት እንጂ እነርሱ ዐውቀው ግረዙን ብለው አይደለም።

የእሥራኤል ቀይ ባሕርን ማቋረጥ የጥምቀት ምሳሌ መሆኑ በ፩ቆሮ.፲፥፪ የተገለጸ ሲሆን ባሕሩን ያቋረጡት ዐዋቂዎች ብቻ ሳይሆኑ ሕፃናትም ጭምር ናቸው። ከባርነት ከፈርዖን አገዛዝ ነፃ የወጡት ሕፃናቱ ጭምር ናቸው።

እሥራኤል ከበኩር ሞት የዳኑበት የአንድ ዓመት ጠቦት በግ ደም ምሳሌነቱ የጌታ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በዚያን ጊዜ በበጉ ደም አማካኝነት ከሞት የዳኑት የታዘዙትን እሺ በጄ ብለው የፈጸሙት ዐዋቂዎች ብቻ ሳይሆኑ የእነርሱ ልጆችም ጭምር ናቸው። እንግዲህ በወላጆቻቸው እምነት ሕፃናቱ መዳናቸውን ልናስተውል ይገባናል።

ስለዚህ ሕፃናት በአእምሮ ባልበሰሉበትና ስለ ጥምቀታቸው አምነው ተቀብየዋለሁ ሳይሉ የሚደረገው ጥምቀት እውነተኛ ጥምቀት አይደለም የሚሉ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ከላይ እንደ ተገለጸው ሁሉ መሳሳታቸው የተረጋገጠ ነው።



እግዚአብሔር ሰውን ይመርጣል እንጂ ሰው እግዚአብሔርን አይመርጥም። ራሱ ባለቤቱ እንዳስተማረው ሁሉ «እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም» ብሏል። ዮሐ.፲፭፥፲፮። ድኅነት በእግዚአብሔር ቸርነት የሚገኝ እንጂ በሰው ትምህርትና ዕውቀት የሚሸመት ወይም የሚገበይ ዕቃ አይደለም። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያናችን ሕፃናትን ማጥመቅዋ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቀደሙት አበው ባገኘችው ትምህርት መሠረት ነው።

## በማን ስም ልንጠመቅ ይገባናል?

ሐዋርያዊትና ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ በሥላሴ ስም ታጠምቃለች። ይህም ጌታ ራሱ ለሐዋርያቱ «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው...ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው።» ማቴ.፳፰፥፲፱። ብሎ የሰጠውን አምላካዊ ቃል መሠረት ያደረገ ነው።

ስለዚህ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም ከተመሠረተችበት ዘመን አንስቶ በሥላሴ (በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ) ስም መጠመቅ የድኅነት በር ቁልፍ መሆኑን ስታስተምርና ተግባራዊ ስታደርግም ኖራለች።

ይህን የወንጌል ቃል የሚያጣምሙ መናፍቃን ‹በኢየሱስ ስም ብቻ መጠመቅ አለብን እንጂ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቅ የለብንም› ይላሉ። ለዚህም ማስረጃ አድርገው ለማቅረብ የሚሞክሩት የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስን አነጋገር ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ከየሃገሩ ለተሰበሰቡት አይሁድ የምሥራቹን ቃል ድምጹን ከፍ አድርጐ ባሰማቸው ጊዜ ልባቸው ተነካ። ስለዚህም «ምን እናድርግ? » ብለው ሊያደርጉት የሚገባቸውን እንዲነግራቸው ጠየቁት። እርሱም «ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁ ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ» አላቸው። የሐዋ.፪፥፴፰።

ሐዋርያው «በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ» ብሎ ማስተማሩ ለምን ነበር? ለምን ጌታ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ ያለውን ተከትሎ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠመቁ አላለም? የሚል ጥያቄ ለሚያነሣ ሁሉ ምክንያቱ እንደሚከተለው ነው።

በበዓለ ሃምሳ ከየሀገሩ የተሰበሰቡት አይሁድ ከጥንት ጀምሮ በነቢያት እንደበት ይወርዳል ይወለዳል እየተባለ የተነገረለትን መሲሕን ተስፋ ያደርጉ ነበር። ሐዋርያውም ያ የተስፋው ቃል ዛሬ መፈጸሙንና በተስፋው ቃል መሠረት ከድንግል ማርያም በሥጋ ተወልዶ ፴፫ ዓመት ከ፫ ወር በምድር ላይ ተመላልሦ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የሰውን ልጅ በደሙ የዋጀው ኢየሱስ ክርስቶስ ትንቢት የተነገረለት ሱባዔ የተቆጠረለት መሆኑን አምነው በስሙ ካልተጠመቁ በስተቀር ‹አብርሃም አባታችን እግዚአብሔር አምላካችን በሚለው› እምነት ብቻ አምነው ጌታን በሰቀሉት አይሁድ መንገድ የሚጓዙ ከሆነ እንደማይድኑ በመሲሕ አምነው በስሙም ከተጠመቁ ግን እንደ ሚድኑ ሊያስተምራቸው ስለ ፈለገ የጌታን ስም ለይቶ ጠራ። በዚህም የጌታን አዳኝነትና መሲሕነት አምነው እንዲቀበሉ በአጽንዖት መናገሩ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ሐዋርያት ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት ቤዛ የሆነልንን ጌታ ሰው ሁሉ አምኖ እንዲድን በየሄዱበት የጌታን አዳኝነትና የባሕርይ አምላክነት አስተምረዋል። የስብከታቸው ማዕከል የነበረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር። ምክንያቱም ክህደቱ ጸንቶ የነበረው በጌታ የባሕርይ አምላክነት ላይ ነበርና። በዚህ የተነሣ የእርሱን አዳኝነትና የባሕርይ አምላክነት ለማሳመን ጌታን የስብከታቸው ማዕከል አደረጉ።

## ጥምቀት አንዲት ናት

ጥምቀት የማትደገም የማትከለስ አንዲት ናት። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ልጅነትን የምናገኝባት ጥምቀት የማትደገምና የማትከለስ አንዲት ብቻ መሆንዋን ሲያስትምር «አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት...አለ» ብሏል። ኤፌ.፬፥፭።

ሃይማኖታቸው የቀና ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንትም «ኃጢአትን በምታስ ተሠርይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።» ብለው አስተምረዋል። በዚህ የተነሣ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን አንድ ጊዜ ያጠመቀችውን ድጋሚ አታጠምቅም። ነገር ግን ከቤተ ክርስቲያናችን ውጪ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ‹ተጠምቀን ነበር› የሚሉትን ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ሲቀርቡ በሥርዓቷ መሠረት አስተምራ አሳምና ታጠምቃቸዋለች። ምክንያቱም አማናዊትዋን ጥምቀት ቀድሞም አልፈጸሙምና።



በሌላ መልኩ ደግሞ ቀድሞ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ተጠምቆ ኋላ ግን ወደ ሌላ እምነት ቢገባ ተናዞ (ንስሐ ገብቶ) በማየ ጸሎት (መጽሐፈ ቄደር) ይረጫል እንጂ ድጋሚ አይጠመቅም። ቄደር የንስሐ እጽበት ነው። ያደፈ ልብስ እንደሚታጠብ ሁሉ ይህም ሰው ንጽሕት እምነቱን አሳድፏልና ከኃጢአቱ ለመታጠቡ ምልክት ይሆን ዘንድ በማየ ጸሎት ይታጠባል።

## ጥምቀት የማይደገምበት ምክንያት

ሀ. ጥምቀት ከእግዚአብሔር ዳግም የምንወለድበት ምሥጢር ነው። የሥጋን ልደት ስንመለከት ሰው ከእናቱ ማኅፀን የሚወጣው (የሚወለደው) አንድ ጊዜ ብቻ ነው። እንዲሁም እግዚአብሔርም በእውነት አንድ ጊዜ ወልዶናል። ስለዚህ አንድ ጊዜ ብቻ እንጠመቃለን።

ለ. ጥምቀት ከጌታ ሞትና ትንሣኤ ተሳታፊ የምንሆንበት ምሥጢር ነው። «በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ በጥምቀትም ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ» ቆላ.፪፥፲፪። ጌታ የሞተውና የተነሣው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። እንዲሁም እኛ ከእርሱ ጋር የምንቀበረውና የምንነሣው አንድ ጊዜ ብቻ ነው።

## ለምን በውኃ እንጠመቃለን?

፩. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው በውኃ ነው። እኛም እርሱን አብነት በማድረግ በውኃ ልንጠመቅ ይገባናል። ማቴ.፫፥፲፫–፲፮።

፪. ጌታ ለኒቆዲሞስ «እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» ስላለ እኛም የጌታን ትእዛዝ ለመፈጸም በውኃ እንጠመቃለን። ዮሐ.፫፥፭።

፫. ሐዋርያት ከጌታ በተማሩት መሠረት ያጠመቁት በውኃ ነው። ጴጥሮስም መልሶ «እነዚህ እንደ እኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ እንዳይጠመቁ ውኃን ይከለክላቸው ዘንድ የሚችል ማን ነው? አለ» የሐዋ.፲፥፵፯ና ፵፰ «ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ አጠመቀውም» የሐዋ.፰፥፴፰።

፬. ውኃ የሰውነትን እድፍ እንደሚያጠራ ሁሉ እንዲሁም ጥምቀት የነፍስን እድፍ ያስወግዳል ያነጻል።

፭. ውኃ መልክን ያሳያል እኛም በውኃ በመጠመቅ የሥላሴን ምሥጢር በዓይነ ሕሊናችን እናያለን።

፮. በጥንተ ፍጥረት መንፈስ እግዚአብሔር በውኃ ላይ ረብቦ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ይገልጻል «የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር» ዘፍ.፩፥፪። እንዲሁም በውኃ፣ በሕይወትና በመንፈስ ያለውን ግንኙነት ማስተዋል ይገባል። ልዑለ ባሕርይ ጌታ በነቢዩ በኤርምያስ አንደበት እንዲህ ሲል ተናግሯል «ሕዝቤ ሁለቱን ክፉ ነገሮች አድርገዋልና እኔን የሕያውን ውኃ ምንጭ ትተውኛል...» ኤር.፪፥፲፫።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ትምህርቱ «በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል» ብሎ አስተምሯል። ዮሐ.፯፥፴፰። ለሳምራዊቷ ሴትም «እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም። እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት» ዮሐ.፬፥፲፬።

ከላይ በተገለጸው መሠረት ውኃ የሕይወት ምልክት ነው። በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደምናነበው ውኃ ለሰማያዊው መንግሥት ለዘላለም ሕይወት ምሳሌ ሆኖ ተገልጿል። «እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደተተከለች ፍሬዋን በየጊዜው እንደምትሰጥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል»። መዝ.፩፥፫። እና የመሳሰሉትን ሁሉ እናገኛለን። ራእይ.፳፩፥፮፣ ፳፪፥፩፣ ፳፪፥፲፯።

እንግዲህ ውኃ ከክፉ ሕሊና ለመንጻታችንና ለመቀደሳችን ማረጋገጫ መሆኑን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል አስተምሯል። «ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ።» ዕብ.፲፥፳፪።

፯. ለንጊኖስ የተባለው ሐራዊ (ወታደር) የጌታን ቀኝ ጎን በጦር በወጋው ጊዜ ትኩስ ደምና ውኃ ባንድነት ፈሷል። ዮሐ.፲፱፥፴፬።



ደሙ ለመጠጣችን፣ ውኃው ለጥምቀታችን መሆኑን ሲያጠይቅ ነው። ይህንንም ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ እንዲህ ሲል ገልጾታል፣ «በውኃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በውኃና በደሙ እንጂ በውኃው ብቻ አይደለም። ፩ዮሐ.፭፥፮-፰።

፰. ውኃ በሁሉም ቤት ይገኛል። በሀብታሙም በድኃውም። ጥምቀትም ላመነ ሁሉ የተፈቀደ መሆኑን ለማጠየቅ በውኃ ሆኗል። ስለዚህም በውኃ ብቻ እንጠመቃለን። ሥርዓተ ጥምቀቱን የሚፈጽመው ካህን አሐዱ አብ ቅዱስ፣ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፣ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብሎ በእግዚአብሐር ቃል ሲባርከው ውኃው ተለውጦ በዕለተ ዓርብ ከጌታችን ቀኝ ጐን የፈሰሰውን ውኃ የሆናል።

## የጌታ ጥምቀት

የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት በብሉይ ኪዳን እንደ ነበሩት እንደ አይሁድና እንደ ዮሐንስ ያለ ጥምቀት አይደለም። ጥምቀተ አይሁድ ትዕዛዘ ኦሪትን ለጣሰ ሰው ይደረግ የነበረ የውኃ መታጠብ ነው። ክርክሰት የሚነጻው በውኃ በመታጠብ ነበር። ዘሌ.፲፭፥፩-፲፰።

የዮሐንስ ጥምቀት ደግሞ የንስሐ ነበር። ማቴ.፫፥፭ና፮።

ጌታ በዮሐንስ እጅ በባሕረ ዮርዳኖስ የተጠመቀው እንደ አይሁድ ሥርዓት ለመንጻት፣ እንደ ዮሐንስም ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት አልነበረም። ዳሩ ግን ስለሚከተሉት ምክንያቶች ተጠምቋል።

፩ኛ. ትሕትናን ለማስተማር። በአገልጋዩ (በፍጡሩ) በዮሐንስ እጅ መጠመቁ መምህረ ትሕትና መሆኑን ይገልጣል።

፪ኛ. በጥምቀት ዳግም ከእግዚአብሔር ለምንወለድ ለእኛ አርአያ ለመሆን።

፫ኛ. ዲያብሎስ በዮርዳኖስ ወንዝ ደብቆት የነበረውን የዕዳ ደብዳቤ ለመደምሰስ።

፬ኛ. በብሉይ ኪዳን በተለያየ ኅብርና ምሳሌ የነበረውን አንድነቱንና ሦስትነቱን ለመግለጥ «ሰማያት ተከፈቱ» የሚለው አነጋገር ሥውር የነበረው ይህ ምሥጢር መገለጡን ገሃድ መውጣቱን

የሚያስረዳ ነው። የተዘጋ ቤት ሲከፈት በውስጥ ያለው የተሠወረው እንደሚታይ ሁሉ ከሰው አእምሮ ረቅቆ የነበረው የሥላሴ ምሥጢርም በጌታ ጥምቀት መገለጡን ያረጋግጣል።

እንዲህም የክርስቶስ እውነተኛ አምላክነት በባ ፡ይ አባቱ በአብና በባሕርይ ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ተረጋግጧል።

## ጌታ ለምን በዮርዳኖስ ተጠመ

### ፩ኛ. ቀድሞ የተነገረውን ትንቢት ሊፈጽም

ልበ አምላክ ዳዊት ጌታ ሰው ከመሆኑ ከሺ ዘመን ቀደም ብሎ የጌታ ጥምቀት በዮርዳኖስ እንደሚሆን ትንቢት ተናግሯል። «ባሕር አየች ሸሸችም። ዮርዳኖስም ወደ ኋላ ተመለሰ። ተራሮች እንደ ኮርማዎች ኮረብቶችም እንደ ጠቦቶች ዘለሉ። አንቺ ባሕር የሸሸሽ አንቺም ዮርዳኖስ ወደ ኋላሽ የተመለስሽ ምን ሆናችኋል? እናንተም ተራሮች እንደ ኮርማዎች ኮረብቶችስ እንደ ጠቦቶች ለምን ዘለላችሁ? ከያዕቆብ አምላክ ፊት» መዝ.፩፻፲፫(፩፻፲፬)፫፥፯።

### ፪ኛ. ምሳሌውን አማናዊ ለማድረግ

ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ (ምንጩ) አንድ ነው። ዝቅ ብሎ በደሴት ይከፈላል፤ ከታች ወርዶ ደግሞ ይገናኛል። ዮርዳኖስ ከላይ ነቁ አንድ እንደ ሆነ የሰው ሁሉ ምንጩ አንድ አዳም የመሆኑ። ዝቅ ብሎ በደሴት መከፈሉ፤ እስራኤል በግዝረት አሕዛብ በቁልፈት የመለያየታቸው፤ ከታች ወረድ ብሎ መገናኘቱና ጌታም በመገናኛው ላይ መጠመቁ ሕዝብና አሕዛብን በጥምቀቱ አንድ ሊያደርግ መምጣቱን ያጠይቃል።

ኢዮብ ከደዌው የዳነው በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ነው። ኢዮብ የአዳም ምሳሌ፤ ደዌ የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ፤ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ነው። የአዳም ዘር ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ዳግም ተወልዶ ከመርገመ ሥጋና ከመርገመ ነፍስ ይላቀቃል።

እስራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት ገብተዋል። ምዕመናንም አምነው ተጠምቀው ገነት መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ።

ኤልያስ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ወደ ብሔረ ሕያዋን ዐርጓል፤ ምእመናንም አምነው ተጠምቀው ገነት መንግሥተ ሰማያት ለመግባታቸው ምሳሌ።



የኤልሳዕ ደቀ መዛሙርት «እነሆ በፊትህ የምንቀመጥበት ስፍራ ጠብቦናል። ወደ ዮርዳኖስም እንሂድ። ከእኛም እያንዳንዱ ከዚያ ምሰሶ ያዑጣ የምንቀመጥበትንም ሥፍራ በዚያ እንሥራ አሉት። እርሱም መምሕረ ትሕትና ነውና አብሯቸው ሄደ። ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ሲቆርጥ ምሳሩ ከዛቢያው ወልቆ ከባሕር ገባበት። «ጌታዬ ጥንቱን የተውሶ ያውም ጠፋ ተጨርሶ» አለው። የገባበትን አሳየኝ ብሎ የዛፍ ቅርፊት ቀርፎ አመሳቅሎ ቢመታው መዝቀጥ የማይቻለው የዛፍ ቅርፊት ዘቅጦ መዝቀጥ የሚገባውን ብረት ይዞት ወጥቷል። ይህም ሞት የማይገባው ጌታ ሞቶ፤ ሞት የሚገባው አዳምን ለማዳኑ ምሳሌ ነው።

ንዕማን በዮርዳኖስ ተጠምቆ ከለምጹ ተፈውሷል እናንተም በማሕፀነ ዮርዳኖስ ተጠምቃችሁ ከኃጢአት ከጉስቁልና ትነጻላችሁ ሲል በዮርዳኖስ ተጠምቋል።

### ፫ኛ. የዕዳ ደብዳቤያችንን ይደመስስልን ዘንድ

(ጌታ ወደ ዮርዳኖስ ሄዶ የተጠመቀበት ምሥጢሩ) ዲያብሎስ የጨለማ መጋረጃ ጋርዶ በአባታችን አዳምና በእናታችን ሔዋን ላይ ሥቃይ አጸናባቸው። ስመ ግብርናችሁን ጽፋችሁ ብትሰጡኝ ፍዳውን ባቀለልሁላችሁ ነበር አላቸው። እነርሱም «አዳም የዲያብሎስ ባርያ፤ ሔዋን የዲያብሎስ ገረድ» መሆናቸውን አመኑለት። ይህን በሁለት ዕብነ ሩካም ጽፎ አንዱን በዮርዳኖስ፤ አንዱን በሲኦል ጥሎታል። በዮርዳኖስ የጣለውን ጌታ ሲጠመቅ እንደ ሰውነቱ ተረግጦ፤ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ አጥፍቶላቸዋል። በሲኦል የጣለውን በዕለተ ዓርብ በአካለ ነፍስ ወርዶ ነፍሳትን ሲያወጣ አጥፍቶላቸው ወጥቷል። ቆላ.፪፥፲፫–፲፭።

## በጥምቀት ላይ ለሚነሡ ጥያቄዎች የተሰጠ መልስ

ጥያቄ ፩– በጥምቀት ‹ከኃጢአታችን እንላቀቃለን፤ የሕይወት ተሐድሶም እናገኛለን› ከተባለ አንድ ጊዜ ከተጠመቅን በኋላ ዳግም ኃጢአት ለምን እንሠራለን?

መልስ – በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን በጥምቀት አዲስ ሕይወትን እንጎናጸፋለን። የኃጢአት ሥርየትም እናገኛለን። ሮሜ.፮፥፬፤ የሐዋ.፪፥፴፰። ይህ ማለት ግን ተጠማቂው ዳግም ኃጢአትን እንዳይሠራ ጥምቀቱ የኃጢአት መከላከያ ግንብ ይሆንለታል

ማለት አይደለም። በጥምቀት ትእዛዘ እግዚአብሔርን በመጣስ ተገፈን የነበረውን የሥላሴን ልጅነት መልሰንእናገኘዋለን፤ ማለትም ከእግዚአብሔር ዳግም እንወለዳለን፣ አዲስ ሕይወት አዲስ ክብር እናገኛለን፤ በአዲስ ተፈጥሮም እንፈጠራለን። የእግዚአብሔር ምርጥ ዕቃ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን «ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደድ በተገለጠ ጊዜ እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብ በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም።» ቲቶ.፫፥፭-፯።

በጥምቀት አዲስ ሕይወት አገኘን ማለት የማንበድል፣ የማንሳሳት፣ ኃጢአትን የማንሠራ፣ ፍጹማን አእምሮ አደረገን ማለት አይደለም። በጥምቀት ከጎሰቆለው ባሕርያችን እንታደሳለን። አዳም ከስሕተቱ በፊት የነበረውን ባሕርይም እናገኛለን። አባታችን አዳም «በአርአያ እግዚአብሔር ንጹሕ ቅዱስ ሆኖ ተፈጥሮ በገነት በሚኖርበት ጊዜ በንጽሕና በቅድስና የተጌጠ ሰውነት ነበረው። ዳሩ ግን በተፈጥሮው ንጹሕ ቅዱስ ሆኖ ሳለ በምክረ ከይሲ ተታሎ ኃጢአት ሠራና ወደቀ። እግዚአብሔር አምላክ አዳምን የፈጠረው ከሙሉ ነፃ ፈቃድ ጋር ነበርና ኃጢአት ለመሥራትም ሆነ ላለመሥራት ፈቃዱ የአዳም በመሆኑ በተፈጥሮ በተሰጠው በዚህ ነፃነቱ ተጠቅሞ ኃጢአት በመሥራቱ ዛሬም እኛ በአዳምና በሔዋን ምክንያት ጎስቁሎ የነበረው ባሕርያችን ዳግም በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ታድሷል። ተቀድሷል። ደሩ ግን በኃጢአት ቀንበር ዳግም ለመያዝና ላለመያዝ ያለው የራሳችን ነፃ ፈቃድ እንደ ተጠበቀ ነው። ጥምቀት አስቀድሞ ለአዳም የተሰጠውን ነፃ ፈቃድ አይገፍም። በዓለም ላይ ያለውንም ፈተና አጠገባችን ዝር እንዳይል ከሩቅ ወጥሮ የሚይዝ ኃይል አይደለም።

በዓለም ሳለን መከራ ቢኖርብንም ታግሠን በድል አድራጊነት / መወጣት መቻል በጥምቀት ያገኘነው ጸጋ ነው። ክርስቲያን በቀን ሰባት ጊዜ ቢወድቅ ሰባት ጊዜ ይነሣልና።

ስለዚህ ጥምቀት ከቀደመው የጉስቁልና ሕይወት የምንላቀቅበትና አዲስ ሕይወትን የምንላበስበት የሰማያዊቱ መንግሥትን በር የሚከፍት ቁልፍ እንጂ ዳግመኛ ኃጢአትን እንዳናስብና እንዳንሠራ የሚያደርግ ባለመሆኑ ከተጠመቅን በኋላ በኃጢአት ብንወድቅ እንኳ በንስሐ



የመነሳት ኃይል ስለተሰጠን፣ እንደ ወደቅን እንዳንቀር በጥምቀት ያገኘው ጸጋ ይደግፈናል።

ጥያቄ ፪ – በምግባራቸው ጥሩ አይደሉም ብዬ የማስባቸው ካህን ቢያጠምቁ ተጠማቂው ከጥምቀት የሚያገኘውን ጸጋ ያስቀርበታልን?

መልስ – በመሠረቱ በጥምቀት የምናገኘው ክብርና ጸጋ ሁሉ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ እንጂ ከካህኑ አይደለም። ካህኑ የሰጭው የእግዚአብሔር መገልገያ ነው። በጥምቀት የሚገኘው ፍጹም ክብርና ጸጋ በእውነተኛውና እንከን በማይገኝበት በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተ እንጂ በሰው ልጅ (በአጥማቂው ካህን) ጥሩነትና መጥፎነት ላይ የተመሠረተ አይደለም።

አጥማቂው በሥነ ምግባሩ ብልሹ መሆን በተጠማቂው ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም። በራሱ በካህኑ ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ከማምጣቱ በስተቀር። ይህንንም በተለያዩ ምሳሌዎች መግለጥ ይቻላል።

አጥማቂው ካህን የምሥራች ቃል የሠፈረበትን ደብዳቤ ይዞ የመጣ መልእክተኛን ይመስላል። የምሥራቹ የሠፈረበትን ደብዳቤ ይዞ የሚመጣው መልእክተኛ መልከ ጥፉ ይሁን መልከ መልካም፣ ጸባየ መልካም ይሁን መጥፎ፣ ይዞት በሚመጣው መልእክት ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም።

እንዲሁም አጥማቂው ካህን በመሬት ላይ ዘርን የሚዘራ ገበሬን ይመስላል። አንድ ገበሬ ጠባዩ ጥሩ ይሁን መጥፎ በሚዘራው እህል ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም። ጥሩ ዘርን በጥሩ መሬት ላይ ከዘራ ጥሩ ምርት ይገኛል። ኃጢአተኛ ገበሬ ዘራው ጻድቅ ገበሬ በምርቱ ላይ ለውጥ አያመጣም። ዘሩ መልካም ከሆነ። በእርግጥ ካህን ለሌላው ምእመን በበጐ ሥነ ምግባር አርአያ የሚሆን እንጂ ምግባረ ቢስ ሊሆን አይገባውም።

ጥያቄ ፫ – በጌታ ቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ (ፈያታዊዘየማን) መቼ ተጠመቀ?

መልስ – ልጅነትን የምታሰጠው ጥምቀት አንድ ስትሆን በአራት ወገን ትከፈላለች። የውኃ ጥምቀት (የጌታ ጥምቀት ለእኛ አርአያ የሆነበት)፣ አንብዓ ንስሐ (የንስሐ ዕንባ)፣ ደመ ሰማዕት እና ባሕረ እሳት። እነዚህን በዝርዝር እንመልከታቸው።

ጌታ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ ለእኛ አርአያ ሆኖናል። «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» ብሎም አስተምሯል። ዮሐ.፫፥፭። ዳሩ ግን ከውኃ ጥምቀት ሳይደርሱ በመንገድ ላይ ስለ ክርስቶስ ሲመሰክሩ በአላውያን ሰይፍ ተቀልተው ያረፉ ወይም ወደ እሳት የሚወረወሩ ሰዎች ለውኃ ጥምቀት ባለመብቃታቸው የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም አይባልም። ጥምቀት ማለት ከክርስቶስ ጋር አብረን የምንሞትበትና የምንቀበርበት እንዲሁም የምንነሣበት ምሥጢር ነውና። ሮሜ.፮፥፫።

ስለዚህ ቀድሞ ኢአማንያን የነበሩ ኋላ ግን አምነው በአላውያን ፊት ስለ ጌታ አዳኝነት ሲመሰክሩ በሰማዕትነት የሚያልፉ ሰዎች ስለ ክርስቶስ ሲሉ ያፈሰሱት ደማቸው ደመ ጥምቀት ይሆንላቸዋል። ወደ እሳትም ቢጥሉአቸው እሳቱ የጥምቀት ባሕር ይሆንላቸዋል። ጌታን በሞቱ መስለውታልና ጸጋውን ይጎናጸፋሉ። የክብር ትንሣኤም ይነሣሉ። «ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን» ሮሜ.፮፥፭ ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረው በውኃ አልተጠመቁምና አይድኑም ማለት አይቻልም። ያመነ የተጠመቀ ይድናል እንዳለ ሁሉ አምነው ለውኃ ጥምቀት ሳይበቁ ጠላት ዲያብሎስ በመንገድ ላይ ሳሉ አላውያንን አሥነስቶ መሰናክል ሆኖባቸዋልና በደማቸው ይጠመቃሉ። ጌታ ለእነዚህ ሳይጠመቁ በሰማዕትነት ላለፉ እንዲህ ሲል ተናግሯል «በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ» ማቴ.፲፥፴፪።

«ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል» ማቴ.፲፮፥፳፭።

ስለዚህ ስለ ክርስቶስ ብለው በሰማዕትነት ያለፉ ሰዎች የዘላለም ሕይወትን ያገኛሉ። ቤተ ክርስቲያናችን አማናዊት ጥምቀት በእንዲህ ዓይነት መልኩም እንደምትሰጥ ታምናለች። ታስተምራለችም። እግዚአብሔር ይህን ለማድረግ የሚሳነው ነገር የለምና።

ከላይ በተዘረዘረው መሠረት በጌታ ቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ የንስሐ ዕንባውን አፍሶ ጌታን ይቅር በለኝ፣ በመጣህ ጊዜም አስበኝ ብሎታል። ጌታም እስከዚያች ቀን ድረስ በሲኦል ውስጥ ሆነው «አምላካችን



አምላካችን ምነው ተውኸን» ለሚሉት ነፍሳት ድኅነት ሲል ደሙን አፍሷል። ፭ሺህ፭፻ ዘመን በሲኦል ተግዘው ለሚኖሩ ነፍሳት የጌታ ደም ደመ ጥምቀት ሆኖላቸው ወደ ገነት ገብተዋል። ስለዚህ በጌታ ቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ ድኅነትና ለ፭ሺህ፭፻ ዘመን በእግረ አጋንንት ሲጠቀጠቁ የነበሩ ነፍሳት ድኅነት አንድ ስለሆነ የእርሱ ብቻ ልዩ ተደርጎ መነሣቱ ለምንድነው? እነዚያ የጌታ ደም ደመ ጥምቀት ሆኖላቸው ከሲኦል እንደ ወጡና ወደ ገነት እንደ ገቡ ሁሉ በጌታ ቀኝ የተሰቀለው ወንበዴም ደሙ ደመ ጥምቀት ሆኖለታል።

ጥያቄ ፬– ድኅነት ያለ ጥምቀት የለም ከተባለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ የወኅኒው ጠባቂ «ጌቶች ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» ባላቸው ጊዜ «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰዎችህም ትድናላችሁ» በማለት ፋንታ ‹ተጠመቅ› ለምን አላሉትም? የሐዋ.፲፮፥፴፩።

መልስ – ከላይ ለቀረበው ጥያቄ መልስ ለመስጠት የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስቀድሞ መጠየቅና መልስ ማግኘት ያሻል። ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ ይህን ያስተማሩት ለማን ነው? ለምንስ ይህን አሉ? «በጌታ በኢየሱስ እመን» ብለው ብቻ አቆሙን?

ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ «በጌታ እመን ትድናለህ» ያሉት ከዚህ በፊት በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ለማያምን ሰው ነው። ዛሬም ቢሆን በቤተ ክርስቲያን ገና ያላመነ ሰው «እድን ዘንድ ምን ላድርግ?» የሚል ጥያቄ ቢያቀርብ «ተጠመቅ፣ ቁረብ፣ መልካም ሥራ ሥራ» ብላ አታስተምረውም። በቅድሚያ በእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ በድንግል ማርያም ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና የባሕርይ አምላክነት እንዲያምን ታስተምረዋለች። የጥምቀቱ አስገኚና ባለቤት እርሱ ነውና።

በተማረው መሠረትም «በወልድ ዋሕድ በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነትና አዳኝነት፣ በሥላሴ አንድነትና ሦስትነት አምኛለሁ» ሲል ይጠመቃል። ተጠምቆ የቤተ ክርስቲያን አባልም ይሆናል። በጥምቀት የጸጋ ልጅነትን ያገኛል። ከዚያም የጌታን አማናዊ ሥጋውንና ደሙን ይቀበላል። ሌሎችንም የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ሕግጋት መፈጸም ይጀምራል።

እንደዚሁም ሁሉ ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስም ገና ላላመነው ሰው አስቀድሞ ስለ ጥምቀትና ስለ ቁርባን ወይም ስለ መልካም ምግባር ማስተማር አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም «ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልምና» ዕብ.፲፩፥፮። የወኅኒ ቤት ጠባቂውንም ለሚሠራው የጽድቅ ሥራ ሁሉ እምነት መሠረት ነውና ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ መጀመሪያ መሠረቱን ሲጥሉ «በጌታ እመን» አሉት። ከመሠረት በኋላ ደግሞ ጣሪያ ግድግዳ ይቀጥላል።

ስለ እምነት አስተምረው ብቻ አላቆሙም። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ባመነ ጊዜም የሚከተሉት ተፈጽመዋል።

ሀ. «ለእርሱና በቤቱም ላሉት ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ተናገሩአቸው» የሐዋ.፲፮፥፴፪። ማለትም አስተማሩአቸው። በማመናቸው ብቻ የሚድኑ ቢሆኑ ኖሮ ማስተማሩ ትርፍ ነገር በሆነ ነበር። ዳሩ ግን እምነትን የሚከተሉ ከእምነት ጋር የማይነጣጠሉ ሌሎች ተግባራት መኖራቸውን ማስተማር የግዴታ በመሆኑ ቃሉን ሰበኩላቸው። የሰበኩላቸውም ጌታ ያስተማረውን ነው። መድኃኒታችን በመዋዕለ ትምህርቱ:-

«ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ማር.፲፮፥፲፮።

«ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» ዮሐ.፫፥፭። ብሏልና።

ለ. «ያን ጊዜውንም እርሱ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር ተጠመቀ» የሐዋ.፲፮፥፴፫።

የትምህርቱ ዓላማ ወደ ጥምቀት ለማምጣት እንደ ነበር የወኅኒ ቤቱ አለቃ ቤተሰቦች መጠመቃቸው ይመሰክራል። በእምነታቸው ብቻ የሚድኑ ቢሆን ኖሮ ባልተጠመቁ ነበር። ጌታ እንዳስተማረው ሁሉ ያለ ጥምቀት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ስለማይቻል የወኅኒ ጠባቂው ከመላ ቤተሰቡ ጋር ተጠመቀ። በዚህም አምኖ ለሁና ይበቃኛል አለማለቱን፤ መጠመቁን እንረዳለን።

ጥያቄ ፳- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች በላከው ክታቡ ላይ «በውኃ መታጠብና በቃሉ አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ (ስለቤተክርስቲያን) ራሱን አሳልፎ ሰጠ» ይላል። ኤፌ.፭፥፳፮። እንዲሁም ቅዱስ ጴጥሮስ «ዳግመኛም የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም። በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር



ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።» ፩ጴጥ.፩፥፳፫። ሐዋርያው ያዕቆብም «ለፍጥረቱ የበኵራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን።» ያዕ.፩፥፲፰ በማለት በቃሉ እንደምንድን አስተምሯል። ስለዚህ የምንድነው በቃሉ እንጂ በውኃ ጥምቀት አይደለም እና ለምን እንጠመቃለን?

መልስ — የጥምቀት ትርጉም በግሪኩም ሆነ በግእዙ አንድ ነው። መንከር ወይም ውኃ ውስጥ መጥለቅ ማለት ነው። ከቃሉ ትርጉም እንኳን ስንነሳ ጥምቀት ሊከናወን የሚችለው በውኃ በመጠመቅ ነው። በውኃ ተጠምቆ ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና ለማግኘት ደግሞ አስቀድሞ ማመን ያስፈልጋል። ለማሳመን ደግሞ ማስተማር ግዴታ ነው። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ» ሮሜ.፲፥፲፬። እንዳለው የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ለሁሉም መሠረታዊና አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ቃሉ ሕይወትን የሚሰጥ ለጽድቅ የሚያበቃ መሆኑን ማንም አይክድም። ዳሩ ግን የቃል ጥምቀት (ቃሉን ሰምቶ በመንፈስ መለወጡ መታጠብ) እንጂ የውኃ ጥምቀት አያስፈልግም ማለት አይደለም። ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሶች አባባል በአንክሮ ማጤኑ አስፈላጊ ስለሆነ አንድ በአንድ በጥሞና እናስተውላቸው።

«በውኃ መታጠብና በቃሉ አንጽቶ እንዲቀድሳት...» በሚለው አነጋገር የውኃ ጥምቀት እንዳለ በግልጽ ተቀምጧል። ጥምቀት ማለት ውኃ ውስጥ ገብቶ መነከር ማለት ከሆነ በውኃ መታጠብ የሚለው የሚያመለክተው መጠመቅን ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው በውኃ ተጠምቆ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ ይነጻል፣ ይቀደሳል።

«ዳግመኛም የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም» ሲል በጥምቀት ዳግመኛ ከሥላሴ መወለዳችን ለኀልፈት ለጥፋት አለመሆኑን፣ ኀልፈት (ማለፍ)፣ መጥፋት ካለበት ባሕርይ እንዳልተወለድን፣ የዘላለም ልጅነት ከሚያሰጥ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ፣ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ መወለዳችንን ሲገልጽ ነው። ምክንያቱም ጌታ እንዳስተማረው ሁሉ «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነውና» ዮሐ.፫፥፮።

«በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ» በማለት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ብሎ ባስተማረው ትምህርት (ቃሉ) መሠረት

በጥምቀት ዳግም የተወለደ ሁሉ ለዘላለም ሕያው ሆኖ ከጌታ ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚኖር ገለጸ።

«ለፍጥረቱ የበኵራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን።» ሲል ሐዋርያው ሊያስገነዝበን የፈለገው ተከታይ ተቀዳሚ የሌለው የአብ የባሕርይ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሥልጣኑ ምንም ምን የሚያመልጥ፣ ከቃሉ የሚወጣ (የሚዛነፍ) የሌለ «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ባለው ቃል መሠረት ወዶ ፈቅዶ ወልዶናልና «ለፍጥረቱ ጀማሮች እንሆን ዘንድ ወለደን» ማለቱም መጀመሪያ ልጅነትን ያገኙ ሐዋርያት በመሆናቸው ራሱን ከወንድሞቹ ከሐዋርያት አግብቶ መናገሩ ነው። እስከ ምጽአት ድረስ ለሚነሡ ሁሉ አበው ሐዋርያት አብነት ይሆናሉና።

እንግዲህ እምነት በመስማት ነው መስማትም ከቃሉ ነው። ለሁሉም መሠረት ቃለ እግዚአብሔር ነው። በእግዚአብሔር ቃል ሁሉም ይከናወናል። ጥምቀቱ ቁርባኑ መልካም ምግባሩ ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ የሚሆን አይደለምና። «በእውነት ቃል አስቦ ወለደን» የሚለው አነጋገር ጥምቀትን የሚሽር አይደለም።

## ምሥጢረ ቁርባን

### የቁርባን ትርጉም

ቁርባን ቃሉ የሱርስትና የዓረብ ሲሆን ትርጉሙም በቁሙ መንፈሳዊ አምኃ፣ መሥዋዕት፤ መባዕ፤ ለአምላክ የሚቀርብ፣ የሚሰጥ ገንዘብ ማለት ነው።[፭]

ቃሉን በምልዓት ስንመለከተው ሰው ለአምላኩ የሚያቀርበውን ነገር ሁሉ የሚያካትት ሲሆን በዚህ ርዕሳችን የምንመለከተው ግን ስለ አማናዊው ቁርባን ወይም መሥዋዕት ስለ ምሥጢረ ቁርባን ነው። ምሥጢረ ቁርባን ማለት ካህኑ ኅብስቱን በፃሕል ወይኑን በጽዋዕ አድርጎ በጸሎተ ቅዳሴ በባረከው ጊዜ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት፣ ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት የሚሆንበትና እኛም የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት ይህንን የክርስቶስን ሥጋና ደም የምንቀበልበት ዓቢይ ምሥጢር ነው። [፮]

---

፭. ኪዳን ወልድ ክፍሌ፤ መዝገበ ቃላት፤ ገጽ ፰፻፲

፮. አባ ቄርሎስ (ሊቀጳጳሳ)፤ ፍሬሃይማኖት፤ ፲፱፻፸፯፤ ገጽ ፳፯



ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ እንካችሁ ብሎ ከመስጠቱ ቀደም ብሎ በዘመነ ብሉይ አማናዊውን መሥዋዕት ቅዱስ ቁርባንን (ምሥጢረ ቁርባን) በምሳሌ እናገኘዋለን። ብሉይ ኪዳን ለሐዲስ ኪዳን አምሳል መርገፍ ነውና።

### በብሉይ ኪዳን የምሥጢረ ቁርባን ምሳሌ

፩.‹ክህነቱ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ ለዝንተ ዓለም ይኖራል› ተብሎ የተነገረለት የሰላም ንጉሥ መልከ ጼዴቅ በዘመነ ብሉይ ከቀደምት አበው ሁሉ ለየት ብሎ በቀራንዮ ኮረብታ ላይ ከእርሱ በፊትም ሆነ ከእርሱ በኋላ ያሉት አባቶች ያቀርቡት እንደ ነበረው የደም መሥዋዕት ሳይሆን በኅብስትና በወይን ይሠዋ ነበር። አበ ብዙኃን ተብሎ የሚጠራው አብርሃም ኮሎደጎሞርንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ነገሥታት ወግቶ ሲመለስ ይኸው የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅ ኅብስትና ወይን ይዞ ተቀብሎታል። የመልከ ጼዴቅ ኅብስተ አኮቴት፣ ጽዋዐ በረከት የሥጋ ወደሙ ምሳሌ ሲሆን መልከ ጼዴቅ ደግሞ የልዑለ ባሕርይ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። ዘፍ.፲፬፥፲፰–፳። ዕብ.፭፥፮–፲። ዕብ.፯፥፩–፫ና፯።[፯]

፪. እስራኤል በምድረ ግብፅ ለ፬፻፴ ዘመን ያህል በባርነት ሲማቅቁ ከኖሩ በኋላ በልዑል እግዚአብሔር ቸርነት በነቢዩ ሙሴ መሪነት ምድረ ግብፅን ለቀው ከመውጣታቸው በፊት ከሞተ በኵር ይድኑ ዘንድ እግዚአብሔር አምላክ እንዲህ አላቸው:-

«...ይህ ወር የወሮች መጀመሪያ ይሁንላችሁ። የዓመቱም መጀመሪያ ወር ይሁናችሁ። በዚህ ወር በአሥረኛው ቀን ሰው ሁሉ ለአባቱ ቤት አንድ ጠቦት ለአንድ ቤትም አንድ ጠቦት ይውሰድ...የእናንተ ጠቦት ነውር የሌለበት የአንድ ዓመት ተባት ይሁን...በዚህም ወር እስከ አሥራ አራተኛ ቀን ድረስ ጠብቁት። የእስራኤልም ማኅበር ጉባኤ ሁሉ ሲመሽ ይረዱት። ከደሙም ወስደው በሚበሉበት ቤት ሁለቱን መቃንና ጉበኑን ይቀቡት። በእሳት የተጠበሰውን ሥጋውንና ቂጣውን እንጀራ በዚያች ሌሊት ይብሉ።

---

፯. መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት)፤ መዝገበ ሃይማኖት፤ ፲፱፻፶፱፤ ገጽ ፴፮፤ (Rev. Marcos Daud, The Orthodox Church, CHURCH SACRAMENTS, 1952, P.25)

ከመራራ ቅጠል ጋር ይበሉታል። ጥሬውን በውኃም የበሰለውን አትብሉ። ነገር ግን ከራሱ ከጭኑ ከሆድ ዕቃው ጋር በእሳት የተጠበሰውን ብሉት። ከእርሱም እስከ ጠዋት አንዳች አታስቀሩ እስከ ጠዋትም የቀረውን በእሳት አቃጥሉት።...እርሱ የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው» ዘጸ.፲፪፥፩–፳፭።

እስራኤል ከሞተ በኵር የዳኑበት ተባት በግ ምሳሌነቱ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን በላከው ክታቡ ላይ ሲያረጋግጥ «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና» ብሏል። ፩ቆሮ.፩፥፯። መጥምቀ መለኮት ዮሐንስም በዕለተ ዓርብ፣ ስለ ዓለሙ ድኅነት የተሠዋውን አማናዊ በግ ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስተዋውቅ «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» ሲል ገልጧል። ዮሐ.፩፥፳፱።

እስራኤል በጉን እንዲያርዱ የታዘዙበት ወር ኒሳን ሲሆን በእኛ ሚያዚያ መሆኑ ነው። በዚህ ወር በአሥረኛው ቀን ነውር የሌለበት ማለትም ጠጉሩ ያላረረ፣ ቀንዱ ያልከረከረ፣ ጥፍሩ ያልዘረዘረ፣ የአንድ ዓመት ጠቦት እንዲያዘጋጁና ወሩ በገባ ከአሥረኛው ቀን እስከ አሥራ አራተኛው ቀን አሥረው በአሥራ አራተኛው ቀን እንዲሠውት ታዘዋል።

የዚህ ምሳሌነቱ ነጥብ የምታክል ነውር የሌለበት ማለትም ምክንያተ ኃጢአት የሌለበት ንጹሐ ባሕርይ ጌታ በቅንዓተ አይሁድ ታሥሮ በመስቀል ላይ ራሱን ለመሠዋቱ ምሳሌ ነው። በጉ የአንድ ዓመት ተባት ለመታረድ የደረሰ እንዲሆን እንደ ታዘዘ ሁሉ ጌታም ፍጹም የሠላሳ ዓመት ጐልማሳ ሳለ ለመስቀሉ ምሳሌ ሲሆን በጉ በአሥረኛው ቀን ታሥሮ በአሥራ አራተኛው ቀን እንደ ተሠዋ ሁሉ ጌታም በአይሁድ እጅ ተይዞ እንደ ወንጀለኛ ታሥሮ በዕለተ ዓርብ ለመሥዋዕት የመቅረቡ ምሳሌ ነው።

«የቤቱ ሰዎች ቁጥርም ለጠቦቱ የማይበቃ ቢሆን እርሱና ለቤቱ የቀረበው ጎረቤቱ እንደ ነፍሶቻቸው ቁጥር አንድ ጠቦት ይውሰድ»ቁ.፬።

ይህ አገላለጽ የሚጠቁመን የእስራኤል ልጆች በጉን በሚሠውበት ጊዜ ቁጥራቸው በርከት ያለ እንዲሆን ሁለትና ሦስት ብቻ ሆነው መሠዋት እንደሌለባቸው የሚያስገነዝብ ነው። ትውፊታዊ መረጃ



እንደሚጠቁመን በጉን በሚሠውበት ጊዜ ሰባት፣ አሥር፣ አሥራ ሁለት ሁነው እንዲሠውት ታዘው እንደ ነበር ነው።

ይህም ያለ አንዳች ምክንያት የሆነ አልነበረም። ሰባት ቁጥር በዕብራውያን የፍጹምነት ምልክት ነው። ለእነርሱ በእግዚአብሔር ኃይልና ቸርነት ከበኵረ ሞት እንደሚድኑ ፍጹም እምነት ሊኖራቸው እንደሚገባ የሚጠቁም ሲሆን፣

ዛሬ ላለነው ክርስቲያኖች ደግሞ የጌታን ሥጋውና ደሙን ከኃጢአት ርቀን በንስሐ ታጥበን ፍጹማን ሆነን መቀበል እንዳለብን የሚያስገነዝበን ነው። አሥር ቁጥር ደግሞ የሙሉ ምልክት ነው። አሥራ ሁለት ሁነው እንዲሰው መታዘዛቸው ለዚያን ጊዜ በጉን የሚበሉትና ከበኲር ልጅ ሞት የሚድኑት አሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ስለ ሆኑ ሲሆን ፍጻሜው ግን በምሴተ ሐሙስ ጌታ ኅብስቱንና ወይኑን ባርኮ አማናዊ ሥጋውና ደሙ መሆኑን አስገንዝቦ የሰጣቸው ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መሆኑን የሚያመለክት ነው።

የበጉን ደም የቤታቸውን መቃንና ጎበኑን እንዲቀቡ መደረጉ ለጊዜው ደሙ ለቀሳፊው መልአክ ምልክት ሆኖት በዚያ ቤት ያሉትን እንዳይቀስፍ አልፎ እንዲሄድ ሲሆን፣

ለፍጻሜው ግን «ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው» ብሎ ጌታ እንደ ተናገረው በሥጋ ወደሙ የታተሙ ሰዎች ሞተ ነፍስ እንደማያገኛቸው በፍጻሜ ዘመንም ኑና ሐሩ በሚልበት ጊዜ ለሥጋ ወደሙ በቅተው የተገኙት ትንሣኤ ዘለክብር እንደሚነሡ የሚያስረዳ ነው።

እስራኤል የበጉን ሥጋ ጥሬውን ወይም ቅቅሉን ሳይሆን ጥብሱን እንዲበሉ መታዘዛቸው የሚያስገነዝበን ነገር አለ። ጥሬውን አትብሉ ሲል ምሳሌነቱ ነፍስ ያልተለየው መለኮት ያልተዋሐደውን የክርስቶስ ሥጋ እንደምትበሉ አድርጋችሁ አትውሰዱ የሚል ሲሆን

‹ቅቅሉን አትብሉ› የሚለው ደግሞ የጌታን ሥጋ በመቃብር ፈርሶ በስብሶ ቀረ የሚሉ አሉና እንዲህ አትበሉ ማለቱ ነው።

‹ጥብሱን ብሉ› ሲል እሳቱ በቀጥታ ከበጉ ሥጋ ጋር የተዋሐደውን እንዲበሉ የሚያስረዳ ሲሆን የዚህም ምሳሌነቱ በእሳት የተመሰለ መለኮት

... የተለየውን የጌታን ሥጋውን ደሙን እንደምትበሉ ዕወቁ፣ እመኑ ሲል ነው።

ከመራራ ቅጠል ጋር እንዲበሉ መታዘዛቸው ለጊዜው የሚበሉትን እንዲበትንላቸው ሲሆን ምሥጢራዊ ትርጓሜው ግን ሥጋ ወደሙን ጾመን በባዶ ሆዳችን፣ ፲፰ ሰዓት ከምግብ ተከልክለን ለአፋችንም ምሬት ሲሰማው መቀበል እንዳለብን የሚያመለክት መሆኑን ሊቃውንት ያመሠጥሩታል።[፬]

፫. ሌላው ምሳሌ ለእስራኤል በምድረ በዳ የወረደላቸው መናነው። የእስራኤል ልጆች ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት በሚጓዙበት ጊዜ በምድረ በዳ ምንም የሚላስ የሚቀመስ ስላላገኙ ረሃብ ጸናባቸው። በዚህ ጊዜ መሪያቸው ሙሴን አስጨነቁት። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት መና ከደመና ወርዶላቸው ያን ተመግበው ከረሃብ ድነዋል።

ለእስራኤል በምድረ በዳ ከደመና የወረደላቸው መና የጌታ ሥጋና ደም ምሳሌ ሲሆን መናው የተገኘበት ደመና ደግሞ ጌታ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ ሰው የሆነባት የድንግል ማርያም ምሳሌ ነው።

ጌታችን በመዋዕለ ትምህርቱ «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። ...እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው» በማለት መናው የሥጋውና የደሙ ምሳሌ መሆኑን አስተምሯል። ዮሐ.፮፥፵፱–፶፩።[፭]

## ምሥጢረ ቁርባን መቼ ተጀመረ?

መሥዋዕተኦሪት አልፎ ምሥዋዕተ ሐዲስ በመተካት ምሥጢረ ቁርባን የተጀመረው በምሴተ ሐሙስ ነው።[፮] ሐሙስ ምሽት በአልዓዛር ቤት ሥርዓተ ቁርባንን መሠረተ። «ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ። ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና ‹እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው› አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ ‹ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው› አለ።» ማቴ.፳፮፥፳፮–፳፱።

---

፬. መዝገበ ሃይማኖት፣ ገጽ ፴፮፣ Church Sacraments, p.25-26

፭. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ ፴፮፣ Church Sacraments, p.26

፮. ዝኒ ከማሁ ገጽ ፴፱፣ Church Sacraments p.26



## የኅብስቱና የወይኑ መለወጥ

በምሴተ ሐሙስ ልዑለ ባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስቱን፣ ወይኑን ባርኮ ቀድሶ አክብሮ ለውጦ ፍጹም ሥጋውና ደሙ አድርጐ ለደቀ መዛሙርቱ «እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋውንም አንሥቶ...ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።» በማለት በዕለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቀል የሚፈተት ሥጋውንና የሚፈስ ደሙን ሰጥቶአቸዋል። ማቴ.፳፮፥፳፮–፳፱።

ይህን መሠረት በማድረግ ዛሬም ካህናት ኅብስቱንና ወይኑን በጸሎተ ቅዳሴ አመስግነው ሲባርኩት ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኮት ይሆናል። (ኲኵሐ ሃይማኖት ገጽ ፩፻፱፣ የአሥራ አራቱ ቅዳሴ ትርጓሜ)

«ይህ ኅብስት የፈጣሪያችን የአማኑኤል ሥጋ ነው። ይህ ጽዋዕ የአማኑኤል ደም ነው» ብለው ሲያቀብሉን «የጌታ ሥጋና ደም ነው ማለት እንደ ምን ይቻላል?» ሳንል በእውነት አምነን የአምላካችንን ቃል መሠረት አድርገን እንቀበላለን። ባለቤቱ ራሱ ኅብስቱን «ሥጋዬ ነው» ወይኑንም «ደሜ ነው» ብሎ ለሐዋርያቱ አቀብሏልና።

ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አበው ይህን የጌታ ቃል መሠረት አድርገው ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለከት፣ ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት እንደሚሆን መስክረዋል። የቂሳርያ ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ባስልዮስ ውዳሴ አምላክ በተሰኘው ድርሳኑ «ጌታዬ ናፍቆቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! በዚህ በቅዱስ ቁርባን በሥጋ በደም መለኮትህ እንደ ተዋሐደው ዐውቃለሁ። ይህንንም ስላወቅሁ ከክብር ሁሉ ጋር የከበረ ሥጋህን ከሰማያዊ ክብሩ ሁሉ ጋር አከብራለሁ። በዚህ በሚታየው ኅብስት መልክ እንድቀበል አምናለሁ። ከክብር ሁሉ የከበረ ደምህን ከሰማያዊ ክብሩ ሁሉ ጋር አከብራለሁ። በዚህ በሚታየው እንድቀበል አምናለሁ። ስግደት የሚገባው ግሩም መለኮትህንም እንድቀበል በፍጹም ልብ አምናለሁ። እንዲሁም ከሆነ አንድ ቀን ፈጣሪዬን ጠባቂዬን፣ ፈራጄን፣ መድኃኒቴን እቀበላለሁ። ዳግመኛም ይህንን ቅዱስ ቁርባን በኅብስትና በወይን አካል እንዳገኘው አምናለሁ። ኅብስትና ወይን መሆን እንደሌለበትም አምናለሁ።

የዓለም ሁሉ ፈጣሪ በመንግሥተ ሰማይ ኪሩቤል ሱራፌል የሚሰግዱልህ ንጉሠ ነገሥት አንተ ተሠውረህበት እንዳለህ አውቄ አምኜ እቀበለዋለሁ።

አምላኬ ሆይ! ይህ ቃል እንደተናገርከው ነውና። የአንተ ቃል ነው እንጂ የሌላ ቃል አይደለም። ያንተ ቃል ስለ መሆኑ እናታችን ቤተ ክርስቲያን የምታምነውን ሁሉ አምናለሁ እውነተኛ ምሥጢር አይደለም ለሚለኝ ነፍሴን ለሞት እሰጥበታለሁ።» ብሏል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ትምህርቱ ይህን አስመልክቶ ሲያስተምር «ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ። ሰው ከእዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል። እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው» ብሏል። ዮሐ.፮፥፶፩። ዳሩ ግን ልባቸው በጥርጥር ግዕበል የተመታ አይሁድ ይህ የጌታ ትምህርት አልዋጥ ብሎአቸው በምጸት «ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል?» በማለት ትምህርቱን ለማስተባበል ሞከሩ። ዮሐ.፮፥፶፪።

ዛሬም ቢሆን ተረፈ አይሁድ የጌታን ቃል ለማስተባበል የማይቆፍሩት የክህደት ጉድጓድ፣ የማይፈንቅሉት የሐሰት ድንጋይ የለም። ይህ መሆኑ ግን ሊያስደንቀን አይገባም።

ሁሉን ቻይ ጌታ ዘመን በማይሽረውና በማይለወጠው ጸማናዊ ቃሉ አስቀድሞ በአጽንዖት እንዲህ ብሎ አስገንዝቦናል። «እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።» ዮሐ.፮፥፶፫።

ለዚህ ቅዱስ ቃል ተጻራሪ ሆኖ ሥጋ ወደሙ መታሰቢያ እንጂ አማናዊ (እውነተኛ የክርስቶስ ሥጋና ደም) አይደለም ብሎ የሚያስተምር የክርስቶስ ጠላት ነው።

ዘላለማዊ ሕይወትን ለማግኘትና የክርስቶስን መንግሥት ለመውረስ የጌታን ሥጋና ደም መቀበል ግዴታ መሆኑን ጌታችን እንዲህ ሲል አረጋግጦልናል። «ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና።» ዮሐ.፮፥፶፬ ና ፶፭።

ጌታችን ራሱ በቃሉ ላስተማረውና ላረጋገጠው ዐቢይ ትምህርት ጀርባውን ሰጥቶ የጌታችንን ትዕዛዝ ጥሎ «ሥጋውና ደሙን መታሰቢያ



ወይም ምሳሌ ነው፤ ለድኅነት አስፈላጊ አይደለም» የሚል ሁሉ ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት የወጣ ነው። ቀጥሩም የጌታን ትምህርት ይቃወሙ ከነበሩት ከአይሁድ እንጂ ከክርስቶሳውያን አይደለም።

«ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና። ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፣ ቆርሶም...እንካችሁ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። እንደዚሁም ከራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው። በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት። ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።» ብሏል። ፩ቆሮ.፲፩፥፳፫–፳፯።

ቅዱስ ቁርባን መታሰቢያ ወይም ምሳሌ እንጂ እውነተኛ የጌታ ሥጋና ደም አይደለም ብለው የሚክዱ ክፍሎች ለክህደታቸው አስረጅ አድርገው ለማቅረብ ከሚጠቃቅሱአቸው አንድ «ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት» የሚለው ነው። ዳሩ ግን ቃሉን በአንክሮ ለሚያጤነው ሰው ሁሉ የእነርሱን ስሕተታዊ ትምህርት የሚደግፍ ወይም የሚያንጸባርቅ አለመሆኑን ይገነዘባል። ይኸውም ስናስተውለው ሥጋውና ደሙን ስንቀበል መድኃኒታችን ለእኛ ድኅነት ሲል ከቤተልሔም ዋሻ እስከ ቀራንዮ ኮረብታ የደረሰበትን ፀዋትወ መከራ፣ ሕማሙን፣ ሞቱን፣ ትንሣኤውን፣ ዕርገቱንና ዳግም ምጽአቱን እንድናስብና እንድናስተውል ለማስረዳት ነው።

ትክክለኛ የቃሉ ትርጉም ከላይ የተገለጸው ለመሆኑ የሐዋርያውን ትምህርት በድጋሚ ብንመለከት «...በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት። ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና» በማለት ያረጋግጥልናል።

ሥጋውን ደሙን በምንቀበልበት ጊዜ ሁሉ የጌታችንን መከራውን፣ ሕማሙንና ሞቱን እንዘክራለን። ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ የሰጠንን የአምላካችንን ፍቅር በኅሊናችን ስሌዳ ተሥሎ እስከ ዕለተ ሞታችን እንዲኖር ቅዱስ ቁርባን ታላቅ ማኅተም መሆኑን ማስገንዘቡ ነው።

«ንዜኑ ሞተከ እግዚእ ወትንሣኤከ ቅድስተ፤ አቤቱ ሞትህንና ቅድስት ትንሣኤህን እንናገራለን» የምንለውም ይኸንኑ ቃል መሠረት አድርገን ነው።

በአጭር ቃል «ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት» የሚለው መከራዬን፤ ሕማሜን፤ ቤዛነቴን፤ እያሰባችሁ፤ አምናችሁ ሥጋዬንና ደሜን ተቀበሉ ማለቱ ነው።

## በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ

በቅዱስ ቁርባን የሚገኘው መንፈሳዊ ጸጋ ብዙ ነው።

ሀ. በዕለተ ዓርብ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጎልጎታ በመልዕልተ መስቀል ላይ የቆረሰውን ቅዱስ ሥጋና ያፈሰሰውን ክቡር ደም እንቀበላለን።

ለ. በመንፈሳዊ ዕውቀት የምናድግበትንና በጸጋው የምንበለጽግበትን የሕይወት ምግብ እናገኛለን። መድኃኒታችን በመዋዕለ ሥጋዌው እንዳስገነዘበን «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይ ራብም። በእኔ የሚያምን ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም...ሥጋዬ እውነተኛ መብል፤ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና» ዮሐ.፮፥፴፭ ና ፶፭።

ሐ. ሥርየተ ኃጢአትን እናገኛለን። አበው «ሰው ሆኖ የማይበድል፤ እንጨት ሆኖ የማይጤስ የለም» እንዲሉ ደካማ ባሕርያችን ወደ ስህተት ጐዳና በሚመራንና የኃጢአት ጭቃ አዳልጦን በምንወድቅበት ጊዜ በንስሐ ሳሙና ታጥበን የጌታችንን ሥጋና ደም በመቀበል ከኃጢአት እንነጻለን እንቀደሳለን። «ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው» ማቴ.፳፮፥፳፰።

መ. ጌታችንና አምላካችን በሕይወታችን ውስጥ ይኖራል። እኛም በእርሱ እንኖራለን «ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ» ብሏልና። ዮሐ.፮፥፶፮።

ሠ. ከጌታችን ጋር ያለንን ተዋሕዶ እንዲሁም ከቅዱሳን ጋር ያለንን አንድነት እናረጋግጣለን። «ኅብስቱ አንድ እንደሆነ እንዲሁም እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ አካል ነን። ሁላችንም ከአንድ ኅብስት እንቀበላለንና። ፩ቆሮ.፲፥፲፯።



ረ. ቅርንጫፍ ከግንዱ እስካልተለየ ድረስ ሕይወት እንዲኖረው ሁሉ ክርስቲያኖችም የወይን ግንድ ከሆነው ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አለመለየታችንን፤ በሕይወት መኖራችንን፤ በኃጢአት አለመሞታችንን እናረጋግጣለን። «እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም» ዮሐ.፮፥፶፫።

ሰ. የዘላለም ሕይወትን እናገኛለን «ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ» ዮሐ.፮፥፶፬።*

## የሚታይ አገልግሎት

## ለመሥዋዕት የሚሆነው ኅብስት አዘገጃጀት

ለመሥዋዕት የሚሆነው ኅብስት የሚዘጋጀው በወራቱ ከደረሰ፤ ዋግ ካልመታው፤ እንክርዳድ ከሌለበት (የተለቀመ) ንጹሕ ስንዴ ነው። ፍት.ነገ አንቀጽ ፲፫። ረስጠጅ ፫ ገጽ ፩፻፴፰

በታቦቱ ላይ የሚሠውት መሥዋዕት ዕለቱን ያዘጋጁት ሊሆን ይገባል። ከተሠዋም በኋላ ለሚቀጥለው ቀን ማደር የለበትም። ኅብስቱም ነቅዕ የሌለበት ያላረረ ያልጠቆረ መሆን ይኖርበታል። (ፍት.ነገ አን ቀጽ.፲፫ ገጽ ፩፻፴፱ ረስጠጅ ፴ ፍት.ነገ አንቀጽ ፲፫ ገጽ ፩፻፴፱ በስ ፶፰)

ኅብስተ አኰቴቱ ገና ሲሠራ ሥርዓቱ አሥራ ሦስት መስቀል ባለው ማኅተም ታትሞ ይሠራል (ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ ፶፬)

## ለመሥዋዕት የሚገባ ወይን

ወፍ ያልመጠጠው፤ አይጥ ያልቆረጠመው፤ መጀመሪያ የደረሰው ወይን ሊሆን ይገባል። ለመሥዋዕቱ የሚቀርበው ወይን በእሳት ከሚበስሉ ከጠጅ እና ከዐረቄ ወገን በማንኛውም አይሠራም (ፍት.ነገ አንቀጽ ፲፫ ገጽ ፩፻፴፰ ረስጠጅ ፫)

ወይኑንም ሲሠሩ ጥሩ መሆኑን ተመልክቶ መሥራት ይገባል። ንጹሕ ጽሩይ ካልሆነ ለመሥዋዕት አይገባም፤ ጊዜ ያለፈውን ወይን መጨመር እንደማይገባ ታዝዟል። እንዲሁም ከሦስት እጅ የበለጠ ውኃ መጨመር አይገባም። (ፍት.ነገ.አንቀጽ ፲፫ በስ ፱፻፶፭ ፩፻፪)

* The Orthodox Church Sacraments p.32

አግብኦተ ግብር (ከቤተልሔም ወደ ቤተ መቅደስ)

ዲያቆኑ በቤተልሔም ኅብስቱንና ወይኑን ለመሥዋዕት ከሠራና ከአዘጋጀ በኋላ ንፍቅ ዲያቆን ኅብስቱን በመሶበ ወርቅ በራሱ ላይ አድርጐ፤ [illegible]ን ሠራዒው ዲያቆን በጽዋዕ ይዞ ቃጭል እያቃጨለ በፊት በ[illegible] ንፍቅ ቄስ መስቀልና ማዕጠንት ይዞ እያጠነ በኋላ በኋላው ሆነው ከቤተልሔም ወደ ቤተ መቅደስ ይገባሉ። (ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ ፶፭)

ቅዳሴ አስቀድሶ ለሚያውቅ ሁሉ ይህ ክስተት እንግዳ አይደለም። ለሚያስቀድስ ምእመን የሁል ጊዜ ክንውን ነው። ምናልባት በአንዳንድ ክርስቲያኖች አእምሮ የምሥጢሩ ምንነት ግልጽ እንዲሆንላቸው የሚሹ ይኖራሉ። ኅብስቱና ወይኑ በቤተልሔም መዘጋጀቱና ከዚያ መምጣቱ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም መወለዱን ያመለክታል። ከቤተልሔም ወደ ቤተ ክርስቲያን መወሰዱ ቤተ ክርስቲያን የቀራንዮ ምሳሌ ነች። ጌታ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ዞሮ አስተምሮ በመጨረሻ በቀራንዮ ኮረብታ መሥዋዕት ሆኗልና ኅብስቱም የሚሠዋው የቀራንዮ አምሳል በሆነችው በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የቃል ኪዳኑ መገለጫ በሆነው በታቦቱ ላይ ነው።

ሌላ ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄ ደሙ በምድር ላይ እንዳይፈስ ጽዋውን ከመጠን በላይ መሙላት አይገባም። ሲያቀብሉም በጥንቃቄ መሆን አለበት። (ፍት.ነገ. አንቀጽ ፲፫ ገጽ ፩፻፵ ረስጣ ፵፩)

## ከቁርባን በፊት ሊደረግ የሚገባ

ማንኛውም ክርስቲያን የጌታን ሥጋና ደም መቀበል ሃይማኖታዊ ግዴታው ነው። ዳሩ ግን ወደ ሥጋ ወደሙ ከመቅረቡ በፊት ሊያደርገው የሚገባ ቅድመ ዝግጅት አለ። እነዚህ ቅድመ ዝግጅቶች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የሚቀድሱና የሚቆርቡ ሰዎች በጋብቻ ሥርዓት የሚኖሩ ከሆኑ ከመቀደሳቸውና ከመቁረባቸው በፊት ሦስት ቀን፣ ከቁርባን በኋላ ሁለት ቀን ከሩካቤ መከልከል ይገባቸዋል።

ለ. ሥጋ ወደሙን የሚቀበል ሰው አስቀድሞ ራሱን ለካህን ማስመርመር ይገባዋል። ይህም ማለት ንስሐ ገብቶ ከኃጢአቱ ነጽቶ



በደሉን አስፍቶ መሆን ይኖርበታል። ቅዱሳን አባቶች እንዳስተማሩን ከክርስቲያን ወገን ማንም ሰው የክርስቶስን ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ትንሣኤ ዘለሕይወትን ሊወርስ ቢወድ ልቡን ከቂም ከበቀል፣ ሰውነቱን ከበደል ንጹሕ ማድረግ አለበት። ይህም ማለት ሰው ስለሚያውቀው ኃጢአት ተናዝዞ ስለማያውቀው ይቅር በለኝ እያለ በንጹሕ ልቡና ይቁረብ ማለት ነው። በንስሐ ከኃጢአት ሳይነጻ በድፍረት ቢቀበል ግን የጌታ ሥጋ እንደሆነ አላወቀምና እንደ ምድራዊ ምግብም አቃልሎታልና በኃጢአት ሳለ ያለ ኃፍረት ሥጋውን ደሙን በመቀበሉ ሥላሴ ይፈርዱበታል። ፩ቆሮ.፲፩፥፳፫ ና ፳፱።

ሐ. ሥጋ ወደሙ ለመቀበል አሥራ ስምንት ሰዓት ያህል ከእህል ከውኃ ተከልክሎ መጾም ይገባል።

መ. ካህን በሚቀድስበት ቀን ዕንቅፋት ቢያገኘው ማለት ነስር፣ ትውኪያ፣ ብስና፣ ማንኛውም የአካል መድማት፣ መቁሰል፣ ወደ አፍ የሚገባ ተሐዋሲ ይህን የመሰለ ሁሉ ቢያጋጥመው በዚያው ዕለት መቀደስ እና መቁረብ አይችልም።

ከቁርባን በኋላ ከአለመጠንቀቅ የተነሣ እንዲህ ያለ ነገር ቢያጋጥመው ንስሐ ሊሰጠው ይገባል። ንስሐውን ሳይፈጽም እንደገና መቁረብ አይችልም። ይህም ለካህን ብቻ ሳይሆን ምእመናንንም ሁሉ የሚመለከት ነው። (ማስረጃ ያዕቆብ ዘእልበረዳኢ) ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን፣ ገጽ ፶–፶፩)

## ለመቁረብ የሚያበቃና የማያበቃ ሁኔታ

ሀ. ቅዳሴ ሲጀምር ያልነበረ ሰው አይቁረብም፣ ቅዳሴ ሲጀመር ያልነበረ ካህንም እንደዚሁ ሥጋ ወደሙ ሊቀበል ሊያቀብል አልተፈቀደለትም። ፍት.ነገ.አንቀጽ ፲፪ ገጽ ፩፻፴፯ በስ ፶፯

ለ. ከምእመናን በስተቀር (የሚቀበሉት የጌታን አማናዊ ሥጋውንና ደሙን መሆኑን ከሚያምኑ በስተቀር) ያላመኑ ሰዎች ሥጋ ወደሙ ሊቀበሉ አይገባም። እንዳይቀበሉ መጠበቅና መቆጣጠር ያስፈልጋል። (ፍት.ነገ. አንቀጽ ፲፫ ገጽ ፩፻፵ ረስጠብ ፵፬)

ሐ. በንስሐ የተለየ ሰው የንስሐ ጊዜውን ሳይፈጽም ለሞት የሚያበቃ ደዌ ቢታመም ሥጋ ወደሙ ከመቀበል አይከለከልም። ሥጋውን ደሙን

ተቀብሎ ከዳነም ከምእመናን ጋር በጸሎት ይሳተፋል። በቀኖና ወደ ተለዩ ሰዎች አይመለስም። (ፍት.ነገ.አንቀጽ ፲፫ ገጽ ፩፻፴፱ ዕንቀራ ፲፩)

መ. የሚጥል በሽታ ያለበት፣ ጋኔን ያደረበት (ሰውን የማይሳደብ ከጣለው በኋላ ዐረፋ የማያስደፍቀው ከሆነ) ሥጋ ወደሙ ከመቀበል አይከለከልም። ሊቀበል ይችላል። (ፍት.ነገ.አንቀጽ ፲፫ ጢሞ ገጽ ፩፻፴፱)

## የአቆራረብ ሥርዓት

ሥጋውን ቄሱ በእጁ ሲያቀብል ደሙን ንፍቅ ቄሱ በዕርፈ መስቀል ለካህናት፣ እንዲሁም ዲያቆኑ ለምእመናን በዕርፈ መስቀል ይሰጣል እንጂ ንፍቅ ቄስና ዲያቆን ሥጋውን ደሙን በእጃቸው አይነኩም።

ያቆራረቡ ተራ እንደሚከተለው ይሆናል።

፩. ሊቀ ጳጳሳት

፪. ጳጳሳት

፫. ኤጲስ ቆጶሳት

፬. ቆሞሳት

፭. ቀሳውስት

፮. ዲያቆናት

፯. ንፍቀ ዲያቆናት በየተራቸው ይቆርባሉ።

ከእነርሱም ቀጥሎ ሁሉም በየማዕረጉ ተራ ይቆርባል። ከካህናት ቀጥሎ በዕለቱ ክርስትና የተነሡ ይቀበላሉ። ከዚያም ሕፃናት፣ ቀጥሎ ደናግል፣ ከዚያም ሕዝባውያን ምእመናን ሥርዓተ ቅዳሴው እንደሚያዝዘው በየማዕረጋቸው ይቆርባሉ።

ቁርባን ተቀብሎ ማየመቁረር ይሰጣል። ይኸውም የቅዳሴ ጸበል በመ ባል የሚታወቀው ነው። (ፍት.ነገ.አንቀጽ ፲፫ ገጽ ፪፻፵፪ እርስጣ ፳፩)

## ከቁርባን በኋላ የሚደረግ ጥንቃቄ

ሀ. ከቆረቡ በኋላ በዚያው ዕለት ወደ ፍርድ ቤት መሄድና መሟገት ክልክል ነው። (ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ገጽ ፳፪)

ለ. በቆረቡበት ቀን ከሚስት ወይም ከባል መገናኘት፣ አብዝቶ መብላት መጠጣት፣ ጥፍር መቆረጥ፣ ፀጉር መላጨት፣ በውኃ መታጠብ፣ ከልብስ መራቆት ክልል ነው። (ሥርዓተ ቅዳሴ ፩፻፳፮)



## የሚቆርቡ እነማን ናቸው?

በማዕከለ ምድረ በቀራንዮ ኮረብታ በመልዕልተ መስቀል የተሰቀለው የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ትምህርቱ በቀራንዮ የቆረሰው ሥጋና ያፈሰሰው ደም ለሚያምንበት ሁሉ የተሰጠ ዘላለማዊ ምግብ መሆኑን አስተምሯል። መላው የሰው ዘር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና የባሕርይ አምላክነት ካመነ ይቀበል ዘንድ ውዴታው ሳይሆን መንፈሳዊ ግዴታው ነው። ማንም ሰው መንግሥተ እግዚአብሔርን ይወርስ ዘንድ መጠመቅ ግዴታው እንደሆነ ሁሉ ሥጋ ወደሙን መቀበልም ለድኅነቱ አስፈላጊና ሃይማኖታዊ ግዴታው ነው።

በ፵ ቀንና በ፹ ቀን ሀብተወልድና ስመ ክርስትና ካገኙት ሕፃናት አንሥቶ እርጅና ከአልጋ ተጣብቀው እንዲኖሩ እስካደረጋቸው አረጋውያን ድረስ ሥጋ ወደሙን ይቀበሉ ዘንድ ቤተክርስቲያን የጥሪ ደውሏን ዘወትር ታስተጋባለች።

የቤተ ክርስቲያንን ቀኖና የማያውቁ ምናልባትም ራሳቸውን የሰየሙ አንዳንድ ካህናት ተብዩዎች «ሥጋ ወደሙን ሊቀበሉ የሚገባቸው ሕፃናት ወይንም ያገቡ ከዚያም በተረፈ መነኮሳት ብቻ እንጂ የሕይወታቸውን አቅጣጫ ለመወሰን ገና በዝግጅት ላይ ያሉና በንጽሕና ያልተጠበቁ ሰዎች ቢኖሩ በደል እንዳይሆንባቸው ሥጋ ወደሙን ከመቀበል እንዲቆጠቡ ያስፈልጋል» ይላሉ።

ነገር ግን ማንም ሰው (ምእመን) ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ሊያደርገው የሚገባውን ቅድመ ሁኔታ ካጠናቀቀ ለመቀበል የሚያግደው ምንም ነገር የለም። ሥጋ ወደሙን እንዳይቀበሉ የሚከለክሉት ያላመኑ ወይም አምነው ተጠምቀው ራሳቸውን በሕገ ቤተ ክርስቲያን ያላስጠበቁ ናቸው። እነዚህም ሥጋ ወደሙ አማናዊ የጌታ ሥጋና ደም መሆኑን የሚጠራጠሩና ትዕቢትን እንደ ሸማ ተጎናጽፈው ንስሐን የናቁ ሰዎች ናቸው።

ከዚህ ውጭ ግን ሕፃን ሆነ ጉልማሳ፣ ያገባም ሆነ ያላገባ ሥጋ ወደሙን ይቀበል ዘንድ መፈቀድም ብቻ ሳይሆን ግዴታውም ነው።

# ምሥጢረ ሜሮን

## ሜሮን ምንድን ነው?

ሜሮን:- ቃሉ የግሪክ ሲሆን፣ ትርጉሙም ቅዱስ ቅብዐት፣ የተባረከ ሽቶ ማለት ነው። ልዩ ልዩ ሽቱነት ካላቸው ዕፀዋት ተቀምሞ ነጥሮም የሚወጣ ቅባት ነው። መደበኛው ግን በለሳን የተባለው የሽቱ እንጨት ነው።[፭]

ይህ በለሳን የተባለው የሽቱ እንጨት በይሁዳና በገሊላ ይልቁንም በኢያሪኮ የሚበቅል ሽታው ከሽቱ እንጨቶች ሁሉ የሚበልጥ ነው።[፮]

ሜሮን ከላይ በተገለጸው መሠረት ተቀምሞ ነጥሮ ከወጣ በኋላ በፓትርያርክና በሊቃነ ጳጳሳት ልዩ ጸሎት ይባረካል ይከብራል። ከዚህ በኋላ ከጥምቀት ቀጥሎ ለአዲስ አማኝ መንፈስ ቅዱስን ለሚቀበል ማረጋገጫ ማኅተም ሆኖ የሚሰጥ ምሥጢር ይሆናል።[፯]

ጥምቀቱን ፍጹም ለማድረግ ይህ ምሥጢር ወዲያው ከጥምቀቱ ቀጥሎ መፈጸም ይኖርበታል። ያለዚህ ምሥጢር ጥምቀት አይጸናም።

## አመሠራረቱ

### በዘመነ ብሉይ

ቅብዐ ሜሮን በአዲስ ኪዳን ኃይል አግኝቶ በጥምቀት ከእግዚአብሔር ዳግመኛ ለተወለዱ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ ማሳደሪያ የጥምቀቱ ማጽኛ ከመሆኑ በፊት በብሉይ ኪዳንም ለመንፈሳዊ አገልግሎት ይውል ነበር።

አባታችን ያዕቆብ ከወንድሙ ከኤሳው ተጣልቶ ከአጎቱ ከላባ ዘንድ ለመኖር ወደ ሶርያ ሲሄድ መሽቶበትና በመንገድ ላይ ድንጋይ ተንተርሶ ተኛ። ተኝቶ ሳለ ከምድር እስከ ሰማይ የተዘረጋ መሰላል ተተክሎ መላእክት ሲወጡበት ሲወርዱበት፣ በላዩ ላይ ዙፋን ተዘርግቶ ንጉሥ ተቀምጦበት ያያል። ሲነጋ «ይህች ቦታ የሰማይ ደጅ ናት። እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ቤት ይሠራል።» ብሎ ተንተርሶት ያደረውን ድንጊያ

፭. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ ፻፲፰፤ ትምህርተ ክርስትና ፪ኛ መጽሐፍ ገጽ ፩፻፭

፮. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ ፪፻፷፬

፯. ትምህርተ ክርስትና ፪ኛ መጽሐፍ



አንስቶ ሐውልት አድርጎ አቆመው። በላዩም ዘይትን አፈሰሰበት። ዘፍ.፳፰፥፲-፳፪።

ለዚህም ነው ዛሬ አንድ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ ካለቀ በኋላ በጳጳሳት አማካይነት በቅብዐ ሜሮን የሚከብረው። መሠረቱም የመጀመሪያውን ቤተ እግዚአብሔር የሰራው ያዕቆብ ነው።

ያዕቆብ የጳጳሳት፣ ዘይት የሜሮን፣ ድንጋዩ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ነው። በሌላም በኩል ያዕቆብ የካህናት፣ ድንጊያው የአሕዛብ፣ ዘይት የምሥጢረ ሜሮን ምሳሌ ነው።

ያዕቆብ:- እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ፈጥሮ በልጅነት አክብሮ ነቢይ ካህን ንጉሥ አድርጎ ስለሾመው በአሪት በወንጌል ሥርዐተ ክህነት እስኪወሰን ድረስ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ የነበሩ አበው በበረከተ አበው ከእግዚአብሔር እየተሾሙ ትንቢትን ክህነትን መንግሥትን ከቅዱስ መንፈሱ እየተቀበሉ በነቢይነታቸው ያለፈውን የሚመጣውን ሲገልጡ ሲያስተምሩ፣ በካህንነታቸው መሥዋዕት ሲያቀርቡ ኖረዋል። አባታችን ያዕቆብም የዚህ በረከት ተካፋይ በመሆኑ ክህነትን ከእግዚአብሔር አምላክ ገንዘብ ማድረጉን ማስተዋል ይገባል። ለዚህም ነው ለዛሬዎቹ ለአዲስ ኪዳን ካህናት ምሳሌ የሆነው።

ድንጊያው – ያዕቆብ ሐውልት አድርጎ ያቆመው ድንጋይ ገና ባልተጠመቁ ባላመኑ አሕዛብ መመሰሉም ከጌታ በተገኘው ትምህርት መሠረት ነው። በዘመነ ስብከቱ በትዕቢት ታጅለው የአብርሃም ልጆች ነን እያሉ ለሚመፃደቁት አይሁድ «አብርሃም አ ት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ። ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጅ ሊያስነሳለት እግዚአብሔር ይችላል» ብሏል። ማቴ.፫፥፱። ድንጋይ ያላቸው ያላመኑት አሕዛብን ነው።

ዘይቱ:- የምሥጢረ ሜሮን ምሳሌ ነው። በታውን ያዕቆብ ዘይት አፍስሶ እንዳከበረው በቅብዐ ሜሮንም ጸጋ እግዚአብሔር ያድራል በልጅነት ጸጋም ተጠማቂው ይከብራል።*

* መለከት መጽሔት ፫ኛ ዓመት ቁጥር ፪ ገጽ ፲፫ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ገጽ ፩፻፲፯

የዚህን ቅዱስ ዘይት (ቅብዐት) አሠራርና አጠቃቀም ለሊቀ ነብያት ሙሴ ያስተማረው እግዚአብሔር ነው። «በቀማሚም ብልሃት እንደተሠራ ቅመም፣ የተቀደሰ የቅብዐት ዘይት ታደርገዋለህ፤ የተቀደሰ የቅብዐት ዘይት ይሆናል። የመገናኛውንም ድንኳን፣ የምስክሩንም ታቦት፣ ገበታውንም ዕቃውንም ሁሉ፣ መቅረዙንም የዕጣን መሠዊያውንም፣ ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆነውንም መሠዊያና ዕቃውንም ሁሉ የመታጠቢያውን ሳንና መቀመጫውንም ትቀባበታለህ። ሁሉንም ትቀድሳቸዋለህ። ቅድስተ ቅዱሳንም ይሆናሉ። የሚነካቸውም ሁሉ ይቀደሳል» ዘጸ.፴፥፳፪–፳፱።

በዚህ ቅዱስ ቅብዐት ተቀብተው የከበሩትን ንዋየ ቅድሳት የሚነካ ሁሉ ክብር ተላልፎለት እንደሚቀደስ ተገልጾአል።

በክህነት እንዲያገለግሉ አሮንና ልጆቹም ለእግዚአብሔር የተቀደሱት በዚህ ቅዱስ ቅብዐት ነው። «በክህነትም ያገለግሉኝ ዘንድ አሮንንና ልጆቹን ቀባቸው፣ ቀድሳቸውም።» ዘጸ.፴፥፴።

ይህ ሥርዓት ቀጣይነት ያለውና ለትውልድ የሚተላለፍም መሆኑንም «ይህ ለልጅ ልጃችሁ የተቀደሰ የቅብዐት ዘይት ይሁንልኝ» በማለት አስገንዝቧል። ዘጸ.፴፥፴፩።

ይህ ቅብዐት እንደ ማንኛውም ዓይነት ተራ ቅብዐት እለመሆኑንና ማንም ሰው ሊሠራውና ሊጠቀምበትም የማይገባ መሆኑንም ሲያስረዳ «በሰው ሥጋ ላይ አይፍሰስ። እንደ እርሱም የተሠራ ሌላ ቅብዐት አታድርጉ፤ ቅዱስ ነው። ለእናንተም ቅዱስ (የተለየ) ይሁን። እንደ እርሱ ያለውን የሚያደርግ ሰው፣ በሌላም ሰው ላይ የሚያፈስሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ» ብሏል። ዘጸ.፴፥፴፪–፴፫።

ነገር ግን ከቤተ አሮን የተወለደ በክህነት ያገለግል ዘንድ ቅዱሱን ቅባት ተቀብቶ ክህነትን ገንዘብ ያደርግ፣ ከቤተ ዳዊት የተወለደ ወንድ ደግሞ ቅዱሱን ቅብዐት ተቀብቶ መንግሥትን ገንዘብ ያደርግ ነበር።

## በዘመነ ሐዲስ

ብሉይ ኪዳን ለሐዲስ ኪዳን ጥላ በመሆኑ በብሉይ ኪዳን በምሳሌነት የተገለጡት በሐዲስ ኪዳን አማናዊ ሆነው እናገኛቸዋለን። በዘመነ ብሉይ የነበሩ አበው በቅዱስ ቅብዐት በረከተ እግዚአብሔርን ይቀበሉ እንደ



ነበር በዘመነ ሐዲስም በቅዱስ ቅብዐት ተቀብተው ምእመናን ጸጋ እግዚአብሔርን ይጎናጸፋሉ።

በዘመነ ኦሪት በመጠኑ ይሰጥ የነበረው የእግዚአብሔር ጸጋ በዘመነ ሐዲስ ግን ዓመቱ የምኅረት ዓመት በመሆኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በምልዐትና በስፋት የወረደበት ነው።

የጸጋ ሁሉ ምንጭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ «እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ። እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» በማለት ተስፋ ሰጥቷአቸው ነበርና። ሉቃ.፳፬፥፵፱። በዕለተ ጰራቅሊጦስ በሰጣቸው ተስፋ መሠረት የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በእነርሱ ላይ ወርዷአል።

በሃምሳኛው ቀን በጽርሐ ጽዮን ላሉ የወረደላቸውን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እነርሱ ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምኖ ለመጣው እጅን በመጫን ያሳድሩበት ነበር።

- «ይህንንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ። ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው» የሐዋ.፲፱፥፭–፮።
- «በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው። እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው። በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጂ ከእነርሱ በአንዱ ላይ ስንኳ መንፈስ ቅዱስ ገና አልወረደም ነበር። በዚያን ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ» የሐዋ.፰፥፲፬–፲፯።

በጥንተ ስብከት ምእመናን ገና ባልበዙበት ወቅት ሐዋርያት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን በምእመናን ላይ ያሳድሩ የነበሩት በአንብሮተ እድ (እጅን በመጫን) ነበር። ዳሩ ግን የምእመናን ቁጥር ዕለት በዕለት እየጨመረና እጅን በመጫን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ማሳደር አድካሚና ሁሉንም ለማዳረስ የማይቻል ሆኖ በመገኘቱ በአንብሮተ እድ ፋንታ በቅብዐ ሜሮን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ማሳደር አማራጭ የሌለው ሆኖ ተገኘ።

ስለዚህ ሐዋርያት፣ ከሐዋርያት በኋላ የተነሱ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ካጣመቁ በኋላ ሜሮን በመቀባት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ማሳደር ጀመሩ።

በሜሮን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ማሳደር በሐዋርያት ጊዜ እንደተጀመረ ሐዋርያው ዮሐንስ በመልእክቱ የገለጸው ማስረጃ ያስገነዝበናል። «እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፣ ሁሉንም ታውቃላችሁ» ፩ዮሐ.፪፥፳።

በሜሮን አማካይነት የሚሰጠውን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ማመልከቱ ነው። መንፈስ ቅዱስ ዕውቀትን የሚገልጽ መንፈስ ነውና። ስለዚህ እጅን በመጫን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ማሳደር በተቀደሰ ቅባት (በሜሮን) ተተክቶ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ሲሠራበት የኖረ ሥርዓት ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በቅብዐ ሜሮን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ ሲያስተምር «በክርስቶስም ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፣ ደግሞም ያተመን የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው» ብሏል። ፪ቆሮ.፩፥፳፩። ለኤፌሶን ክርስቲያኖች ሲጽፍላቸውም «ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሳን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ» ብሏቸዋል። ኤፌ.፬፥፴።

ሜሮን ማኅተመ መንፈስ ቅዱስ ነው።

## የሜሮን ጥቅም

ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ ሜሮን ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ለማስገኘት ከመንፈስ ቅዱስ ለመወለድ ማረጋገጫ ማኅተመ መንፈስ ቅዱስ ነው። ያለ ሜሮን ጥምቀት አይጸናም። ለዚህም ማስረጃ የሚሆኑን የሰማርያ ሰዎች ናቸው። በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠመቁ እንጂ በእነርሱ በአንዳቸውም ላይ መንፈስ ቅዱስ አልወረደላቸውም ነበር። ዳሩ ግን ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ እጃቸውን ጭነው በጸለዩላቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደላቸው። የሐዋ.፰፥፲፬–፲፯።

እጅን በመጫን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ማሳደር በቅብዐ ሜሮን የተተካ በመሆኑ ያለ ሜሮን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በተጠማቂው ላይ አያድርም። ቅብዓ ሜሮን በጥምቀተ ክርስትና ጊዜ የሚደረግ ሥርዓት እንጂ



ከጥምቀት በኋላ ብዙ ዘመን ተቆይቶ የሚፈጸም አይደለም። ይህንንም በመጽሐፍ ቅዱስ አስረጅነት ማረጋገጥ ይቻላል።

- በበዓለ ሃምሣ በሐዋርያት ላይ የወረደውን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ያጤኑና ኋላም በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ልባቸው የተነካው አይሁድ «...ምን እናድርግ?» ሲሉ ጠየቁ። ቅዱስ ጴጥሮስም «ንስሐ ግቡ፣ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ» አላቸው። የሐዋ.፪፥፴፯–፴፰።

የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የሚቀበሉት ወዲያው እንደተጠመቁ እንደሆነ ማረጋገጡን ልብ ይሏል። ሜሮንም ማኅተመ መንፈስ ቅዱስ ነው።

- «በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ። ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው» የሐዋ.፲፱፥፲፭።

ሜሮን እጅ መጫንን የተካ ሥርዓት በመሆኑ ዛሬም ካህናት እንዳጠመቁ ወዲያው ሜሮን መቀባት እንደሚኖርባቸው ከቅዱስ ጳውሎስ እንረዳለን። ተጠማቂው ሕፃን ሆነ ትልቅ መንፈስ ቅዱስ ለሁሉም አስፈላጊ ነው።

ለመንፈሳዊ እድገት ሆነ ለዘላለማዊ ድኅነት መንፈስ ቅዱስ ያስፈልገናል። እስከተሻለ ድረስ ቅብዐ ሜሮን እስኪያድጉ ማገናዘብ እስኪችሉ ተብሎ መጠበቅ የለበትም። በአንዳንድ እምነቶች ዘንድ ሕፃናት እስከ ፲፪ና ከዚያም በላይ ለሆኑ ዓመታት እንዲቆዩ ይደረጋል ይህ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም።*

## የሜሮን አቀባብ

ሜሮን በጥምቀተ ክርስትና ጊዜ የሚደረግ ሥርዓት ሲሆን አቀባቡም እንደሚከተለው ነው።

- ዲያቆኑ ተጠማቂው ትልቅ ከሆነ ራሱን ዝቅ አድርጎ (በአትሕቶ ርእስ) በእግዚአብሔር ፊት እንዲቆም ያዝዛል።
- ካህኑ ሜሮኑን ይዞ በተጠማቂው ላይ ይጸልያል።

* ትምህርተ ክርስትና ፪ኛ መጽሐፍ ገጽ ፩፪፪

* ካህኑ ሜሮኑን በትእምርተ መስቀል አምሳል እያመሳቀለ መጀመሪያ ግራና ቀኝ ግንባሩ ላይ ይቀባል። ሁለት ቦታ ማለት ነው። ግንባሩን ሲቀባ በፊቱ ላይ እፍ ይልበታል።

ቀጥሎም «ቅብዐ ቅዱስ ዕቀብዐከ ለሱታፌ ሕይወት ዘለዓለም» እያለ ሁለቱን የአፍንጫውን በር፣ ሁለቱን ከናፍር፣ ሁለቱን ጆሮዎቹን፣ ሁለቱን ዓይኖቹን፣ ደረቱንና ልቡን፣ ከመሐል ራስ እስከ ወገብ ያለውን፣ መሐል ጀርባውንና እንብርቱን ይቀበል።

ከዚያም «ዕቀብዐከ ለአምላክ መሢሕ በማኅተሙ ዘኢይትፌታሕ። አሜን።

እያለ የቀኝ እጁንና የግራ እጁን፣ የእጆቹን መገናኛዎች፣ የቀኝ ትከሻውንና የግራ ትከሻውን፣ ማጅራቱን፣ አንገቱን፣ የቀኝና የግራ ክርኑን፣ የሁለት እጅ መዳፍ የውጭ ሁለት የውስጥ ሁለት ይቀባል።

እንደዚሁ «እቀብዐከ ቅብዐተ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ» እያለ

የእግር መገናኛዎችን (ዳሌ ወይም ሙላ)፣ የሁለት እግሩን ጉልበት፣ የሁለት እግሩን ጣቶች የውጭው ሁለት የውስጡን ሁለት ይቀባል።

በአጠቃላይ ሠላሳ ስድስት ሕዋሳቱን ቀብቶ ከፈጸመ በኋላ በተጠማቂው ላይ እጁን ጭኖ «ቡሩክ ኩን በበረከተ መላእክት ሰማያውያን» እያለ ይባርከዋል። ከዚያ በኋላ ተጠማቂው ነጭ ልብስ ይለብሳል። በራሱ ላይ አክሊል ይቀዳጃል።*

## የሚታይ አገልግሎት– የማይታይ ጸጋ

ምሥጢረ ሜሮን የሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ አለው። የሚታይ አገልግሎት የሚባለው ካህኑ ከላይ እንደተገለጸው ሠላሳ ስድስቱን ሕዋሳት ሲቀባ መታየቱ ሲሆን የማይታይ ጸጋ መባሉ ደግሞ በዚህ በሚታይ ቅብዕ የማይታይ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ማደሩ ነው።

ሜሮን መቀባት የሚችሉት ካህናት ብቻ ናቸው። በዘመን ብሉይም ሌላው ተራው ምእመን እንዳይጠቀምበት እግዚአብሔር ሕግ መሠራቱን ቀደም ተብሎ ተገልጹአል። ዘጸ.፴፥፴፪። እግዚአብሔር የመረጣቸው ነቢያትና ካህናት ግን ሀብተ ክህነትና ሀብተ መንግሥትን ለማሳደር ይቀቡ ነበር። ዳሩ ግን ይህ አገልግሎት በእነርሱ ይፈጸም እንጂ ጸጋውን

* ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ ፺፪–፺፬



በተቀባው ሰው ላይ ያሳድር የነበረው እግዚአብሔር ነው። ነቢዩ ሳሙኤል የዘይቱን ዕቃ በሳዖል ከራስ ላይ ካፈሰሰው በኋላ «በርስቱ ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶሃል» ማለቱ በእርሱ አማካይነት ሳዖልን ለእስራኤል ንጉሥ ይሆን ዘንድ የመረጠው እግዚአብሔር መሆኑን ማረጋገጡ ነው። ፩ሳሙ.፲፥፩።

ሳዖል ባሳዘነው ጊዜ በእርሱ ምትክ ዳዊትን ሊያነግሰው ሲፈልግም «ይህ ነውና ተነስተህ ቀባው» ነበር ያለው። ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ ወስዶ በወንድሞቹ መካከል ዳዊትን ቀባው። የሚታየው አገልግሎት የተፈጸመው በሳሙኤል ነው። የማይታየው ጸጋ እግዚአብሔር ይህን ምክንያት አድርጎ በዳዊት ላይ አደረበት። ፩ሳሙ.፲፮፥፲፪:፲፫።

ስለዚህ ሜሮን በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ የሚገኝበት ምሥጢር ነው።

## ምሥጢረ ቀንዲል

«ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያን ቀሳውስትን ወደ እርሱ ይጥራ። በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል። ጌታም ያስነሳዋል። ኃጢአትም ሠርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል» ያዕ.፭፥፲፬–፲፭።

ሐዋርያው ያዕቆብ ያስተማረው ይህ ሥርዓት በቤተ ክርስቲያን ቀንዲል በመባል ይታወቃል። በካህናት ጸሎትና ቡራኬ አንድ ሕመምተኛ ሰው በተቀደሰው ዘይት በመቀባት ከበሽታው የሚፈወስበትና ከኃጢአትም የሚነፃበት አገልግሎት ነው።

የዚህ ሥርዓት መስራች ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሆኑ ይህ ማስረጃ ያስርዳናል «አሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ ጠርቶ ሁለት ሁለቱንም ይልካቸው ጀመር፣ በርኩሳን መናፍስትም ላይ ሥልጣን ሰጣቸው» ማር.፮፥፯–፰።

ይህ ታዲያ መቼ ዘይት ቀብታችሁ አድኑ ይላል? የሚል ቢኖር የተላኩት ደቀ መዛሙርት ያደረጉት ከዚያው ዝቅ ብሎ ተጽፏአልና እንመልከተው። «ወጥተውም ንስሐ እንዲገቡ ሰበኩ፣ ብዙ አጋንንትንም አወጡ፣ ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሱአቸው» ማር.፮፥፲፫።

ደቀ መዛሙርቱ ዘይት እየቀቡ መፈወስን ከማን ተማሩት? ከጌታ ካላገኙት በስተቀር። ለዚህም ነው የምሥጢረ ቀንዲል መስራች ጌታ ነው ያልነው።

ቀንዲልም ሆነ ሜሮን ሁለቱም የተቀደሱ ቅብዐቶች ናቸው በሁለቱም በኩል ያለው ሥርዓት የሚፈጸመው በመቀባት ነው። ታዲያ ሁለቱን እንዴት መለየት ይቻላል?

## የቀንዲልና የሜሮን ልዩነት

ሜሮን:- የሚቀመመው (የሚወጣው) ከተለያዩ ሽቶንት ካላቸው ዕፅዋት ነው። መደበኛው ግን በለሳን ነው።

- በፓትርያርክና በሊቃነ ጳጳሳት ጸሎትና ቡራኬ የሚከብር ቅብዕ ነው።
- ጥምቀትን የሚያጸና፣ ማኅተመ መንፈስ ቅዱስ ነው።
- አዳዲስ ንዋየ ቅድሳት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ የሚከብሩበት የሚባረኩበት ነው።
- አዲስ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃው ተሰርቶ ሲያልቅ የሚከብርበት ነው።
- የማይደገም ምሥጢር ነው።

ቀንዲል – ቅብዐ ቅዱስ እየተባለ የሚጠራ ከንፁሕ የወይራ ዘይት የሚወጣ ነው።

- በየጊዜው ለታመሙ ምእመናን የሚደረግ አገልግሎት በመሆኑ የሚደገም ሥርዓት ነው።
- ለጤነኞች ሳይሆን ለበሽተኞች ብቻ የሚደረግ ሥርዓት ነው።

## የቀንዲል አፈጻጸም

- ይህ ቅብዐት በብልቃጥ ወይንም ቀርነ ቅብዕ ሆኖ ከመንበር ይቀመጣል።
- በሽተኛው ምእመን ካህኑን በጠራ ጊዜ ካህኑ መጽሐፈ ቀንዲል ደግሞ የበሽተኛውን አካል በመስቀል ምልክት ይቀባል።

የሚቀቡት የአካል ክፍሎች–ግንባሩን ከሁለት ቦታ፣ ፊቱን ከሁለት ቦታ፣ አገጩን፣ ቀኝና ግራ እጁን፣ በውስጥም በውጭም፣ ሁለት እግሩን፣ ቢቻል ታላላቅ ሕዋሳቱን ሁሉ ያለዚያም ለጊዜው የሚያመው አካሉ ላይ ይቀባዋል።*

---

* ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ ፩፻፺፪



# ምሥጢረ ንስሐ

## «ጻድቅ ሰባት ጊዜ ቢወድቅ ሰባት ጊዜ ይነሳል»

የሐሰት ምንጭ፣ የጥፋት አበጋዝ ዲያብሎስ በነገሠባት ዓለም እየኖሩ በኃጢአት ተሰናክዬ አልወድቅም ማለት ግብዝነት ነው። «ሰው ሆኖ የማይበድል እንጨት ሆኖ የማይጨስ የለምና።» ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም በመልእክቱ እንዲህ ብሏል። «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፣ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም።» ፩ዮሐ.፩፥፰።

ክርስቲያን ግን በኃጢአት ሲወድቅ በንስሐ ፈጥኖ ይነሳል። አንድ ጊዜ ወድቄያለሁ ብሎ በኃጢአት ላይ ኃጢአት፣ በበደል ላይ በደል አይጨምርም። ለዚህም ነው «ጻድቅ ሰባት ጊዜ ቢወድቅ ሰባት ጊዜ ይነሳል» የተባለው።

የሰውን ድኅነቱን እንጂ ጥፋቱን የማይወድ መፍቀሬ ሰብእ እግዚአብሔር «ኃጢአተኛውም ካደረጋት ኃጢአት ሁሉ ቢመለስ፣ ትእዛዜንም ሁሉ ቢጠብቅ፣ ፍርድንና ቅን ነገርንም ቢያደርግ ፣ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም። የበደለው በደል ሁሉ አይታሰብበትም። በሠራው ጽድቅ በሕይወት ይኖራል።» በማለት ከኃጢአታችን ተመልሰን በጽድቅ መንገድ እንድንጓዝ ያስገነዝበናል። ሕዝ.፲፰፥፳፩–፳፫።

የርኅራኄ አባት፣ የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ከበደላቸው ተመልሰው የዘላለም ሕይወትን ይወርሱ ዘንድ «ንስሐ ግቡ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ። የበደላችሁበትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ። አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ። የእስራኤል ቤት ሆይ ስለምን ትሞታላችሁ? የምዋቹን ሞት አልፈቅድምና...ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ።» ይላል። ሕዝ.፲፰፥፴–፴፪።

ንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር የምንታረቅባት፣ ከሞት ወደ ሕይወት የምንሸጋገርባት ረቂቅ ድልድይ ናት። ለቸርነቱ ወሰን ለርኅራኄው መጠን የሌለው አምላካችን የባሕርያችንን ድካመት ያውቃልና በኃጢአት ተሰናክለን በምንወድቅበት ጊዜ ስለ ኃጢአታችን ተጸጽተን በድለናል ማረን ይቅር በለን በማለት አውቀን በድፍረት ሳናውቅ

በስህተት ለሠራነው ኃጢአት ይቅርታን እንድንጠይቅና ወደ እርሱ እንድንመለስ የሠራልን ደገኛ ሥርዓት «ንስሐ» ናት።

ንስሐ በዝሙት ማጥ ገብቶ ይዳከር የነበረውን ዘማዊ ድንግል፣ ቋንጃ ሲቆርጥ፣ ደም ሲያፈስ የነበረን ወንበዴ ንጹሕ የምታደርግ የእግዚአብሔር ልዩ በረከት ናት።

ከኃጢአት ሕይወት በሚመለሱ ሰዎች በሰማይ ያሉ ሠራዊተ መላእክት ሳይቀሩ ይደሰታሉ። «ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል» ሉቃ.፲፭፥፯።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ስብከቱ የንስሐን ጥቅም በምሳሌ ሲያስረዳ «አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት። ከእነርሱም ታናሹ የአባቱን ገንዘብ ወስዶ ለዘዋሪ ለአዝማሪ በትኖ ባዶ እጁን ቀረ። ራብና ጥም ሲፈራረቁበት የሚልሰው የሚቀምሰው ሲያጣ እሪያዎች ከሚበሉት አሰር ሊጠግብ ሞከረ።

ችግሩ ሲጠናበት በደስታ ይኖርባት የነበረውን የአባቱን ቤት አሰበ። አባቴ አይጨክንብኝም ይቅርታ ብጠይቀው ይቅር ይለኛል። «አባቴ ሆይ በሰማይና በፊትህ በደልሁ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም። ከአገልጋዮችህ እንደ አንዱ ቁጠረኝ እለዋለሁ» ብሎ ወደ አባቱ ሄደ።

አባቱም የጠፋው ልጁን በሩቅ ባየው ጊዜ ደስ ተሰኘ። ሮጦም አቀፈው። በመመለሱም ደስ ተሰኝቶ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አልብሱት፣ ለእጁ ቀለበት፣ ለእግሩም ጫማ ስጡት፣ የሰባውን ፍሪዳ አምጥታችሁ እረዱት፣ ደስም ይበለን። ይህ ልጅ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል። ጠፍቶም ነበር ተገኝቱአል» አለ። ሉቃ.፲፭፥፲፩–፴፪።

ምሳሌው በኃጢአት ምክንያት ከአባታችን ከእግዚአብሔርና ከመኖሪያችን ከቤተ ክርስቲያን ለምንርቅ ክርስቲያኖች የተመሰለ ነው።

በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ስንመለስ በኃጢአት ምክንያት ተገፈነው የነበረውን ጸጋ እግዚአብሔር መልሰን እንጎናጸፋለን። ሥጋውና ደሙን ለመቀበልም እንበቃለን።

ይቅር ባዩ አምላካችን በሠራነው ኃጢአት ሳይንቀንና ሳይጸየፈን በደላችንን ይቅር ብሎ በጸጋው ይጎበኘናል። «በኃጢአታችን ብንናዘዝ



ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» ፩ዮሐ.፩፥፱።

«እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለሕይወት የሚሆን ንስሐን ሰጣቸው» እንደ ተባለው የሐዋ.፲፩፥፲፰። በኃጢአት ምክንያት ምዉት ለሆኑት ሁሉ ንስሐ ያሻቸዋል– ሕይወትን ያገኙ ዘንድ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «አስቀድሜ በደማስቆ ላሉት በኢየሩሳሌምም በይሁዳም አገር ሁሉ ለአሕዛብም ንስሐ ይገቡ ዘንድና ለንስሐ የሚገባ ነገር እያደረጉ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ ተናገርሁ» በማለት ንስሐን እንደሰበከ አስገንዝቦናል። የሐዋ.፳፮፥፳።

የእግዚአብሔር ፈቃድና ትዕዛዝ በበደላችን እንዳንጠፋ ንስሐም እንድንገባ ነው። «እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል» የሐዋ.፲፯፥፴።

ቀድሞ በኃጢአት እግዚአብሔርን ያሳዘኑ የነበሩ ሰዎች ወደ ማኅበረ ምእመናን የሚቀላቀሉት በንስሐ ነው። «ካመኑትም ከነበሩት እጅግ ብዙ ሰዎች ያደረጉትን እየተናዘዙና እየተናገሩ ይመጡ ነበር» የሐዋ.፲፱፥፲፰።

ከላይ እንደተጠቀሰው ሰዎች የቀደመ በደላቸውን በመናገር ንስሐ ሊገቡ ይገባቸዋል። መጥምቁ ዮሐንስ የንስሐ ጥሪ ጩኸት እያሰማ ከምድረ በዳ በመጣ ጊዜ በኢየሩሳሌምና በዮርዳኖስ ዙሪያ ያሉ ሰዎች ሁሉ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር። ማቴ.፫፥፮።

ከዚህም የምንገነዘበው ንስሐ ስንገባ ኃጢአታችንን ሥልጣነ ክህነት ላላቸው ሰዎች መናዘዝ እንዳለብን ነው።

የጥበብ ሰው ሰሎሞን «ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል» በማለት ኃጢአታችንን ለካህን መንገርና ከዚያም በኋላ ኃጢአትን መተው እንደሚገባ አስረድቷል። ምሳሌ.፳፰፥፲፫።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለካህናት ንስሐን የመቀበልና ኃጢአትን የማስተሥረይ ሥልጣን እንደሰጣቸው ሲያረጋግጥልን «ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል» ብሏል። ዮሐ.፳፥፳፫።

ይህ ሥልጣን ደግሞ ለሐዋርያት ብቻ ሳይሆን እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ለሚሾሙ ካህናት የተነገረ ነው። ጌታ ለሐዋርያቱ «እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ» ማለቱም ይህን ሲያስገነዝብ ነው።

በጥምቀት የሥላሴ ልጅነትን ላገኘንና በስሙ ለምንጠራ ሁሉ «እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ! ንስሐም ግባ። ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ» በማለት ጌታ ያሳስበናል። ራእይ.፪፥፭—፮።

እንዲሁም ልቦናችን በኃጢአት ወይም በኑፋቄ ለጠመመውም «ቅና ንስሐም ግባ» በማለት የጠመመው ልቡናችንን በንስሐ እንድናቀና ያስገነዝበናል። ራእይ.፫፥፲፱።

ድኅነት ንስሐ በመግባት ካለፈ. ጥፋትም በመመለስ የሚገኝ ነው። የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ የተመለሰውና አጥቶት የነበረውን የአባቱን ፍቅርና ቸርነት ያገኘው ባለፈው ስህተቱ ተጸጽቶ ንስሐ በመግባቱ ነው።

በሰማይ ያሉ ቅዱሳን መላእክት ታላቅ ደስታ የሚያደርጉት ንስሐ በሚገባ ሰው ነው። በሽተኛ የሆነ ሰው ሁሉ መድኃኒት ያስፈልገዋል። በኃጢአት ደዌ ለተመታ ሰውም ንስሐ አማራጭ የሌለው መድኃኒትና የድኅነት በር ነው።

## ምሥጢረ ተክሊል

ተክሊል የግቢ ሥርዓት፣ ቃል ኪዳን፤ ካህናት በመርዓዊና በመርዓት ላይ የሚፈጽሙት የሕግ ጋብቻ ሊፈርስ የማይችል ማለት ነው።* ይኸውም ፍጹም ክብርን የሚያጎናጽፍ ነው። መልካም ሚስት ለባልዋ ዘውድ ናት እንደ ተባለው ባል በሚስቱ የክብር አክሊልን የሚቀዳጅበት መንፈሳዊ አገልግሎት ነው።

ይህ ሥርዓት ያለ ቅዱስ ቁርባን አይፈጸምም። ሁለቱን ተጋቢዎች አንድ የሚያደርጋቸው የጌታ ሥጋውና ደሙ ነውና። ስለዚህ የሥርዓተ ተክሊል ፍጻሜ ጸሎተ ቅዳሴ ነው። በመሆኑም ሙሽሮች ሥጋውን ደሙን ይቀበሉ ዘንድ ይገባል።

---

* ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ ፭፻፴፱



## ጋብቻ መቼ ተጀመረ?

ጋብቻ የተጀመረው በመጀመሪያዎቹ ሰዎች በአዳምና በሔዋን ነው። የጋብቻ መሥራችም ልዑለ ባሕርይ አምላክ እግዚአብሔር ነው። የአዳምን ብቸኝነት የተመለከተ አምላክ «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም። የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።» በማለት ከአዳም ጎን አንዲት አጥንት ወስዶ ሔዋንን ፈጠራት። ዘፍ.፪፥፲፰—፳፪።

አዳምም ሚስት ትሆነው ዘንድ የተፈጠረችለትን ሔዋንን ወደዳት። «ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፣ ሥጋም ከሥጋዬ ናት። እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል» አለ። ዘፍ.፪፥፳፫።

አዳም ሚስቱ ሔዋንን የአጥንቴ ፍላጭ፣ የሥጋዬ ቁራጭ በማለቱ ባልና ሚስት አንድ አካል መሆናቸውን ተናግሯል። ይህ መሠረት ሆኖ ዛሬም ሰው አባቱንና እናቱን ያተዋል፣ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል። ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። በአንድ ጣሪያ ስር ይኖራሉ። ዘፍ.፪፥፳፬።

## ጋብቻ ቅዱስ ነው

በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት የተነሱ «ግኖስቲኮች» የሚባሉ መናፍቃን ጋብቻ የሰይጣን ሥራ ነው። በዚህ ዓለም መውለድ መራባት ኃጢአት ማብዛት ነው። እያሉ ያስተምሩ ነበር።*

የእነዚህን መናፍቃን የክህደት ትምህርት ቅዱስ ጳውሎስ ሲነቅፍ «በገዛ ኅሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው እነዚህ ውሸተኞች መጋባት ይከለክላሉ» ብሏል። ፩ጢሞ.፬፥፫።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ትምህርቱ ስለ ጋብቻ ቅዱስነት አስተምሯል። በአካል በሠርግ ቤት በመገኘትም ጋብቻን ባርኳል። ማቴ.፲፱፥፫—፮። ዮሐ.፪፥፩—፲።

ስለዚህ ጋብቻን ርኩስ አድርገው የሚያስተምሩ ሁሉ ከክርስቶስ አፀደ ወይን ከቤተ ክርስቲያን የተለዩ ናቸው።

---

* የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ ፺፮

## የጋብቻ ዓላማ

ጋብቻ ሦስት ዓበይት ዓላማዎች አሉት። እነዚህም:-

፩. መረዳዳት – ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ ይላሉ አበው። ለመደጋገፍ፣ አንዱ ሲደክም ሌላው እንዲያበረታ ከአንድ ሁለት መሆን የተሻለ ነው። ሁሉን የሚያውቅ አምላካችን እግዚአብሔር «ሰው ብቻውን ሊኖር አይገባውምና የምትረዳው እንፍጠርለት» ማለቱ የሰውን የባሕርይ ድክመት በማወቁ ነው። ዘፍ.፪፥፲፰።

፪. ዘር መተካት – ትውልድ ያልፋል:- ትውልድ ይተካል:- ሁሉም የተወሰነለትን የዕድሜ ገደብ ሲጨርስ ይጓዛል። አሮጌው ያልፋል አዲሱ ይመጣል። ይህ የሕይወት ሒደት ቀጣይነት እንዲኖረው ዘር መተካት ያስፈልጋል። ፈጣሪ ኩሉ ዓለማት እግዚአብሔርም «ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሉአት» ያለው ዘር መተካት እንደሚገባ ሲያስገነዝብ ነው። ዘፍ.፩፥፳፰። ዘር የሚተካው ደግሞ በየሜዳው ካገኙት ጋር በመዝለል አይደለም። ሰው ክቡር ፍጥረት እንደ መሆኑ በሥርዓት ይመራ ዘንድ ሕግ ተሰጥቶታል። ይህ ዘር የመተካት ሥርዓት ቅዱስ ጋብቻ ነው።

፫. ከዝሙት መጠበቅ – ሰዎች ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን ሲደርሱ ሥጋዊ ፍትወት ይፈታተናቸዋል። ስለዚህ በዝሙት ማጥ እንዳይወድቁና ሰውነታቸውን እንዳያረክሱ በቅዱስ ጋብቻ መወሰን ይኖርባቸዋል። ኮከበ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ጳውሎስ «ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው፣ ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት» በማለት ያስተማረው ለዚህ ነው። ፩ቆሮ.፯፥፪።

## ቅድመ ጋብቻ ሊጤኑ የሚገባቸው ነገሮች

- ሃይማኖት ለሁሉ ነገር መሠረት ነው። በጋብቻ ሕይወት በአንድ ላይ ለመኖር የተጫጩ ሁለት እጮኛሞች በሃይማኖት፣ በዓላማ አንድ ሊሆኑ ይገባል። (ዘኊቁ ፫፪)
- ከጋብቻ በፊት ማለትም በእጮኝነት ዘመን፣ ስለ ወደፊት ሕይወታቸው ከመመካከር ውጪ ምንም ዓይነት ግንኙነት ሊያደርጉ አይገባም።
- መተጫጨታቸው በእነርሱ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ቢሆንም የንስሐ አባታቸውና ቤተሰብ ሊያውቀው ይገባል።



- የተጫጪዎቹ እድሜ የሴትዋ ከ፲፭ ዓመት በላይ የወንዱ ደግሞ ከ፳ ዓመት በላይ ሊሆን ይገባል።[፩]
- ተጫጪዎቹ ስለ ሃይማኖታቸውና፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ከጋብቻቸው በፊት ሊማሩ ሊያውቁ ይገባቸዋል።

ከጋብቻው ቀን አስቀድሞ ቃል ኪዳናቸውን በቤተ ክርስቲያን ይፈጽማሉ። ሙሽራውና ሙሽራይቱ ከዘመዶቻቸው ጋር በቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ለቃል ኪዳን በተሰጠው ሕግ መሠረት የቀለበቱን ሥነ ሥርዓት ያደርጋሉ። በመተጫጨት የሰጡትንም የፈቃድ ቃል በመሐላ ያጸናሉ።

## ሥርዓተ ተክሊል

- ተክሊሉ በሚደርስበት ቀን ሙሽሮች ከዘመዶቻቸው ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ። ሙሽራውና ዘመዶቹ በሰሜናዊ ማዕዘን ሙሽራይቱና ዘመዶቹዋ በደቡባዊ ማዕዘን ሥፍራ ሥፍራቸውን ይዘው ይቆማሉ።
- በቤተ መቅደሱ ፊት ለፊት ባለው (ዐውደ ምሕረት) (ቅድስት) ላይ ሊቀ ዲያቆናቱ ሙሽራውና ሙሽራይቱ ሥርዓተ ተክሊል የሚፈጽሙበትን ምንጣፍ አንጥፎ ለሁለቱ የሚሆን መቀመጫ እንዲሁም አንድ ጠረጴዛና ሙሽሮቹ አንድ ሆነው የሚለብሱትን መጐናጸፊያ፣ የሚቀቡትን ቅዱስ ቅባት፣ የሚያቀዳጁዋቸውን አክሊላት ያዘጋጃል።
- ቀጥሎ ካህናቱ ሥርዓተ ተክሊሉን ማድረስ ይጀምራሉ።

ሙሽሮች በቃል ኪዳናቸው ጊዜ ቀለበት ያደርጋሉ። ወንድ በሴትዋ ጣት ላይ ያጠልቅላታል፤ ሴትዋ ደግሞ በወንድ ጣት ላይ ታጠልቅለታለች። ይኸውም የቃል ኪዳንና የሃይማኖት ምልክት በመሆኑ ነው።

በራሳቸው ላይ የሚቀዳጁት አክሊል የክብራቸው ምሳሌ ነው። አንድ መጎናጸፊያ መጎናጸፋቸው አንድ አካል ለምታደርጋቸው ጸጋ መብቃታቸውን የሚያስረዳ ነው።[፪]

---

፩. ፍት.ነገ አንቀጽ ፳፬ ምዕራፍ ፫

፪. ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ ፩፻፴፪ ና ፩፻፵

## ድኅረ ጋብቻ

- ባልና ሚስት አንድ አካል ከሆኑ በኋላ በሀሳብ፣ በዓላማ ሊለያዩ አይገባም። በመካከላቸው ጊዜያዊ ጠብ ቢፈጠር እንኳን እሳት ሆኖ የመጣውን ሌላው ውኃ ሆኖ ማብረድ ይገባል። በተለይ ሚስት ባልዋ ከውጭ ተበሳጭቶ የመጣበት ነገር ካለ እርስዋ ብስጭቱን የሚረሳበትን መንገድ መፍጠር እንጂ ተጨማሪ ፈተና ሆና ልትቀርብ አይገባትም።
- ባል ለሚስቱ የሚገባትን ሁሉ ያደርግላት ዘንድ ይገባዋል። እንዲሁም ሚስት ለባልዋ የሚገባውን ሁሉ መጠበቅ፣ ማድረግ ይኖርባታል። እርሱ የሚጠላውን ማድረግ የለባትም። እርሱም እርስዋ የሚጠላውን ማድረግ አይኖርበትም። የመከባበር ሕይወት ሊኖራቸው ይገባል። ፩ቆሮ.፯፥፫።
- ሚስት በአካልዋ ልታዝ አትችልም። በሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፣ ሥልጣን ለባልዋ ነው። እንዲሁም ባል በአካሉ ሊያዝ አይችልም፣ በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን። የለውም ሥልጣን ለሚስቱ ነው። ፩ቆሮ.፯፥፬።
- ለጾምና ለጸሎት ከተወሰነ ጊዜ በስተቀር ባልና ሚስት ተለያይተው ሊኖሩ አይገባም። በአንድ ጣሪያ ሥር ተጠልለው ሊኖሩ እንጂ ሊለያዩ አልተጋቡምና። ሰይጣን መለያየታቸውን ምክንያት አድርጎ እንዳይፈትናቸው በአንድነት ሊኖሩ ይገባቸዋል። ፩ቆሮ.፯፥፭።
- መከባበር የፍቅር መሠረት ነው። ስለዚህ ባልና ሚስት ሊከባበሩ አንዱ ለሌላው ሊታዘዝ ይገባል። ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትታዘዝ ሚስትም ለባልዋ መታዘዝ ይገባታል። እንዲሁም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ራሱንም ለሞት አሳልፎ እንደ ሰጠላት እንደዚሁም ባል ለሚስቱ ሕይወቱን አሳልፎ እስኪሰጥላት ድረስ ሊወዳት ይገባል። ኤፌ.፭፥፳፭–፳፮፤ ፩ጴጥ.፫፥፭።

## መፋታት ይቻላልን?

እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለያይ አይገባውም እንደ ተባለ ባልና ሚስት በሥጋወደሙ አንድ ከሆኑ በኋላ የተገባቡትን ቃል ኪዳን አፍርሰው ሊለያዩ ወይም ሊፋቱ አይገባቸውም። ለመለያየት



የሚያስችል ምክንያት ካልገጠመ በስተቀር። ባልና ሚስትን ሊለያዩ የሚችሉ ምክንያቶች ከሁለት አንዱ በዝሙት የተያዘ እንደሆነ። እንደዚሁም በመካከላቸው የሃይማኖት ልዩነት የተፈጠረ እንደሆን ነው። ከዚህ ውጭ ግን ሰነፈች፣ መከነች፣ ጠቆረች፣ ደኸየች በሚሉ ተልካሻ ምክንያቶች መፋታት አጥብቆ የተከለከለ ነው።

ይህን አንቀበልም ብለው ቢለያዩ እንኳን ወይ መታረቅ አለባቸው። አንታረቅም ካሉ ግን በየራሳቸው ንጽሕናቸውን ጠብቀው ማለትም ከዝሙት ርቀው ለብቻቸው መኖር አለባቸው እንጂ ሌላ እንዲያገቡ ቤተ ክርስቲያን አትፈቅድላቸውም። ፩ቆሮ.፯፥፲–፲፩።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በሚስት ታሥረህ እንደሆንህ መፋታትን አትሻ» ብሏል። ፩ቆሮ.፯፥፳፯። እንዲሁም መለያየት !መፋታት እንደማይገባ ሲያስገዝብ «ሴት ከባልዋ አትለይ። ወንድም ከሚስቱ አይለይ። ሁላችሁም በጌታችን ትእዛዝ አንድ ሆናችሁ ኑሩ» ብሏል። ፩ቆሮ.፲፩፥፲፩።

ነቢየ እግዚአብሔር ሚልኪያስም «የሕፃንነት ሚስትህን አትፍታ» በማለት የመጀመሪያ ሚስትን አገኙሁ፣ ብሎ ሌላ ሽቶ መፍታትና ሌላ ማግባት ከእግዚአብሔር መጣላት መሆኑን ያስተምራል። ሚል.፪፥፲፬–፲፮።

## ድጋሚ ጋብቻ ይፈቀዳልን?

ከላይ እንደተገለጸው ለፍቺ ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች የተወሰኑ ናቸው። እነዚህም የሃይማኖት ልዩነት መፈጠርና ከሌላ አካል ጋር በዝሙት መውደቅ ናቸው።

ከባልና ሚስት አንዱ ሃይማኖቱን ቢለውጥ ያልለወጠው ወገን በቤተ ክርስቲያን አባቶች ያስመክራል። ነገር ግን ለዋጩ ክፍል ልቡን እንደ ፈርኦን አደንድኖ በፍጹም አልመለስም ካለ ፍቺው በቤተ ክርስቲያን አባቶች ይጸናል። ሃይማኖቱን የጠበቀው ያልጠበቀው እንደሞተ ተቆጥሮ ለብቻዬ መኖር ያቅተኛል ካለ ንጽሕናዋን የጠበቀችውን በሕገ ቤተ ክርስቲያን ያገባል።

በሌላም በኩል ሁለተኛ ጋብቻ የሚፈቀደው በዝሙት ምክንያት ሚስቱን ወይም ባልዋን ለፈታች ወይም ለፈታ ነው። ቃል ኪዳኑን

የጠበቀው ክፍል ለቤተ ክርስቲያን ነግሮ ለብቻው መኖር የሚያቅተው ከሆነ ንጽሕናዋን የጠበቀችውን በዝሙት ምክንያት ያልተፈታችውን ያገባ ዘንድ ወይም ታገባ ዘንድ ይፈቀድለታል (ይፈቀድላታል)።

በተጨማሪም ከሁለት አንዱ በሞት ቢለይ በሕይወት የቀረው ቀሪውን ጊዜ በብቸኝነት ማሳለፉ ይከብደኛል ካለ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተወስኖ ያለውን ያገባ ዘንድ ተፈቅዶለታል። ፩ቆሮ.፯፥፴፱።

ሁለተኛ ጋብቻ በሥጋ ወደሙ ይከናወናል እንጂ ሥርዓተ ተክሊል አይደረግም።

# ምሥጢረ ክህነት

## የክህነት ትርጉም

ካህን የሚለው ቃል በቁሙ ሲተረጎም ቄስ፣ ጳጳስ፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ፣ የሕዝብ መሪ፣ አስተማሪ፣ መንፈሳዊ አባት ማለት ነው።[፩]

ክህነት የሚለው ደግሞ ተክህነ ከሚለው ቃል የወጣ ሲሆን፣ ካህንነት፣ ተክኖ ማገልገልን ፣ መንፈሳዊ ሹመት መቀበልን ያመለክታል።[፪]

ክህነት በክርስቶስ አምኖ ለተጠመቀ ሁሉ የሚታደል መንፈሳዊ ሹመት ሳይሆን በፈቃደ እግዚአብሔር ለዚህ አገልግሎት ተመርጠው በአንብሮተ እድ በጳጳሳት አማካይነት ለተሾሙ ብቻ የሚሰጥ ነው። አንዳንድ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ግን ሁሉም ክርስቲያን ካህን ነው የሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለው የስህተት ትምህርት ያስተምራሉ።

በቅዱስ መጽሐፍ ተዘግቦ እንደምናገኘው ማንኛውም ምእመን ካህናት ሊሠሩት የሚገባውን ሥራ መሥራት አይገባውም። ክህነት ተሹሞ በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ማገልገል ስለራሱና ስለ ሕዝብ መሥዋዕትና ጸሎት ማቅረብ፣ መባረክ፣ መቀደስ፣ ማጥመቅ፣ ማቁረብ የመሳሰሉትን መፈጸም የሚገባው ካህን ብቻ ነው።

---

፩. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ ፭፻፳፪

፪. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ ፭፻፳፪



## በዘመነ ብሉይ

እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ፈጥሮ በልጅነት አክብሮ ነቢይ፣ ካህን፣ ንጉሥ አድርጎ ስለ ሾመው በአሪት በወንጌል ሥርዓት እስኪወሰን ድረስ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ የነበሩ አበው በበረከተ አበው ከእግዚአብሔር እየተሾሙ ትንቢትን፣ ክህነትን፣ መንግሥትን ከቅዱስ መንፈሱ እየተቀበሉ በነቢይነታቸው ያለፈውን– የሚመጣውን ሲገልጡ ሲያስተምሩ፣ በካህንነታቸው መሥዋዕት ሲያቀርቡ ኖረዋል።[፩]

ካህን መባል በኦሪት ከመገለጹ በፊት የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ የወንጌል ሥርዓተ ቁርባን መምህርና ሰባኪ የብዑዓን ሐዋርያት መሪና ፊታውራሪ ሆኖ በቀራንዮ ሊያገለግል ታላቁ ካህን ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ከመምጣቱና ለመሥዋዕት ከመቆሙ በፊት ቤተ መቅደሱን ሊጠብቅ ንዋያተ ቅድሳት፣ ጾምን፣ ጸሎትን፣ ተባሕትዎን፣ ድንግልናንና ከዊነ ሰማዕትን ሊያዘጋጅ ከእግዚአብሔር ተመርጦ የተላከው በታማኙ ሽማግሌ በሴም አማካይነት ለእግዚአብሔር የተሾመው ካህን መልከጼዴቅ ነው። ዘፍ.፲፬፥፲፰–፳። መዝ.፻፲፥፬።[፪]

መዓረገ ክህነቱ ምጡቅ፣ ምስጢረ ክህነቱ ረቂቅ ለሆነው መልከጼዴቅ የሌዋውያን አባት አብርሃም ሌዊ ገና በወገቡ ሳለ በረከተ ገጽ እጅ መንሻ አቀረበለት። ዐሥራት አወጣለት። ካህኑ መልከጼዴቅም ኅብስተ አኰቴቱን፣ ጽዋዐ በረከቱን ባርኮ ቀድሶ በመስጠት ከቁርባነ ኦሪት ልዩ የኾነችውን ከመሥዋዕተ እንስሳ የከበረችውን ቁርባነ ወንጌል ከሰበከለት በኋላ አብርሃምን ባረከው። ዕብ.፯፥፩–፲።

የእምነት አባት አብርሃምም ይህን ታላቅ በረከት ተቀብሎ ዘንባባ ይዞ በዓለ እግዚአብሔርን አከበረ። እንስሳት በመሠዋት የክህነትን ሥራ ይሠራ ዘንድ መዓረገ ክህነትን እግዚአብሔር የፈቀደለት በረከቱን ከታላቁ ካህን መልከ ጼዴቅ በተቀበለበት ቀን ነው። ዘፍ.፲፬፥፳፩–፳፬። ዘፍ.፲፭፥፩–፲።

ሙሴ ለአሮንና ለአልአዛር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ሥልጣነ ክህነት ከመስጠታቸው በፊት ክህነትን በመምህራን ቡራኬ ከመንፈስ ቅዱስ ለማግኘትና ለመሾም መሠረቱና መጀመሪያው መልከ

---

፩. የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት ገጽ ፷፬

፪. የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት ገጽ ፷፮

ጼዴቅ አብርሃምን የባረከበት አብርሃም ከመልከ ጼዴቅ የተባረከበት ያ ቡሩክ ሰዓት ነው።*

ከቀደሙት አበው ተያይዞ በመጣው ሥርዓት መሠረት ሊቀ ነብያት ሙሴ ከእግዚአብሔር በታዘዘው መሠረት ከእስራኤል ልጆች መካከል አሮንና ልጆቹን በክህነት እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ ለይቷል። «አንተም ወንድምህን አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይተህ ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ ወደ አንተ አቅርብ» ዘጸ.፳፰፥፩።

በዚህ መሠረት ከነገደ እስራኤል የሌዊ ነገድ ለክህነት ተመርጠው በዘመነ ኦሪት የእግዚአብሔርን ቤት ያገለግሉ ነበር። ለክብረ እግዚአብሔር ሲባል ያደርጉት የነበረው ልብስም ለየት ያለ በወርቅና በሰማያዊ በሐምራዊም በቀይም ግምጃ የተፈተለ ከጥሩ በፍታ በብልህ ሠራተኛ የተሠራ ነበር።

ከሌላው ምእመን የተለየም አገልግሎት ነበራቸው። ሌላው ሕዝብ ሊነካው ሊሰራው የማይገባውን እነርሱ ብቻ ያከናውኑ ነበር። ዳሩ ግን ክህነትን ገንዘብ ሳያደርጉ ማለትም ሳይሾሙ በትዕቢት ሳይገባቸው ካህናት ብቻ ለፈጸሙት (ሊነኩት) የሚገባቸውን ፈጽመው ወይም ነክተው የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ላይ የነደደችና የተቀሰፉ በቅዱስ መጽሐፍ ታሪካቸው ተመዝግቦ ይገኛል።

ሳይገባቸው ጥናውን ይዘው እጣን እናጥናለን ያሉት ዳታንና አቤሮን መሬት አፍዋን ከፍታ ውጣቻቸዋለች። በዚህም ሳይገባቸው ማለትም ክህነት ሳይሾሙ በትዕቢት ካህናት ነን ብለው ለሚነሱና የክህነትን ሥራ እንሰራለን ለሚሉ ሁሉ መቀጣጫ ሆነዋል። ዘኍ.፲፮፥፩–፶።

በሌላም ቦታ እንደተዘገበው ንጉሥ ያዝያን ዝናው ሲናኝ ጭብጥ ልቡ ለጥፋት ታበየ። አምላኩ እግዚአብሔርንም አሳዘነ። ክህነት ሳይኖረው ወደ መቅደስ ገብቶ በዕጣን መሠዊያ ላይ ዐጠነ። ካህኑ ዓዛርያስና ከእርሱ ጋር ጽኑዓን የነበሩ ካህናት ተከትለው ገብተው «ያዝያን ሆይ ዕጣን ማጠን የተቀደሱት (የተመረጡት) የአሮን ልጆች የካህናት ሹመት ነው እንጂ ለእግዚአብሔር ታጥን ዘንድ ለአንተ

---

* የኢ.ት.እምነት በሦስቱ ሕግጋት ገጽ ፷፯



አይገባህም በድለሃልና ከመቅደስ ውጣ ከአምላክም ከእግዚአብሔር ዘንድ ክብር አይሆንልህም አሉት» ፪ዜና.፳፮፥፲፰።

ንጉሡ ያዝያን ግን ራሱን ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ አድርጓልና የካህናቱን ማስጠንቀቂያ ከመጤፍ ሳይቆጥር እንዳውም እንዴት ተናገሩኝ በማለት ተቆጥቶ ጥናውን እንደያዘ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በዕጣኑ መሠዊያ አጠገብ ሳለ በግምባሩ ላይ ለምጽ ታየ። ይህንን ያዩት ካህናቱም ፈጥነው አበረሩት። እስኪሞትም ድረስ ለምጻም ሆነ።

፪ዜና.፳፮፥፲፱–፳፫። ዖዛም ሳይገባው እጁን ዘርግቶ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት በመንካቱ ተቀስፏል። ፪ሳሙ.፮፥፮–፰።

ሕዝበ እግዚአብሔር እስራኤል ኃጢአት በሠሩና ከአምላካቸው ጋር በተጣሉ ጊዜ ስለሠሩት ኃጢአት ማስተስረያ የሚሆን መስዋዕት ያቀርቡ የነበሩት ካህናት ብቻ ነበሩ። ይህም በሙሴ መጽሐፍ እንዲህ ተጽፏል። «...ስለ ሠራው ኃጢአት ለእግዚአብሔር የበደል መሥዋዕት ያመጣል። እርሱም ከመንጋው የበግ፣ የፍየል እንስት ለኃጢአት መሥዋዕት ይሆናል፤ ካህኑም ስለ ኃጢአቱ! ያስተሰርይለታል።» ዘሌ.፭፥፮።

«ሙሴም አሮንን ወደ መሠዊያው ቀርበህ የኃጢአትህን መሥዋዕትና የሚቃጠለውን መሥዋዕትህን ሰዋ። ለራስህና ለሕዝቡም አስተሰርይ። እግዚአብሔርም እንዳዘዘ የሕዝቡን ቁርባን አቅርብ አስተሰርይላቸውም አለው» ዘሌ.፱፥፯። በኤርሚያስ መጽሐፍም እንዲህ የሚል ተጽፏል። «እንደ ልቤ የሆኑ ጠባቂዎችን እሰጣችኋለሁ በጥበብና በዕውቀት ይጠብቁዋችኋል» ኤር.፫፥፲፭።

## በዘመነ ሐዲስ

ብሉይ ኪዳን ለሐዲስ ኪዳን ምሳሌ መሆኑ የታወቀ ነው። እንዲሁም ካህናተ ብሉይ ለካህናተ ሐዲስ አምሳል ናቸው። የዘመነ ሐዲስ ካህናት በብዙ መልኩ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ከነበሩት ካህናት ይለያሉ። መዓረገ ክብራቸው ምጡቅ፣ ሥራቸውም ረቂቅ ነው። የማሠርና የመፍታት፣ እንዲሁም ልጅነትን የማሰጠት ሥልጣን አላቸውና። በወንጌልም በብዙ ሥፍራ ስለ ምሥጢረ ክህነት ተጽፎ እናገኛለን። ለአብነት ያህል የሚከተሉት ተጠቅሰዋል።

ሀ.ልዑለ ባሕርይ አምላክ በዘመነ ብሉይ ከሕዝቡ መካከል እርሱን እንዲያገለግሉ ሌዋውያንን ልዑለ ባሕርይ አምላክ እንደመረጣቸው ሁሉ በዘመነ ሥጋዌው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሌላው ምእመን ለይቶ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ አክብሮ የክህነትን ሥራ እንዲሠሩ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትን መርጧል። «እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል። በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል» ማቴ.፲፰፥፲፰።

ማሰርና መፍታት ሥልጣነ ክህነት ላለው ብቻ እንጂ ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና ለተሰጣቸው ክርስቲያኖች ሁሉ የተሰጠ አይደለም።

ለ. «በነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ። በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፣ ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ። ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው» ሉቃ.፮፥፲፪። ማቴ.፳፰፥፳።

በዚህም ሥልጣነ ክህነት ለሚሾሙ ሁሉ አብነት ሆኗቸዋል። በጾም፣ በጸሎት ሊሾሙ እንደሚገባቸው።

ሐ. ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል አንዱ ይሁዳ ከማኅበረ ሐዋርያት በወጣ ጊዜ በእርሱ ምትክ ሌላ ሰው መተካት እንዳለበት ቅዱስ ጴጥሮስ ለቀሩት ወንድሞቹ ነገራቸው። ማትያስን ሲተኩ «በመዝሙር መጽሐፍ:-...ሹመቱን ሌላ ይውሰዳት ተብሎ ተጽፎአልና።» በማለት በይሁዳ ምትክ ሊተካ የሚገባውን ሰው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንዲመርጥ ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ ጌታ እስካረገበት ቀን ድረስ ከእነርሱ ጋር አብረው ከነበሩት መካከል ዮሴፍንና ማትያስን በእግዚአብሔር ፊት አቁመው «የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ ሆይ ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ ስፍራ ይሄድ ዘንድ በተዋት በዚህች አገልግሎትና ሐዋርያነት ስፍራን እንዲቀበል የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው አሉ። ዕጣም ተጣጣሉላቸው። ዕጣውም ለማትያስ ወደቀና ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቆጠረ» የሐዋ.፩፥፲፭—፳።

ይሁዳ የተወው ሹመት ወይም አገልግሎት የክህነት መሆኑን ማንም የሚገነዘበው ነው። ሁሉም ሐዋርያ መሆን ስለማይችል ለሐዋርያነት ማትያስ ተመረጠ። ዛሬም ለክህነት ከምእመኑ መካከል ሥርዓተ ቤተ



ክርስቲያን በሚያዘው መሠረት ጸንተው የተገኙ ተሹመው ካህናት ይባላሉ እንጂ ሁሉም ክርስቲያን ካህን ሊሆን አይችልም።

መ. ንዋየ ሕሩይ የተባለ ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈስ ቅዱስ ልጁ ለቅዱስ ጢሞቴዎስ በላከለት ቀዳማዊ መልእክቱ ጌታ ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንደሾመው ገልጹአል።«ለአገልግሎቱ ሾሞኝ ታማኝ አድርጎ ስለቆጠረኝ ኃይል የሰጠኝን ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታችንን አመሰግናለሁ» ፩ጢሞ.፩፥፲፪።

ሠ. ሥልጣን ክህነትን ማንም በገዛ ፈቃዱ ገንዘብ ሊያደርግ እንደማይችል ፈቃደ እግዚአብሔር መኖር እንዳለበት አስመልክቶ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስገነዝብ «እንደ አሮንም ከእግዚአብሔር ከተጠራ (ከተመረጠ) በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም» ብሏል። ዕብ.፭፥፬።

ረ. ሁሉም በተሰጠው ጸጋ እግዚአብሔርን ማገልገል እንዳለበት በእግዚአብሔር ቃል ታዟል። «እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ ሌሎቹም ነቢያት ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፣ ሌሎችም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ» ኤፌ.፬፥፲፩።

ሰ. «አሁንም እግዚአብሔር በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያንን እንድትጠብቁ መንፈስ ቅዱስ ጳጳሳት አድርጎ እሱን ለማገልገል የሾመባችሁን መንጋውን ሁሉና ራሳችሁን ጠብቁ» የሐዋ.፳፥፳፰።

መንጋውን እንዲጠብቁ በመንፈስ ቅዱስ የተሾሙ ካህናት መኖራቸውን በዚህ አነጋገር እንረዳለን።

## የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ

ለቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የካህናት የአሿሿም ሥርዓትን በተመለከተም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መሠረት ያደረገችው ቅዱስ መጽሐፍን ነው። በቅዱስ መጽሐፍ እንደተዘገበው ሥልጣነ ክህነት በጾም በጸሎት እጅን በተሿሚው ላይ በመጫን እፍ በማለት በጳጳሳት አማካይነት ይሰጣል። ከላይ እንደተገለጸው ሥርዓቱ የተወሰደው አእማደ ቤተ ክርስቲያን ከተባሉት ሐዋርያት ነው።

«መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ። በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም በኋላ እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው» የሐዋ.፲፫፥፪።

ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ ከሌሎቹ ስድስት ሰዎች ጋር ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተመርጠው ክህነት ሲሾሙ በአንብሮተ እድ በጸሎት ነው። ‹በሐዋርያትም ፊት አቆሙአቸው። ከጸለዩም በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው» የሐዋ.፮፥፮። መፍቀሬ ሰብእ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ክህነትን ሲሾማቸው ‹እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፣ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው» ዮሐ.፳፥፳፪።

ከእነርሱ ተለይቶ ነፍሳትን ተረግጦ መሬትን ለቆ ወደ ሰማይ ከመውጣቱ፣ ከማረጉ በፊት ሐዋርያትን እስከ ቢታንያ አውጥቶ እጆቹን በማንሳት ባርኳቸዋል። ሉቃ.፳፬፥፶። በዚህም ዛሬ ላሉት ካህናት አብነት ሆኗቸዋል።

ጌታችን ለሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን በንፍሐት፣ በአንብሮተ እድ ከሰጣቸው በኋላ እነርሱም ለተከታዮቻቸው ከእርሱ በተማሩት መሠረት ሥልጣነ ክህነትን በአንብሮተ እድ እያስተላለፉ እስከ ዛሬ ደርሷል።

በምሥጢረ ክህነት አፈጻጸም ላይ ሁለት ነገሮችን እንገነዘባለን። የሚታይ አገልግሎትና የማይታይ ሀብት።

የሚታይ አገልግሎት ስንል ጳጳሱ በአንብሮተ እድ (እጅን በመጫን) ሲሾም፣ ጸሎት ሲጸልይ ክህነት የሚቀበለውም በሰቂለ ሕሊና፣ በሰፊሐ እድ፣ በአንቃዕደዎ አዕይንት፣ በአድንኖ በተመስጦ ሲጸልይ ይታያል። በቅዱስ መጽሐፍ «በጳጳሳት እጅ ከተሾምከው ሹመት ጋርም የተሰጠህን ባንተ ላይ ያደረውን የእግዚአብሔርን ጸጋ አታቃል» የተባለውን መሠረት በማድረግ። ፩ጢሞ.፬፥፲፬።

የማይታይ ሀብት የምንለው ሥልጣነ ክህነት ጸጋ፣ ሀብት፣ የማሠር የመፍታት፣ የማንጻትና፣ የማጽናት፣ የማዳን ሥልጣን ሲሰጥ አይታይም።*

* ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ ፺፮



## ሢመተ ክህነት

የክህነት ሹመት ሦስት ደረጃ አለው። ዲቁና፣ ቅስና፣ ኤጲስ ቆጶስነት። ከዚህም በላይ ጳጳስ፣ ሊቀ ጳጳስ፣ ፓትርያርክ አለ። እንደየማዕርጉም ሥርዓተ ሲመትና ጸሎት አለው።[፩]

## ፓትርያርክ

ፓትርያርክ የሚለው ቃል የግሪክ ቋንቋ ነው። ፓተር ወይም ፓተር አባት ማለት ነው። ያርክ ማለት መዠመሪያ ወይም በር ከፋች ማለት ነው። ፓትርያርክ የመዠመሪያ አባት ወይም የመዠመሪያ በር ከፋች ማለት ነው።[፪]

ፓትርያርኩ ርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ነው። የሲኖዶስን ጉባኤ በሰብሳቢነት ይመራል። ሲሾም ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳት ይገኛሉ። ያለ ኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ ሹመቱ አይደረግም።[፫]

ሲጠራም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ__________ፓትርያርክ ርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ዘ__________ተብሎ ነው። ሌሎች ሊቃነ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ እገሌ ይባላሉ እንጂ ብፁዕ ወቅዱስ ተብለው አይጠሩም።

በጥንተ ክርስትና ሊቀ ጳጳሳት ተብሎ ነበር የሚጠራው። ከሊቃነ ጳጳሳትና ከጳጳሳት ከኤጲስ ቆጶሳትም ለአንዱስ እንኳ ሌላው ያወገዘውን መፍታት አይገባውም። ከሞተ በኋላ ነው እንጂ። ሊቀ ጳጳሳት ግን የሁሉንም ግዝት ሊፈታ ሥልጣን አለው። እርሱ በነርሱ ላይ እንደ ባለቤት ነውና። በሁሉም ላይ ክቡር ነው።[፬]

ሊቀ ጳጳስ የጳጳሳትና የኤጲስ ቆጶሳት አለቃ ነው።[፭]

ሊቃነ ጳጳሳት ቤተ ክርስቲያንን እንዲጠብቁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሾማቸው የሐዋርያት ተከታዮች ናቸው። የሐዋ.፳፥፳፰።

ሊቃነ ጳጳሳት:- ኤጲስ ቆጶሳትን ይሾማሉ፣ ስለ ሀገር ይጸልያሉ፣ በጉባኤ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ ያመለክታሉ፣ ሥልጣነ ክህነትን ይሰጣሉ።

፩. ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ገጽ ፺፰
፪. መጽሔተ አሚን ገጽ ፺፰
፫. ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ገጽ ፺፰
፬. ፍ.ነገሥት አንቀጽ ፬ ኒቅያ ፺፩
፭. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ ፬፻፮

ጳጳስ ወይም መጥሮጶሊስ የኤጲስ ቆጶሳት አለቃ ፓፓ፣ ሊቀ ጳጳስ፣ አዛዥ ነው።

ኤጲስ ቆጶስ (በግሪክ ኤፒስኮፖስ) ጠባቂ መምህር፣ የጳጳስ ኹለተኛ፣ የሊቀ ጳጳስ ሦስተኛ ነው።[፩]

ስለ ኤጲስ ቆጶስነት አሿሿም በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል «ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው። እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል። የማይነቀፍ የአንዲት ሚስት ባል፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ እንደሚገባው የሚሠራ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ለማስተማር የሚበቃ፣ የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ፣ ነገር ግን ገር የሆነ፣ የማይከራከር፣ ገንዘብን የማይወድ፣ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል? በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ነቀፋና ወጥመድም እንዳይወድቅ በውጭ ካሉት ሰዎች ደግሞ መልካም ምስክር ሊኖረው ይገባል» ፩ጢሞ.፫፥፩-፯።

በፍትሐ ነገሥት እንደተደነገገው ኤጲስ ቆጶስነት የሚሾመው ሰው እድሜው ከ፶ ዓመት በታች መሆን የለበትም። ነገር አዋቂ መምከር የሚችል መሆንም ይኖርበታል።[፪]

በሐዋርያት ዘመን ኤጲስ ቆጶስ የአንዲት ሚስት ባል መሆን እንዳለበት ተጽፎ እናነባለን። ዳሩ ግን በኋለኛው ዘመን ግን በችግር ጊዜ ካልሆነ በቀር ሕዝባዊ ሊሾም እንደማይገባ የግዴታ የሚያስመሰግን ሥራ ያለው መነኩሴ እንዲሆን ተደንግጓል።[፫]

የሚሾመውም በሚሾምበት አገር ምእመናን ምርጫና በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ፈቃድ ነው። በሚሾምበት ጊዜ ሦስት ወይም ሁለት ኤጲስ ቆጶሳት ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ጋር አብረው ይሾማሉ።[፬]

ኤጲስ ቆጶስ ቀሳውስትን ይባርካል። እሱ ግን በቀሳውስት አይባረክም። ከቀሳውስት እስከ ዐጻዊ ኆኅት ያለውን ሹመት ይሾማል። ነገር ግን ሳይመረምር ሳይፈትን ማንንም ክህነት እንዳይሾም ተከልክሏዋል። ፩ጢሞ.፭፥፳፪።

፩. ፍት.ነገ.አንቀጽ ፮ ቁጥር ፪፻፲፫ ረስጠጅ ፪ (ኪዳን ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ ፪፻፶
፪. ፍት.ነገ. አንቀጽ ፭ ቁጥር ፻፶ ድስቅ ፪ ገጽ ፴፰
፫. ፍት.ነገ. አንቀጽ ፭ ቁ.፻፱ ገጽ ፵
፬. ፍት.ነገ. አንቀጽ ፭ ቁ. ፲፪ ረስጠጅ ፩፭ ፪



## ቄስ

ቀሳውስትን በተመለከተ በቅዱስ መጽሐፍ የሠፈረ አለ። በቀደሙት የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች ላይ በአግባቡ ቀሳውስት የሚለው ተጽፎ ስናገኝ በቅርቡ በአዲስ ትርጉም የታተሙት ቅዱሳት መጻሕፍት ደግሞ ሽማግሌዎች በሚለው ተተክቷል። ሽማግሌዎች የሚለው ቃል ቀሳውስትን ለማመልከት መሆኑ ግልጽ ነው። አለበለዚያ ሁሉም ሽማግሌ ለቤተ ክርስቲያን የተሾመ ነው ወደሚለው ይወስዳል። «ለቤተ ክርስቲያንም ቀሳውስትን ሾሙ። ጾሙ፣ ጸለዩ፣ ለሚታመኑት ለእግዚአብሔርም አደራ ሰጡአቸው» የሐዋ.፲፬፥፳፫።

«ስለዚህም ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም እኔ አንተን እንዳዘዝሁ ቀሳውስትን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ። የማይነቀፍና የአንዲት ሚስት ባል የሚሆን የሚያምኑም ልጆች ያሉት ስለመዳራትም ወይም ስለ አለመታዘዝ የማይከሰስ ማንም ቢኖር ሹመው» ቲቶ.፩፥፭።[፩]

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ለቅስና የሚመረጥ ዲያቆን

- ነውርና ነቀፋ የሌለበት
- አንዲት ድንግል ሴት ያገባ፣
- ቂመኛ ያልሆነ፣ አብዝቶ የማይጠጣ
- እጁን ለመማታት አንደበቱን ለመገዘት የማያፈጥን
- በፍቅረ ንዋይ ልቡ ያልነደደ፣ እንግዳ መቀበልን የሚወድ።
- ወንጌልን በማስተማር ምእመናንን ማጽናናት የሚቻለው መናፍቃንን በትምህርት የሚረታ። ሊሆን ይገባዋል።[፪]

ሠላሳ ዓመት ያልሞላው ቅስና መሾም እንደሌለበት ሕጉ ይደነግጋል። ምንም የበቃ ቢሆን ይህ ዘመን እስኪሞላው ድረስ ይቆይ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሠላሳ ዘመኑ የተጠመቀበትና ማስተማር የጀመረው ይህንኑ ለማጠየቅ ነውና።[፫]

፩.ሐዲስ ኪዳን በናሽናል ባይብል ፕሬስ፣ ፊላደልፊያ በ፲፱፻፴፰ ዓ.ም የታተመ) ሐዲስ ኪዳን በሊቃውንት ጉባኤ ታርሞ የተዘጋጀ ፲፱፻፸፭ ዓ.ም መጽሐፍ ቅዱስ (ሰማንያ አንዱ) በ፲፱፻፹ ዓ.ም
፪. ፍት.ነገ. አንቀጽ ፮ ቁጥር ፪፻፲። ገጽ ፸
፫. ፍት.ነገ.አንቀጽ ፮ ቁጥር ፪፻፲፩

## ሹመቱን በተመለከተ

በበጎ ምግባራቸው በሃይማኖታቸው ጽናት በእውቀታቸው ለቅስና ማዕርግ የሚበቁ ዲያቆናት በኤጲስ ቆጶሱ ይሾማሉ። «ኤጲስ ቆጶስ ቄስን ይሾም ዘንድ ቢወድ በአንብሮተ እድ ይሹመው» [፩]

ያለ ኤጲስ ቆጶሱ ፈቃድ ቄስም ዲያቆንም አይሾምም።

## አገልግሎታቸው

በዘመነ ኦሪት ለካህናቱ ለአሮን ልጆች እግዚአብሔር አምላክ በባለሟሉ በሙሴ አማካይነት ሊያደርጉት የሚገባቸውን ሁሉ አስታውቋቸዋል። ዘሌ.፳፩፥፩–፲፭።

ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በምልዓት በተለገሰበት በዘመነ ሐዲስ ደግሞ የካህናት አገልግሎት እጅግ ሰፍቷል። ነገር ግን ሁሉም በየደረጃው የሚያከናውነው አገልግሎት አለው። ቀሳውስት ያስተምራሉ፣ ያጠምቃሉ፣ ይቀድሳሉ፣ ይባርካሉ፣ ይጸልያሉ። ዳሩ ግን ክህነት አይሾሙም።[፪]

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም «ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ቀሳውስትን ወደ እርሱ ይጥራ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል። ጌታም ያስነሣዋል ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል» ያዕቆብ ፭፥፲፬ ና ፲፭።

ቀሳውስት ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ክህነትን ብቻ መሾም አይችሉም እንጂ ሌላውን መፈጸም ይችላሉ።

## ዲያቆን

ዲያቆን የሚለው ቃል «ዲያኮኖስ» ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ነው። ትርጉሙም ረዳት አገልጋይ ማለት ነው።[፫]

የቄስ ተወራጅ ወይም ረዳት ሲሆን የሚሾመውም በአንብሮተ እድ ነው። ዲያቆን የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደ መሆኑ መጠን ለኤጲስ ቆጶሱና ለቄሱ ይላካል። በተጨማሪም ሕሙማንን በመጐብኘት

፩. ፍት.ነገ. አንቀጽ ፮ ቁጥር ፪፻፲፫።
፪. ፍት.ነገ.አንቀጽ ፯ ቁጥር ፪፻፲፭ ድስቅ ፴፱
፫. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ ፫፻፵፯



የችግረኞችን ጉዳይ ወደ ቄሱ ወደ ኤጲስ ቆጶሱ በማቅረብ ለችግረኞች ምጽዋት የሚሰጡትን ምእመናንን ሁሉ በማስተባበርና በመላላክ ያገለግላል። ከዚህ ውጭ ግን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ሊፈጽም አይችልም። ቀድሶ ደሙን ከማቀበል በስተቀር።[፩]

ዲያቆናት ምግባረ ሰናይ ሊሆኑ እንደሚገባቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። «ዲያቆናት ጭምቶች፣ በሁለት ቃል የማይናገሩ፣ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጐመጁ፣ ነውረኛ ረብ የማይወዱ፣ በንጹሕ ሕሊና የሃይማኖትን ምሥጢር የሚይዙ ሊሆኑ ይገባቸዋል» ፩ጢሞ.፫፥፰ ና ፱።

ሐዋርያት ለወንድሞች ዲያቆናት መልእክትን ይልኩላቸው ነበር። «የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያዎች የሆኑ ጳውሎስና ጢሞቴዎስ በፊልጵስዩስ ለሚኖሩ ለኤጲስ ቆጶሳትና ከዲያቆናት ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ቅዱሳን ሁሉ» ፊል.፩፥፩።

## ዲያቆናዊት

ሴት ዲያቆን ዲያቆናዊት ትባላለች። ዲያቆናዊት የ፷ ዓመት ባልቴት ልትሆን እንደሚገባት ተደንግጓል። በሴቶች ወገን እንደ ዲያቆን ሆና የምትላክ የምታገለግል ናት። ፩ጢሞ.፭፥፱። ዲያቆናዊትን በተመለከተ በፍትሐ ነገሥት እንዲህ ተደንግጓል። «ኤጲስ ቆጶስ ንጹሖቹን ሴቶች መርጦ ሴቶችን ለማገልገል ዲቁናን ይሹማቸው። ሴቶች ስለሚያሻቸው ነገር በጠና ጊዜ ከዲያቆናዊቱ በቀር ዲያቆንን ወደ ሴቶች ቤት ሊልክ አይገባምና። ስለዚህና ዳግመኛም ስለሚያጠምቋት ሴት ሰውነቷን ሜሮን ትቀባ ዘንድ ነው።» ወንድ የተራቆተችውን ሴት ማየት አይገባውምና። በቃል ብቻ እንጂ በአንብሮተ እድ አይሹሚቸው»[፪]

ከላይ ከተገለጸው ውጭ እንደ ዲያቆን «ተንሥኡ፣ ጸልዩ» እያለች ጸሎት አታገዝዝም። ዲያቆን ሳያዛትም ምንም ነገር አትሠራም። ሴቶችን በምክር ትረዳቸው ዘንድ ይገባል።[፫]

፩. ፍት.ነገ.አንቀጽ ፯ ቁ. ፪፻፵፯
፪. ፍት.ነገ.አንቀጽ ፰ ድስቅ ፲፯
፫. ፍት.ነገ.አንቀጽ ፰ ቁጥር ፪፻፰ በደስ ፯

## ኃጢአትን ለካህን መናገር እንደሚገባ

በዘመነ ብሉይ ሕዝበ እግዚአብሔር እስራኤል ስለሠሩት ኃጢአት ሥርየትን ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኙ የነበሩት በካህናት አማካይነት ነበር። ሕዝቡ ኃጢአቱን ለካህናት ይናዘዛል። ካህኑም ስለ ሕዝቡ ኃጢአት መሥዋዕት በማቅረብና በመጸለይ ሥርየተ ኃጢአትን እንዲያገኙ ያደርጋሉ። ዘሌ.፭፥፱–፲። ዘሌዋ.፬፥፩–፴፭።

በአሪቱ ለምጽ የወጣበት ሰው ወደ ካህኑ ሄዶ ለካህኑ ያሳየዋል። ካህኑም አይቶ መዳን አለመዳኑን ከመረመረ በኋላ ሱባኤ ገብቶ እንዲጸልይ ያዝዘዋል። ንስሐውን ከፈጸመ በኋላ ካህኑ እጁን ከቅብዑ ነክሮ ሰውነቱን ይቀባውና ከለምጹ ይነጻል። ዘሌ.፲፫፥፩–፲፯።

ኦሪት ለወንጌል ምሳሌ እንደመሆንዋ ጌታም በመዋዕለ ሥጋዌው የኦሪቱን ሕግ መሠረት በማድረግ ከለምጹ የነጻውን ሰው «ሂድና ራስህን ለካህን አስመርምረህ ከኃጢአትህ ስለ ነጻሕ (ስለዳንክ) መባዕህን አቅርብ» ብሎታል። ማቴ.፰፥፪–፬፤ ማር.፩፥፵፪–፵፭፤ ሉቃ.፭፥፲፬።

መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ የንስሐ ጥሪ ጩኸት እያሰማ ወደ ይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ በመጣ ጊዜ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ የሚኖሩ ሁሉ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ የንስሐ ጥምቀት ከዮሐንስ ይጠመቁ ነበር። ማቴ.፫፥፮።

ዛሬም ምእመናን ኃጢአታቸውን ለመምህረ ንስሐ አባታቸው በመንገር ከኃጢአታቸው ይፈታሉ። ጌታ «ምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሠረ ይሆናል፣ በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል» በማለት ከኃጢአት ማሰሪያ የመፍታት ሥልጣን ለግሏቸዋልና። ማቴ.፲፰፥፲፰።

መድኀኒ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም እንኳ የሚሾም የሚሽር ከኃጢአት የሚያነጻ የዘላለም ሕይወት የሚሰጥ እርሱ ቢሆንም ቃሉ የካህናትን ሥልጣን ለማስከበርና «ምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሆናል። በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል» ያለውን ቃል ለማጽደቅ በለምጽ የተመቱ አሥር ሰዎች እየጮኹ ወደ እርሱ በመቅረብ «ኢየሱስ ሆይ አቤቱ ማረን» ሲሉት አይቶ «ሂዱ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ (አስመርምሩ)» አላቸው እንጂ የማድን የማነጻ እኔ ሳለሁ ካህን ምን ያደርጋል? አላለም። ሉቃ.፲፯፥፲፬።



በዚህም ዛሬ በኃጢአት ለምጽ «ሕይወታቸው ለተመታ ሰዎች ወደ ካህናት ሔደው ኃጢአታቸውን ሳያፍሩ ሳይፈሩ በመናዘዝ ከኃጢአት ለምጽ ሊነጹ እንደሚገባ አስተምሯል።

ስለዚህ ምእመናን ኃጢአታቸውን ለካህን በመናገር ከካህኑ የሚሰጣቸውን ቀኖና በሚገባ ጨርሰው ከኃጢአት ማሰሪያ በካህኑ አማካይነት ሊፈቱ ይገባቸዋል። ከዚህ ውጭ ግን ኃጢአቴን ለእግዚአብሔር ብቻ እንጂ ለሰው አልናገርም በሚለው የሰነፎች ትምህርት ተሰናክለው ከእግዚአብሔር ሕግ ሊወጡ አይገባቸውም።

ካህኑም የተሾመበትን ሹመት ዘንግቶ የንስሐ ልጆቹን ኃጢአት ለሌላ ቢናገር እዳ ፍዳው በእርሱ ላይ ይሆናል ቅጣቱም ከባድ ነው። ካህን ምሥጢር ደባቂ፣ የሰማውን በልቡ ከረጢት ይዞ የሚኖር ሊሆን ይገባዋል። አንዳንድ ከሥርዓት የወጡ ካህናት የንስሐ ልጆቻቸውን ንስሐ ለሌሎች ሲናገሩ ይሰማሉ። ይህ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ጽኑ ፍርድ የሚያስፈርድባቸው እንደሆነ ሊያውቁት ይገባል።

## በካህን እጅ መባረክ ይገባል

በካህናት እጅ ተባርኮ ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከትን መቀበል ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ የነበረ ነው። ያዕቆብ ወልደ ይስሐቅ ወደ ግብፅ በወረደ ጊዜ ልጁ ዮሴፍ በግብፅ ምድር የወለዳቸውን ኤፍሬምንና ምናሴን በአባቱ እጅ ሊያስባርክ ይዞ ቀረበ። ያዕቆብም «እባርካቸው ዘንድ ወደዚህ አቅርብልኝ አለ»።

ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ የነበሩ አበው በበረከተ አበው ከእግዚአብሔር እየተሾሙ ክህነትን ከቅዱስ መንፈሱ ተቀብለዋልና ያዕቆብም በዚህ መሠረት ካህን ነበርና የዮሴፍን ልጆች በአንፃሩ በማቆም ቀኝ እጁን ዘርግቶ በኤፍሬም ራስ ላይ አኖረው ግራውንም በምናሴ ራስ ላይ አኖረ። እጆቹንም አስተላልፎ (በእጆቹ መስቀልያ ሰርቶ) የዮሴፍን ልጆች እንዲህ ሲል ባረካቸው «አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ የሄዱለት እርሱ እግዚአብሔር፣ ከታናሽነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እኔን

የመገበኝ እግዚአብሔር፣ ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ እርሱ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ» አለ። ዘፍ.፵፰፥፲፭–፲፮።

ዛሬም ካህናት በዚህ መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት መስቀል በረከትን በምእመናን ላይ ያሳድራሉ። «እግዚአብሔር ይባርካችሁ፣ ወላዲተ አምላክ ትባርካችሁ፣ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ይባርካችሁ» በማለት። ያዕቆብም «ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ እርሱ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ» በማለት መባረኩን መዘንጋት የለብንም። ዛሬም ካህናት «መልአኩ ገብርኤል ወይም ሚካኤል» ይባርኳችሁ ብለው መባረካቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ስብከቱ ወላጆች ከጥንት በተያያዘው ልማድ መሠረት ልጆቻቸውን ለማስባረክ ወደ ጌታ ይዘው ይመጡ ነበር። ጌታም ሕፃናቱን እጁን በመጫን በረከትን አሳድሮባቸዋል። በዚህም እንደራሴው እንዲሆኑ በንፍሐት በአንብሮተ እድ ለሾማቸው ካህናት አብነት ሆኗቸዋል። ማቴ.፲፱፥፲፫ ና ፲፭።

## ማእድን በካህን እጅ ማስባረክ

የምንመገበውን በካህን እጅ አስባርኮ መመገብ ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሲያያዝ የመጣ ነው። ጌታ አምስቱን እንጀራ፣ ሁለቱን ዓሣ አንሥቶ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየ። ባርኮና ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው። ደቀ መዛሙርቱም ተቀብለው ለሕዝቡ ሰጡ። ማቴ.፲፬፥፲፯–፳።

ይህን በመያዝ ማንኛውም ክርስቲያን ከካህን ጋር ማእድ ከቀረበ ማእዱን በካህን እጅ ያስባርካል። ማእዱ በርከት ያለ ሲሆን ታላቁ ቄስ ባርኮ በአጠገቡ ላሉት ይሰጣቸውና የቀሩትም አንዱ ለአንዱ እየተቀባበሉ ይመገባሉ። አብነቱም ከጌታ የተገኘ ነው። ጌታ ባርኮ ለሐዋርያት ሰጥቶ ለሕዝቡ እንዲሰጡ ባዘዛቸው መሠረት ሐዋርያት ከጌታ ተቀብለው ለሕዝቡ ሰጥተዋልና።*

---

* መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ገጽ ፴፬



## ሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን መቼ ተቀበሉ?

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ በተነሣበት በዕለተ እሑድ ሐዋርያት አይሁድን ፈርተው በዝግ ቤት ተሰብስበው ሳለ። መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ ሁሉ በዝግ ቤትም ገብቶ «ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው» እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ሥልጣነ ክህነትንም ሰጣቸው። «ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው» ዮሐ.፳፥፳፫። (መርሐ.ጽድቅ ገጽ ፴፩)

ይህ ዕለት ሐዋርያት ሥልጣነ ክህነት የተቀበሉበት ቀን እንደሆነ በሊቃውንቱ ይነገራል። ከዚያ በፊት በማቴ.፲፮፥፲፱ ላይ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ የማሰርና የመፍታት ሥልጣን እንደሰጣቸው ተዘግቦ እናገኛለን። ይህ የላይኛውን የሚቃረን መስሎ ይታያል። ዳሩ ግን በዚህ ሥፍራ ላይ የተጠቀሰው ለወደፊት በትንሣኤው ዕለት ባለው እሑድ የሚሰጣቸውን ሥልጣነ ክህነት ማመልከቱ ነው። የወደፊቱን አስቀድሞ እንደመናገር ነው።

## ግዴታቸውን የማይፈጽሙ ካህናት

ክህነትን ከተሾሙ በኋላ በተካኑበት ክህነት ተግቶ አለመገኘት ያስፈርዳል። «ራሳቸውን ለሚያሰማሩ ለእስራኤል እረኞች ወዮላቸው፣ እረኞች በጎችን ያሰማሩ ዘንድ አይገባቸውምን? ጮማውን ትበላላችሁ፣ ጠጉሩንም ትለብሳላችሁ፣ የወፈሩትን ታርዳላችሁ፣ በጎቹን ግን አታሰማሩም። የደከመውን አላጸናችሁትም፣ የታመመውንም፣ አላከማችሁትም የተሰበረውንም አልጠገናችሁትም፣ የባዘነውንም አልመለሳችሁትም፣ የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም፣ በኃይልና በጭቆናም ገዛችኋቸው። እረኛንም በማጣት ተበተኑ፣ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ፣ ተበተኑም። በጎቼ በተራሮች ሁሉና በረዘሙ ኮረብቶች ሁሉ ላይ ተቅበዝብዘዋል፣ በጎቼም በምድር ፊት ሁሉ ላይ ተበትነዋል...ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። እነሆ በእረኞች ላይ ነኝ። በጎቼንም ከእጃቸው እፈልጋለሁ» ሕዝ.፴፬፥፪–፲።

የክህነት ተግባራቸውን በአግባቡ ለሚፈጽሙና ለማይፈጽሙ ጌታችን በማስተማር ዘመኑ እንዲህ ብሏል «መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል። እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ። ሞያተኛ ግን ተኲላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል። ተኲላም ይነጥቃቸዋል። በጎቹንም ይበትናቸዋል። ሞያተኛ ስለ ሆነ ለበጎቹም ስለማይገደው ሞያተኛው (ምንደኛው) ይሸሻል» ዮሐ.፲፥፲፩–፲፫።

## ከክህነት የሚሽሩ ምክንያቶች

- የራሱን አካል የሰለበ ካህን ቢኖር ከሹመቱ ይሻር።[፩]
- በዝሙት ወይም በሥርቆት ወይም በሐሰት በመማል የተገኘ ከክህነቱ ይሻራል።[፪]
- የክህነትን መዓረግ ከተቀበለ በኋላ ያገባ ካህን ከሹመቱ ይሻራል። (ቄስ ከሆነ በኋላ)[፫]
- ሥጋዊ ሕማም ሳይከለክለው ጾመ አርብዓን ወይም የዓርብንና የረቡዕን ጾም የማይጾም ከክህነቱ ይሻራል።[፬]

እነዚህን የመሳሰሉ በፍትሐ ነገሥት የሠፈሩ ምክንያቶች ከክህነት ያስሽራሉ።

፩. ፍት.ነገ.አንቀጽ ፮ ቁጥር ፫፻፲፭
፪. ፍት.ነገ.አንቀጽ ፮ ቁጥር ፫፻፲፱ ረስጠጅ ፳፪
፫. ፍት.ነገ.አንቀጽ ፮ ቁጥር ፫፻፳፫
፬. ፍት.ነገ.አንቀጽ ፮ ቁጥር ፫፻፳፪



ምዕራፍ ሦስት

# መንፈሳዊ ተጋድሎ

«መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደሉ» ፩ጢሞ.፮፥፲፪።

ይህቺ ዓለም የተጋድሎ መድረክ ናት። በዓለም ላይ የሚኖሩ ክርስቲያኖችም በመንፈሳዊ ጦርነት ላይ ያሉ ናቸው። ጦርነቱም ከሥጋዊ ከደማዊ አርበኞች ጋር አይደለም። በአራቱ መዓዘን ካሉ ዓለመ ጽልመትን ከሚገዙ ከአጋንንት ጋር እንጂ። «የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፤ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ሥፍራ ካሉት ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።» በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረው። ኤፌ.፮፥፲–፲፫።

ዳዋ ጥሰው፤ ጤዛ ልሰው፤ ድንጋይ ተንተርሰው፤ የሌሊቱን ግርማ፤ የአራዊቱን ድምፅ ታግሰው በጦምና በጸሎት ተጠምደው በበረሃ ወድቀው ከጽልመት አበጋዝ ከዲያብሎስ ጋር አባቶቻችን መነኮሳት እንዲሁም በዓለም ውስጥ እየኖሩ ዳሩ ግን በተግባራቸው ዓለምን መስለው የማይኖሩ ክርስቲያኖች የሚያደርጉትን ተጋድሎ የሚነቅፉና የማይረባ የማይጠቅም እንዳውም የእግዚአብሔርን ቸርነት የሚቃወም አድርገው የሚገምቱ ዲያብሎስ ልቦናቸውን ዙፋን አድርጎ የተኮፈሰባቸው የሐሰት መምህራን ተከስተዋል።

እነዚህ ሰዎች አውቀውትም ይሁን ሳያውቁ በዲያብሎስ ፍላጻ ተነድፈው ከእግሩ ሥር የወደቁ የዲያብሎስ ተገዦች ናቸው። የጽድቅ መምህር ቅዱስ ጳውሎስ «ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፤ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ። እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፤ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፤ በሰላም ወንጌል በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ

በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነት ጋሻ አንሡ። የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ። እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።» ኤፌ.፮፥፲፫–፲፯። በማለት በእግዚአብሔር ቃል የተገለጠውን እና ዲያብሎስን የምንቃወምበትን መንፈሳዊ መሣሪያ እንድንታጠቅ አስገንዝቦናል።

ቅዱስ ጴጥሮስም ዲያብሎስን በመንፈሳዊ ተጋድሎ መቃወም እንደሚገባን ሲያስረዳ «ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፣ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።» ፩ጴጥ.፭፥፰ ና ፱። ብሏል።

## ዲያብሎስን የምንቃወምባቸው ረቂቅ መሳሪያዎች

ጾም – የሥጋን ምኞት የምታጠፋ፣ የነፍስን ቁስል የምታደርቅ ለጐልማሶች ጸጥታንና ርጋታን የምታስተምር፣ ከእንስሳዊ ግብርና ጠባይ፣ የምትከላከልና ሰው መላእክትን መስሎ የሚኖርባትና መንፈሳዊ ኃይልን የምታጎናጽፍ ናት።

ጾም የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ ከተባሉት አንደኛዋና ዋነኛዋ ስትሆን የሰይጣንን ረቂቅ ፍላጻ የምንመክትባት ረቂቅ ጋሻም ናት።

የጾምን ጥቅም የተረዱ ቀደምት አበው «በአምላካችን ፊት ራሳችንን እናዋርድ ዘንድ ከእርሱም የቀናውን መንገድ ላእኛና ለልጆቻችን ለንብረታችንም ሁሉ እንለምን ዘንድ በዚያ በአኅዋ ወንዝ አጠገብ ጾም አወጅሁ።» መጽ.ዕዝ.፰፥፳፩። በማለት ጾምን አውጀዋል።

«በጽዮን መለከት ንፉ፣ ጾምንም ቀድሱ» ኢዩ.፪፥፲፭።

ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ኃጢአት በሰውነታችን ላይ እንዳይሰለጥን ሥጋን በጾም ማድከም እንደሚያስፈልግ ሲያስገነዝብ «ነፍሴን (ሰውነቴን) በጾም አደከምኋት» ብሏል። መዝ.፴፬(፴፭)፥፲፫።

ትግላችን ከረቂቁ መንፈስ ጋር በመሆኑ የምንዋጋው በረቂቅ መሣሪያ ነው። ጾም ደግሞ የሥጋን ፈቃድ አድክማ የነፍስን ፈቃድ የምታበረታታ



ናት። ቅዱስ ዳዊት «ጉልበቶቼ በጾም ደከሙ ሥጋዬም ቅቤ በማጣት ከሳ» ያለው ለዚህ ነው። መዝ.፩፻፰፥፳፬።

ወደ እግዚአብሔር የምንቀርበው በጾም ነው። «አሁንስ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፣ በፍጹም ልባችሁ በጾምም በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ» ኢዩ.፪፥፲፪።

ጸጋ እግዚአብሔርን የምንጎናጸፈው በጾም ነው። ሊቀ ነቢያት ሙሴ ፵ መዓልትና ሌሊት ከጦመ በኋላ ነው ጽላትን የተቀበለው። ዘጸ.፴፬፥፴፬፤ ፳፰። ዘዳግ.፲፥፲።

ከጽልመት አበጋዝ ከዲያብሎስ ጋር በምናደርገው ፍልሚያ ጾም ዋነኛዋ መሳሪያ ናት። ጌታም ዲያብሎስን ድል የምናደርግበት ረቂቅ መሳሪያ መሆንዋን «ይህ ወገን በጸሎትና በጦም ካልሆነ በምንም ሊወጣ አይችልም» በማለት ርኵስ መንፈስን ሊያወጡ ለተሳናቸው ደቀ መዛሙርቱ አስገንዝቧቸዋል። ማር.፱፥፳፱።

የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ በሚደረገው ትግል ውስጥ ጾም አስፈላጊ መሆኑን ጌታ ሲያስረዳ «እናንተ አሁን የምትራቡ ብፁዓን ናችሁ ትጠግባላችሁ» ብሏል። ሉቃ.፮፥፳፩። በዚህ ትምህርቱ በፈቃዳቸው ለተራቡ ማለትም የሚጦሙ ሰዎች የሚያገኙትን በረከት ገልጡአል።

ጌታ ፵ መዓልትና ፵ ለሊት መጦሙ ለእኛ አብነት ይሆነን ዘንድ ነው። ከጦመ በኋላ በዲያብሎስ ተፈትኖ ዲያብሎስን ድል ነስቷል። በዚህም እኛም ከዲያብሎስ ጋር በምናደርገው ፍልሚያ ድል እናደርግ ዘንድ ጾምን እንድንይዝ መምህር ሆኖናል። ማቴ.፬፥፩–፲፩።

የስንፍናን ዝናር የታጠቁ ሰነፎች «የምንድነው በጸጋው እንጂ በእኛ ተጋድሎ አይደለም» በማለት። ጹሙ ሲባሉ «ጌታ ጾሞልናል» በማለት ጀርባቸውን ለጦም ይሰጣሉ። ዳሩ ግን ጌታ የዮሐንስ መጥምቅ ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ቀርበው «እኛና ፈሪሳውያን ብዙ ጊዜ የምንጦመው ደቀ መዛሙርትህ ግን የማይጦሙት ስለምንድር ነው?» ብለው በጠየቁት ጊዜ «ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ይችላሉን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ያመጣል፣ በዚያ ጊዜም ይጦማሉ» አለ እንጂ «እኔ ስለ እነርሱ ጾሜላቸዋለሁ የሚል መልስ አልሰጠም። ማቴ.፱፥፲፬–፲፭።»

ሐዋርያትም ይህን ትምህርት ተቀብለው ጌታ ከእነርሱ ከተለየ በኋላ ጦምን የሥራቸው መጀመሪያ አድርገዋል። የሐዋ.፲፫፥፩።

## ጾም በአዋጅ ወይስ በሥውር?

ጾም መጦም ያለበት በስውር እንጂ በአዋጅና በማኅበር መሆን እንደሌለበት የሚናገሩ አሉ። ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ጾም በአዋጅ ወይም በማኅበር እንዲሁም በግል እንደሚጾም ያስረዳል።

### ሀ. የአዋጅ (የማኅበር ጾም)

- የነነዌ ሕዝቦች ከተቃጣባቸው መቅሰፍት ይድኑ ዘንድ ከልሕቅ እስከ ደቂቅ በአዋጅ፣ በአንድነት ሆነው ጾመዋል። እግዚአብሔርም አዋጅ ተነግሮ በኅብረት በጾሙት ጾም የምኅረት እጁን ዘርግቶላቸዋል። ትን.ዮናስ.፫፥፭–፲።
- ሕዝበ እግዚአብሔር እስራኤል በአዋጅ (በማኅበር) ጾመዋል።

«በዚህም ወር በሀያ አራተኛው ቀን የእስራኤል ልጆች ጾመው ማቅም ለብሰው በላያቸው ትቢያ ነስንሰው ተከማቹ።» መጽ.ነህምያ ፱፥፩።

«በጽዮን መለከት ንፉ፤ ጾምንም ቀድሱ፤ ጉባኤውንም አውጁ፤ ሕዝቡንም አከማቹ፤ ማኅበሩንም ቀድሱ፤ ሽማግሌዎችንም ሰብስቡ፤ ሕፃናቱና ጡት የሚጠቡትን አከማቹ፤ ሙሽራው ከእልፍኙ፤ ሙሽራይቱም ከጫጉላዋ ይወጡ።» ትን.ኢዮ.፪፥፲፭–፲፮።

- ከጌታ እግር ስር ቁጭ ብለው ከአንደበቱ የተማሩ ሐዋርያት በማኅበር በመጾም ምሳሌ ሆነውናል። «በአንጾኪያ ባለችው ቤተክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ። እነርሱም በርናባስ፣ ኔጌር የተባለው ስምዖንም፣ የቀሬናው ሉክዮስም የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስም ባለምዋል ምናሔ፣ ሳውልም ነበሩ። እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ (ጌታን ያመልኩ የነበሩት እየጦሙ ነበር) መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ። በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጃቸውን ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው» ሐዋ.፲፫፥፩–፫።
- ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ፈሪሳውያን ይጾሙት የነበረውን የአዋጅ ጾም አልነቀፈም። በግብዝነት የተሞላ



ሕያወታቸውን እንጂ። «የዮሐንስና የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት የሚጦሙት ያንተ ደቀ መዛሙርት ግን የማይጦሙት ስለ ምንድር ነው ባሉት ጊዜ «የእነርሱ ጦም የአዋጅ ነው ስለዚህ ጥቅም የለውም የሚል መልስ አልሰጠም። እንደ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ ፊት እንደሚጾሙ ከማረጋገጥ በስተቀር። ማር.፪፥፲፰።

### ለ. የግል (የድብቅ) ጾም

ጌታ ስለ ግል ጦም ሲያስተምር «አንተ ግን ስትጦም በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ፣ ፊትህንም ታጠብ፣ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ያስረክብሃል።» ብሏል። ማቴ.፮፥፲፯።

የግል ጾም በግል የሚጦም እንደመሆኑ በሌላው ሰው ዘንድ ሊታወቅ አይገባም። ውዳሴ ከንቱን እንዳያመጣ። ይህም የግል ጦም ሰዎች ንስሐ በሚገቡበት ጊዜና በግላቸው ከአምላካቸው ይፈጸምላቸው ዘንድ የሚሹት ነገር ሲኖር በገዛ ራሳቸው ለራሳቸው የሚያውጁት ጾም ነው። ይህንንም የሚያደርጉት ከካህናት ጋር በመመካከር የሚያደርጉት ነው።

ቅዱስ ዳዊት ልጁ በታመመ ጊዜ የጦመው የግል ጦም ነው። መጽ.ሳሙ.ካልዕ.፲፪፥፲፮።

## የተወሰነ የጾም ወቅት ሊኖር ይገባልን?

አንዳንድ የእምነት ክፍሎች የጾምን አስፈላጊነት ያምኑና ዳሩ ግን የጾምን ወቅት በተመለከተ በቀኖና የተደነገገውን ድንጋጌ ይቃወማሉ። በእነርሱ አመለካከት ‹ማንኛውም ሰው በወደደውና በፈቀደው ጊዜ እንጂ ወቅት ተወስኖለት ሊጾም አይገባም። መጽሐፍ ቅዱስም የጾምን ቀን ወስኖ ጹሙ አላለም› ባዮች ናቸው።

በመሠረቱ የጾም አስፈላጊነት በመጽሐፍ ቅዱስ እስከ ተረጋገጠ እንዴትና መቼ ከምንስ መጾም እንዳለብን በቀኖና ቤተክርስቲያን መደንገጉ አስፈላጊና የማያጠያይቅ ነው። ምክንያቱም እንኳን ክርስቲያኖች አሕዛብም ለአምልኮታቸው ሥርዓትና ደንብ አላቸው። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የሕግና የሥርዓት ምንጭ ናት። ስለዚህ ለጦማችን ሥርዓትና ደንብ መውጣቱ አስፈላጊ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም ቢሆን የተወሰነ የጾም ወቅት ሊኖር እንደሚገባ ያስተምራል። ለምሳሌ የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት:-

- ዕዝራ ለእስራኤል ልጆች በአኅዋ ወንዝ አጠገብ ጾምን ሲያውጅ ጊዜን ወስኖ እንጂ እንዲሁ ያለ ገደብ ጡሙ አላለም። የጾሙም አዋጅ የመጣው ከእርሱ መሆኑን እንረዳለን። ዕዝ.፰፥፳፩።
- ከሕንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ በአሥራ ሁለት አገሮች ላይ እንደ አፈር ተበትነው ይኖሩ የነበሩት አይሁድ ከሐማ ሰይፍ ያመልጡ ዘንድ ወደ ንጉሡ አርጤክስስ ዘንድ እንድትገባ የተነገራት አስቴር በሱሳ ለሚኖሩት አይሁድ የሦስት ቀን ጾም እንዲይዙ በመርዶክዮስ በኩል ትዕዛዝ አስተላልፋለች። በዚህም መሠረት ጾመው የጾማቸውን መልስ አግኝተዋል።
- እስራኤል የተወሰኑ የጾም ወራት እንደነበሩአቸው «የአራተኛው ወር ጾም፣ የአምስተኛው፣ የሰባተኛው፣ የአሥረኛው ወር ጾም ለይሁዳ ቤት ደስታና ተድላ የሐሤትም በዓላት ይሆናል» የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ያስገነዝባል። ትን.ዘካ.፰፥፲፱።
- ሐዋርያትም የተወሰነ የጾም ወቅት እንደ ነበራቸው «የጦም ወራት አሁን አልፎ ስለ ነበር» በሚለው ቃል እንገነዘባለን የሐዋ.፳፯፥፱።
- ትዕቢተኛው ፈሪሳዊ «በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ» ማለቱ። ሉቃ.፲፰፥፲፪። የሚያስገነዝበን ፈሪሳውያን ከሳምንቱ ውስጥ ሁለቱን ቀን ወስነው ይጾሙ እንደ ነበር ነው።

የእግዚአብሔር የጸጋው ግምጃ ቤት የሆነችው ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያንም ምእመናን በፍጹም ልባቸው ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡበት ሰባት የአዋጅ አጽዋማትን ጊዜና ወቅት ወስና ደንግጋለች። በዚህም መሠረት:-

፩ኛ. ዓቢይ ጾም:- ፶፭ ቀን ሲሆን መጀመሪያውና መጨረሻው በየጊዜው ይለያያል።

፪ኛ. ጾመ ሐዋርያት:- መነሻው ከዕለተ ጰራቅሊጦስ ማግስት ሆኖ መጨረሻው ወይም መፍቻው ሐምሌ ፭ ቀን ነው።

፫ኛ. ጾመ ስብከት (የገና ጾም) የጾሙ መጀመሪያ ወር እኩሌታ ኅዳር ፲፭ ቀን ሲሆን መጨረሻው የጌታ ልደት ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ነው።



፬ኛ. ጾመ ፍልሰታ:- የሚጀምረው ነሐሴ ፩ ቀን ሲሆን የሚፈታው ነሐሴ ፲፮ ቀን ነው።

፭ኛ. ጾመ ድኅነት:- ረቡዕና ዓርብ።

፮ኛ. ጾመ ነነዌ — ሦስት ቀን ሲሆን

፯ኛ. ጾመ ገሃድ:- ጥር ፲ ቀን ለ፲፩ አጥቢያ ነው።

እነዚህን የጾም ወቅት የወሰኑት በመንፈስ ቅዱስ የተሾሙ የቤተክርስቲያን አባቶች ናቸው። ጌታ «እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፣ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል» በማለት ቤተ ክርስቲያንን የማስተዳደር ሥልጣን የሰጣቸው በመሆኑ እነርሱ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የደነገጉትን ሁሉ መቀበል ሃይማኖታዊ ግዴታችን ነው። ማቴ.፲፰፥፲፰።

## ከምን ልንጾም ይገባል?

ጦም ማለት መከልከል ማለት ነው። በጾማችን ጊዜ የቤተክርስቲያን ቀኖና እንደሚያዘን ከጥሉላት ምግብ ማለትም ከቅቤ፣ ከሥጋ፣ ከእንቁላል ከመሳሰሉት መከልከል አለብን።

- ነቢየ እግዚአብሔር ዳንኤል በሱባዔው ጊዜ ማለፊያ እንጀራ እንዳልበላ፣ ሥጋና ጠጅም በአፉ እንዳልገባ ይናገራል። ትን.ዳን.፲፥፪።
- ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት በጾሙ ወቅት ቅቤ ባለመብላቱ ሥጋው እንደከሳ ሲገልጥ «ጉልበቶቼ በጾም ደከሙ፣ ሥጋዬም ቅቤ በማጣት ከሣ» ብሏል። መዝ.፩፻፰፥፳፬።

ከእግዚአብሔር ቃል እንደተረዳነው ጾም የጽድቅ በር ነው። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንገባ ዘንድ ጾምን መቀደስ አለብን። የእግዚአብሔር ጸጋ የሚገኘው በጾም እንጂ ጾምን በመናቅና በማጥላላት አይደለም።

## ጸሎት

ከጨለማው ዓለም ገዢ ከዲያብሎስ ጋር በምናደርገው ፍልሚያ ከምንታጠቃቸው ረቂቅ መሳሪያዎች ሌላኛው ጸሎት ነው። ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሪያና የፈለጉትን ከእግዚአብሔር ለማግኘት

መለመኛ ነው። ሰማያዊው አባታችን እግዚአብሔር ጠላት ዲያብሎስን ድል የምናደርግበት ኃይል እንዲሰጠን የምንጠይቅበት መንፈሳዊ ቴሌግራም ነው።

«ለምኑ ይሰጣችሁማል፤ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል። የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና፤ የሚፈልግም ያገኛል፤ መዝጊያውንም ለሚያንኳኳው ይከፈትለታል።» ሉቃ.፲፩፥፱–፲፩።

ጸሎት የዲያብሎስን ረቂቅ ፍላጻ የምንመክትበት ረቂቅ ጋሻ መሆኑን ጌታ ሲያስገነዝበን «ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ» ብሏል። ማቴ.፳፮፥፵፩።

ደካማውን ሥጋ ለመንፈሳዊ ተጋድሎ የምናዘጋጀው በጸሎት ነው። «መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው።» በማለት ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ እንዳስተማራቸው። ማቴ.፳፮፥፵፩።

ጸሎት የክርስቲያኖች ዋና መሣሪያ መሆኑን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አብነት በመሆንና በማስተማርም አስገንዝቦናል። ማቴ.፳፮፥፴፮–፵፰። ዮሐ.፲፯፥፩–፳፮።

ዲያብሎስ በረቂቅ ገመድ ያሰራቸው በሽተኞች ከእስራቸው በጸሎት ይፈታሉ። የኃጢአት ምርኮኛ ያደረጋቸውም እርነት ይወጣሉ። መንፈሳዊ ኃይልንም ይጎናጸፋሉ። ያዕቆብ ፭፥፲፫–፲፰።

የጸሎትን ጥቅም አውቆና ተረድቶ በስንፍና ልዝም ተለጉም የማይጸልይ ሰው ኃጢአተኛ ነው። ምክንያቱም መልካም ነገርን ተምሮና አውቆ ተግባራዊ የማያደርገው ሁሉ እግዚአብሔርን በደለ ብሎ ሐዋርያው ያዕቆብ ተናግሯል። ያዕ.፬፥፲፯።

## ምን ብለን እንጸልይ?

ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ስትጸልዩ እንዲህ በሉ በማለት አቡነ ዘበሰማያትን አስተምሯቸዋል። ሉቃ.፲፩፥፪–፬። የቀረው ጸሎት ሁሉ የፈቃድ ሲሆን አቡነ ዘበሰማያት ግን የትእዛዝ ነው። ስለዚህ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኘ ሁሉ ይህን ጸሎት መጸለይ ግዴታው ነው። እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ይህን ጸሎት በቀን ሰባት ጊዜ እንጸልየዋለን። ይህም እንደው በዘፈቀደ የተወሰነ ሳይሆን ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት



«ስለ ጽድቅህ ፍርድ ሰባት ጊዜ በቀን አመሰግንሃለሁ» ያለውን መሠረት ያደረገ ነው። መዝ.፩፻፲፰፥፩፻፷፬።

አቡነ ዘበሰማያት በሚለው ጸሎት ውስጥ:- ሃይማኖት፤ ተስፋ፤ ፍቅር፤ ትሕትናና ልመና ተካተውበታል። ሃይማኖት ያላዩትን እግዚአብሔር አባታችን ብሎ መጥራት፤ ተስፋ መንግሥትህ ትምጣ ማለት፤ ፍቅር ሌላውንም ጨምሮ ለዚያም እንዲደረግለት መለመን፤ ትሕትና:- ቅዱሳን ከበቁ በኋላ ኃጢአታችንን ይቅር በለን እያሉ የሚጸልዩት ነውና ልመና የምንሻው ሁሉ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲደረግልን መጠየቅ።

## ሰባቱ የጸሎት ጊዜያት

እግዚአብሔር አምላካችንን በየሰዓቱ ማመስገን ወይም ማሰብ እንደሚገባን ቅዱስ ዳዊት «እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ እባርከዋለሁ፤ ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው» በማለት አስረድቶናል። ዳሩ ግን የየሰው ብቃት የተለያየ ነውና የበቁ የነቁ በየሰዓቱ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ (ሲጸልዩ) በማእከላዊነት ደረጃ ያሉ ደግሞ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በቀን ሰባት ጊዜ እንዲጸልዩ ሥርዓት ሠርታለች። እነዚህ የጸሎት ጊዜያት የሚከተሉት ናቸው።

፩. ነግህ (ማለዳ፤ ጧት) – ከእንቅልፋችን እንደተነሣን በሰላም ያሳደረንን አምላክ ልናመሰግን እንዲሁም ቀኑን በሰላም እንዲያውለን ልንጸልይ ይገባል። «በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ፤ በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ» እንዳለ መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት። መዝ.፭፥፫።

ይህ ሰዓት የተመረጠበት ሌላ ምክንያትም አለ። በዚህች ሰዓት አባታችን አዳም ያልተፈቀደለትን ዕፀ በልቶ ከገነት የተባረረበት ሲሆን ለአዳም ሊክስ የመጣው ጌታም በዚሁ ሰዓት ከጲላጦስ ፊት ቆሞ ተወቅሶበታል። ማቴ.፳፯፥፩።

፪. ሠለስት – ነቢየ እግዚአብሔር ዳንኤልን አብነት በማድረግ ነው። ትን.ዳን.፮፥፲። እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ለሐዋርያት የወረደበት ሰዓት ነው። የሐዋ.፪፥፲፭። በተጨማሪም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለእመቤታችን ያበሠረበት ሰዓትና ጌታ ከጲላጦስ ፊት ቀርቦ የተገረፈበት ሰዓት ነው።

፫. ቀትር – (ስድስት ሰዓት )እኩለ ቀን፣ ልበ አምላክ ዳዊት በዚህ ሰዓት ወደ አምላኩ ይጸልይ እንደ ነበር ተዘግቧል። መዝ.፶፬፥፲፯። ይህ ሰዓት ጌታችን በቀራንዮ ኮረብታ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መራራ ሐሞት ጠጥቶበታል፣ ልብሱን ተገፎበታል። በዚህ ሰዓት ስለ እኛ ብሎ ጌታ የተቀበለውን መከራ እያሰቡ መጸለይ ስለሚገባ አባቶቻችን ይህን ሰዓት ጸልዩበት ብለው ሥርዓት ሠርተዋል። ዮሐ.፲፱፥፲፬።

፬. ተሰዓት (ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት) – ጴጥሮስና ዮሐንስ በዘጠኝ ሰዓት ጸሎት ሊያደርጉ ወደ ቤተ መቅደስ ይወጡ ነበር። የሐዋ.፫፥፩። ይህ ሰዓት ጌታ ቅድስት ነፍሱን ከክቡር ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ የለየበትና በመስቀል ላይ እንዳለ ሰባት አጽራሐ መስቀል የተናገረበት ነው። ማር.፲፭፥፴፬፣ ማቴ.፳፯፥፵፭–፶።

ስለዚህ የእኛን ሞት ተቀብሎ የእርሱን ሕይወት ለእኛ እንደሰጠን እያሰቡ መጸለይ ይገባል በማለት ይህን ሰዓት ለጸሎት ተመርጧል።

፭. ሠርክ (ምሽት የቀን መጨረሻ የሌሊት መግቢያ) – በዚህ ሰዓት በዘመነ ኦሪት መሥዋዕት ይቀርብበት ነበር። ዘጸ.፳፱፥፴፱–፵፪። ቅዱስ ዳዊትም «ጸሎቴን በፊትህ እንደ ዕጣን ተቀበልልኝ እጅ መንሣቴንም እንደ ሠርክ መሥዋዕት ትሁን» ብሏል። መዝ.፩፻፵፥፪።

በዚህ ሰዓት ጌታችን ወደ ከርሠ መቃብር ወርዷል። ስለዚህ በመቃብር ውስጥ ፈርሶ በስብሶ መቅረትን ያስወግድ ዘንድ ስለ እኛ ወደ መቃብር መውረዱን እያሰቡ መጸለይ ይገባል። ማቴ.፳፯፥፷።

፮. ንዋም – (የእንቅልፍ የመኝታ ሰዓት)

ቅዱስ ዳዊት «ልቅሶ ማታ ይመጣል፣ ጥዋት ግን ደስታ ይሆናል» በማለት ማታ ከመተኛት በፊት ኃጢአትን እያሰቡ ማልቀስ መጸለይ እንደሚገባ አስረድቷል። መዝ.፳፱፥፭።

በዚህ ሰዓት ጌታችን ለሐዋርያቱ ሥርዓተ ጸሎት አሳይቶበታል። አ ኃሁድ በይሁዳ መሪነት ተረባርበው የያዙበት ሰዓት በመሆኑ ለእኛ ነ ሎ መያዙን እያሰቡ መጸለይ ይገባል። ማቴ.፳፮፥፴፰–፵፫።

፯. መንፈቀ ለሊት – «በእኩለ ሌሊት አመሰግንህ ዘንድ እነሣለሁ» በማለት ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በዚህ ሰዓት መጸለይ እንደሚገባ አስተምሯል። መዝ.፩፻፲፰፥፷፪።



እንዲሁም ጌታ ከእመቤታችን የተወለደው፣ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣበት፣ ዓለምን ለማሳለፍ ዳግመኛ ይመጣል ተብሎ የሚገመተው በዚሁ ሰዓት ነው። (እኩለ ሌሊትም ሲሆን – እነሆ ሙሽራው ይመጣል ትቀበሉት ዘንድ ውጡ» የሚለውን የጌታ ምሳሌያዊ አነጋገር መሠረት በማድረግ ነው። ማቴ.፳፭፥፭።

«ጸሎትን ደጋግሞ መጸለይ ምን ጥቅም አለው? እግዚአብሔር እንደ ሰው የሚረሳ አይደለ አንድ ጊዜ ከጸለዩ አይበቃም? በቀን ሰባት ጊዜ መጸለይ ምን ይሰራል?» የሚል ጥያቄ በአእምሯአቸው ለሚጉላላ ጌታ ያስተማረውን መጥቀስ ያሻል።

ጌታችን ምን ብለው መጸለይ እንደሚገባቸው ካስተማራቸው በኋላ ደግመው ደጋግመው ያለመሰልቸት መጸለይ እንዳለባቸው በምሳሌ ገልጾላቸዋል ሉቃ.፲፩፥፭–፲፫።

ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው ሌላ ምሳሌ መስሎም አስተምሯቸዋል። ሉቃ.፲፰፥፩–፰።

## በቅዱሳን ስም መጸለይ ይገባልን?

«ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል፣ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ» ትን.ዳን.፲፪፥፫ በማለት የእግዚአብሔር ነቢይ ዳንኤል እንደተናገረው ቅዱሳን በላይ በአርያም እንደ ከዋክብት በሥራቸው ደምቀው በክብር ቦታ አሉ። እነዚህ ስለ እግዚአብሔር ሲሉ አንገታቸውን ለሰይፍ ሥጋቸውን ለእሳት መቃጠል አሳልፈው የሰጡ ቅዱሳን በአጸደ ነፍስ ሆነው በከሃድያን ላይ እንዲፈርድ፣ ለክርስቲያኖች ደግሞ ምኅረትን እንዲያደርግ እንደሚለምኑ በቅዱስ መጽሐፍ ላይ ተዘግቧል። ራእይ.፮፥፱።

ስለዚህ የቅዱሳንን አማላጅነት ተረድቶ እግዚአብሔርን በእነርሱ ስም መለመን የሚገባ መሆኑን ከእግዚአብሔር ቃል እንረዳለን።

የተመረጠው ሙሴ እስራኤል በበደላቸው ምክንያት በመጣባቸው መቅሰፍት ጨርሰው እንዳይጠፉ ስለ እሥራኤል ሊለምን በእግዚ አብሔር ፊት በቆመ ጊዜ «ለዘላለም ይወርሱአታል ብለህ በራስህ የማልህላቸውን ባሪያዎችህን አብርሃምንና ይስሐቅን እስራኤልንም

አስብ» በማለት የቅዱሳኑን የአብርሃምን የይስሐቅንና የያዕቆብን ስም መለመኛ እንዳደረገው እናስተውላለን። ዘጸ.፴፪፥፲፬።

እግዚአብሔርም የባለሙዋሎቹ ስም በተጠራ ጊዜ በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፋት ራርቷል። በዚህም ሙሴን የሚያህል ታላቅ ነቢይ፣ ጌታ ራሱ ባለሟልነቱን የመሰከረለት ሲጸልይ በእግዚአብሔር የተመረጡትን የእነ አብርሃምን ስም መማለጃ አድርጓል።

«ስለ ዳዊት ስለ ባሪያህ የቀባኸውን ሰው ፊት አትመልስ» በሚለው ጸሎት። በዚህም እግዚአብሔር በመረጣቸውና ደስ አሰኝተውት ባለፉት ቅዱሳን ስም መለመን እንደሚገባን እንረዳለን። መዝ.፩፻፴፩፥(፩፻፴፪)፥፲።

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም «ስለ እኔ፣ ስለ ባሪያዬም ስለ ዳዊት ይህችን ከተማ አድናት ዘንድ እጋርዳታለሁ» በማለት ስለ ቅዱሳን ሲል ከተቃጣ መቅሰፍት እንደሚያድን ተናግሯል። ትን.ኢሳ.፴፯፥፴፭።

ስለዚህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን «በእንተ ማርያም፣ በእንተ ቅዱሳን መሐረነ ክርስቶስ– ስለ እናትህ ስለ ድንግል ማርያም ስለ ወዳጆችህ ስለ ቅዱሳን ስትል ማረን» በማለት በጸሎትዋ ሁሉ የቅዱሳንን ስም እየጠራች የምትለምነው ጌታ ስለ ቅዱሳን ሲል እንደሚምር ከቅዱስ መጽሐፍ ስላገኘች ነው።

ጸሎት የክርስቲያኖች ረቂቅ መሳሪያ በመሆኑ አንድ ክርስቲያን ምንም ሥራ ቢበዛበት ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነሳ፣ ማታ ከመተኛቱ በፊት፣ እንዲሁም በምግብ ሰዓት መጸለይ ግዴታው ነው።

## የመንፈሳዊ ተጋድሎ ጥቅም

የገድል ዓይነቱ ብዙ ነው። ሥጋን ለነፍስ ማስገዛትና፣ ለኃጢአት ሥራ ማድከም በመሆኑ በተለያየ መልኩ ክርስቲያኖች ከጠላታቸው ከዲያብሎስ ጋር ይጋደላሉ።

የእግዚአብሔርን ቸርነት ምክንያት በማድረግ የስንፍና አጋፋሪ ሆኖ ከገድል በመራቅ እንደው በነፃ ያለ አንዳች ገድል (ሥራ) መንግስቱን እወርሳለሁ እያሉ መፎከር አያዋጣም። በጸጋው የተጎበኙ ሐዋርያት እንኳን «ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ (ድካም) እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል» በማለት ነው ያስተማሩት። የሐዋ.፲፬፥፳፪።



በመንፈሳዊ ሕይወታችን ዝለን የሰይጣን ወርከሾተ እንዳንሆን መጋደል እንዳለብን ሐዋርያው ያስጠነቅቀናል። «በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ፣ ከኃጢአተኞች በደረሰበት እንዲህ ባለ መቃወም የጸናውን አስቡ። ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም» ዕብ.፲፪፥፫።

«እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ» በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደትና በሌላውም መንፈሳዊ ተጋድሎ በመጽናት፤ «ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ» በመጾም በመጸለይ በመስገድ «ከእናንተም ይሸሻል። ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል።» ያዕ.፬፥፯–፰።

የእግዚአብሔርን ጸጋ የምናገኘው በመንፈሳዊ ተጋድሎ ነው። «እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እያስተማርን ሰውን ሁሉ እየገሠጽን፣ ሰውንም ሁሉ በጥበቡ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱን ነው፣ ለዚህም ነገር ደግሞ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ እደክማለሁ» በማለት በመንፈሳዊ ተጋድሎ። ልንኖር እንደሚገባ አስተምሯል። ቆላ.፩፥፳፱።

በብልጠት የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያገኙ የሚመስላቸው ደካሞች «ምሕረት ለወደደ ወይንም ለሮጠ አይደለም፣ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ» የሚለውን ጥቅስ በመጥቀስ ቅዱስ ጳውሎስ ገድል ትሩፋት አያስፈልግም ብሏል። ስለዚህ «ይህ ለመዳን የሚደረግ ከንቱ ሩጫ ነውና አይጠቅምም» ይላሉ።

ዳሩ ግን ሐዋርያው ይህን ማለቱ እነርሱ እንደተረዱትና እንደተረጎሙት ይሆን? ሐዋርያው በሃይማኖት የሚደረገውን ሩጫ ነቀፈን? እንዲህ ከሆነማ እርሱ የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ለምን ሮጠ? «ሩጫዬን ጨርሻለሁ ገድሌንም ተጋድያለሁ ከእንግዲህ የሕይወት አክሊል ይጠብቀኛል» ማለቱ ምሕረትን ለማግኘት እንደሮጠ የሚያመላክት አይደለምን?

ለቆሮንቶስ ምእመናን «በእሽቅድምድም ስፍራ የሚሮጡት ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን? እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ» በማለት ዘላለማዊ ሽልማትን ያገኙ ዘንድ እንዲሮጡ ለምን አዘዛቸው? ፩ቆሮ.፱፥፳፬።

በተጋድሎ ጸጋ እግዚአብሔርን መጎናጸፍ እንደሚቻል ሲያስገነዝብም «የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል። እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው፤ እኛ ግን የማይጠፋውን» ብሏል። ፩ቆሮ.፱፥፳፭።

እንግዲህ ትግላችን ከማን ጋር ነው? ከእኩያን አጋንንት ከዓለም ፍላጐት ጋር አይደለምን። መንፈሳዊ ተጋድሎአችንና ሩጫችን ግብዝነት የሞላበት፤ ለቸርነቱ ምክንያት የሚሆን ካልሆነ ሐዋርያው እንዳስገነዘበን «ነፋስን እንደሚጎስም ሁሉ እንዲሁ አልጋደልም» እንዳለው ከንቱ ተጋድሎ ይሆናል። ፩ቆሮ.፱፥፳፮።

ስለዚህ ሐዋርያው በገድላቸው የሚታመኑና በእነርሱ ሩጫ ብቻ ለሚታመኑ ሰዎች ተናገረ እንጂ የእግዚአብሔርን ምኅረትና ቸርነት ተረድተው ለቸርነቱ ምክንያት ይሆን ዘንድ ብለው በትህትና ለሚጋደሉትና ለሚሮጡት አይደለም።

ጭው ባለ በረሃ ላይ ወድቆ፤ በጣም በጸሎት ተወስኖ የሚኖር አንድ ባህታዊ ጌታ ተገልጦለት «እንደ ሥራህ ልስጥህ እንደ ቸርነቴ?» ብሎ ቢጠይቀው ባህታዊው በሥራው የሚመካ ነበርና «እንደ ሥራዬ ስጠኝ እንጂ ከሰው ርቄ፤ ከላመ ከጣመ ተከልክዬ ድንጋይ ተንተርሼ ጤዛ ልሼ ይህን ያህል ዘመን የኖርኩት ለጽድቅ አይደለምን? ስለዚህ ለእኔ እንደተጋድሎዬ ብዛት ስጠኝ ቸርነትህን ግን በከተማ የላመ የጣመ እየበሉ በዓለመ ሥጋ ለሚኖሩት አድርገው።» ብሎ ተናገረ።

ይህ ባህታዊ የእግዚአብሔርን ቸርነት ፈጽሞ የዘነጋና በሥራው ብቻ ሊጸድቅ የተነሣ በመሆኑ ከጸጋው ወጥቶ በሥራው ተመካ። ያን ጊዜ ጌታ «እሺ እንደ ሥራህ እሰጥሃለሁ» ብሎ ከእርሱ ተሰወረ። ወዲያው ዝሙት ጦሩን ሰብቆ መጣበት። ሊቋቋመው አልቻለም። ጾሙ ጸሎቱ ሊያግደው አልቻለም። ታብዮአልና። ተቅበዘበዘ በዓቱን ለቆ ወደ ከተማ ሄደ። በኃጢአት ወደቀ። በደለኛም ሆነ።

ልቡ ላይ ተተክሎ የነበረውን የትዕቢት ጦር ነቅሎ ጌታዬ ሆይ «እንደ ቸርነትህ እንጂ እንደ ሥራዬ አትስጠኝ» ብሎ ተማጸነ። የዚህን አባት መማሩን እንጂ ጥፋቱን የማይሻ ጌታ ትምክህቱን እንደ አሮጌ ቁና አሽቀንጥሮ በጣለ ጊዜ የምኅረት እጁን ዘረጋለት። ወደ በዓቱም ተመለሰ።



ተጋድሎው ለእግዚአብሔር ቸርነት ምክንያት እንጂ ብቻውን ለጽድቅ እንደማያበቃው ተማረ።

የቀደሙት አበው ታሪክ ለእኛ መገሠጫ መማሪያ በመሆኑ «በተጋድሎአችን እንጸድቃለን» ብለው ለሚታበዩ ሁሉ ትምህርት ሰጥቶ አልፏል። ሐዋርያውም «ምኅረት ለሮጠ ብቻ አይደለም» በማለት የእግዚአብሔር ምኅረት በቸርነቱም ጭምር የሚገኝ እንደሆነ አስገንዝቦናል።

## ዝግጅት ከሰው ድል ከእግዚአብሔር

ሰው ያስባል እግዚአብሔር ይፈጽማል። የልብ መዘጋጀት ከሰው የምላስ መልስ ግን ከእግዚአብሔር የሚሉት አባባሎች የሚያንፀባርቁት ሰዎች የሚገባቸውን በማድረግ የእግዚአብሔርን ቸርነት ተስፋ ማድረግ እንዳለባቸው ነው።

ገበሬ ይተክላል፤ ውኃ ያጠጣል በተረፈ እግዚአብሔር አዝመራውን እንዲባርክለት ወደ ላይ ያንጋጥጣል። «እኔ ተከልሁ፤ አጵሎስ አጠጣ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር» በማለት ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስ ተማረ። ፩ቆሮ.፫፥፮። መትከልና ማጠጣት ምክንያቶች መሆናቸውን ማስተዋል ይገባል። ዋናው አሳዳጊው እግዚአብሔር ነው። ሐዋርያው ይህንን ሲያገናዝበን «እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ ቢሆን አንዳች አይደለም» ብሏል።

በዚህም የእግዚአብሔር ቸርነት ዋናውና መሠረት እንደሆነ ገልጧል። የሚያሳድግ እግዚአብሔር ነው ብሎ ግን ከመትከልና ውኃ ከማጠጣት መታቀብ ክስረትን ያመጣል። እግዚአብሔር የሚያሳድገው የተተከለውንና ውኃ የሚጠጣውን እንደሆነ ልብ ማለት ያስፈልጋል።

እስራኤል ከአማሌቅ ጋር በሚዋጉበት ጊዜ ኃይል፤ ጽን ይሆናቸው ዘንድ ሙሴ እጁን ወደ እግዚአብሔር ዘረጋ፤ የእግዚአብሔር ኃይል መገለጫ ይሆን ዘንድ ኢያሱ ደግሞ ዘገር ነጥቆ ጋሻ መክቶ ተነሳ።

የተዘረጋው የሙሴ እጅ ኃይል ከእግዚአብሔር ለኢያሱ እንዲሰጥ አደረገ። የእግዚአብሔር እጅ በኢያሱ ተገልጣ አማሌቅን ድል አደረገች። ለድሉ የሁለቱ ጽምረት ወሳኝ ነበረ። የሙሴ ጸሎት፤ የኢያሱ ሰልፍ ሥሙር ሆኖ ለድል በቁ። ዘጸ.፲፯፥፰–፲፫።

በእኛም ላይ ኃይለ እግዚአብሔር ይገለጥ ዘንድ እንደ ሙሴ በእምነት እጆችንን ወደ እግዚአብሔር መዘርጋት፣ እንደ ኢያሱ ደግሞ ጠላታችንን የምንዋጋበት መንፈሳዊ መሳሪያ (ስግደት፣ ጦም ሌላም ገድል) መታጠቅ በዚህ ጊዜ ጠላታችንን ዲያብሎስን ድል እናደርገዋለን።

ዳዊት ጎልያድን ድል ያደረገው ስሙን ብቻ በመጥራት ነው? አልነበረም። በእግዚአብሔር ታመነ (የእምነትን ሰይፍ ታጠቀ)፤ ጎልያድን «አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለህ» አለው የጎልያድ መታመኛው ሰይፉና ጦሩ እንዲሁም ጉልበቱ ነበር። «እኔ ግን ዛሬ በተገዳደርኸው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ» አለው። የዳዊት መታመኛው ደግሞ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነበር።

ግን በእግዚአብሔር ብቻ ታምኖ እጁን አጣምሮ ጎልያድን አልጠበቀውም። እግዚአብሔር ለሁሉ ነገር ቸርነቱ ኃይሉ የሚገለጥበት ምክንያት ይሻልና ወደ ወንዝ ወርዶ አምስት ድቡልቡል ድንጋዮች መርጦ በእረኛ ኮረጆው በኪሱ ከተተ። ወንጭፉንም አዘጋጀ። ጎልያድ እየፎከረ ሲመጣ ዳዊት ከኮረጆው ኪስ ድንጋዩን አውጥቶ በወንጭፉ ኩቶ ወደ ጎልያድ ወረወረ። ያቺ ድንጋይ ጎልያድ ግንባር ላይ ሄዳ ተመሰገች። ጎልያድም እንደ ግንድ ተገንድሶ ወደቀ። ዳዊት በእግዚአብሔር ኃይል፣ በወንጭፍዋ ባስፈነጠራት ድንጋይ ሳር ቅጠሉ ያረግድለት፣ እስራኤል ስሙ ሲጠራ ያንቀጠቅጣቸው የነበረውን የፍልስጤም መመኪያና መኩሪያ የነበረውን ጎልያድን ድል አደረገው። ፩ኛ ሳሙ.፲፯፥፴፯—፶፩።

ስለዚህ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ምሕረት ምክንያት የሚሆን ተግባር መሥራት ይጠበቅብናል። ዝግጅት ከእኛ፣ ውጤት ደግሞ ከአምላካችን ነውና።

## መንፈሳዊ ተጋድሎ በየትኛው አኗኗር?

በክርስትና ሕይወት ሁለት ዓይነት አኗኗር አለ። በሥጋ ወደሙ በሥርዓተ ተክሊል በቅዱስ ጋብቻ ተወስኖ መኖርና ወይም አንድ ልብ አንድ ሐሳብ ሆኖ እግዚአብሔርን በማገልገልና እሱን ብቻ በማሰብ ተወስኖ መላእክትን በመምሰል ከዓለማዊው ተድላ ደስታ ተለይቶ በምንኩስና መኖር።



በምንኩስና ከዓለም መለየት ሲባል ሰው መሆንን መርሳት ወይም መተው ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። ዳሩ ግን መነኮሳት ከሰብአ ዓለም ይልቅ ለዝህች ዓለም ፍትወት ራሳቸውን የገደሉ መሆን አለባቸው። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ «ዓለም በእኔ ዘንድ የሞተ ነው እኔም በዓለም ዘንድ የሞትኩ ነኝ።» ያለው። ገላ.፮፥፲፬።

መንኰሰ ማለት ሞተ ማለት ነው። ይህም ከዓለማዊ ግብር መለየትን፣ የሥጋን ፈቃድ መግደልና በነፍስ ፈቃድ መመራት ማለት ነው። «ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?» በማለት ሐዋርያው ለኃጢአት ሥራ ብልቶቻቸውን የገደሉ እንደሆነ ያስገነዝባል። ሮሜ.፮፥፪።

የድንግልናን ወይም የምንኩስንና ሕይወት የሚነቅፉና እንዲውያም ሕገ እግዚአብሔርን እንደ መጣስ የሚቆጥሩ አሉ። ዳሩ ግን ነቢዩ ኤልያስ፣ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ፣ እንዲሁም ዮሐንስ ወንጌላዊ በድንግልና ሕይወት የተወሰኑ እንደ ነበሩ ሳያውቁ ቀርተው ይሆን ወይስ ሰይጣን ዓይነ ኅሊናቸውን ጋርዶባቸው?

የአሕዛቡ መምህር የቤተ ክርስቲያን የአጥቢያ ኮከብ ቅዱስ ጳውሎስ «ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁ» ያለው በድንግልና ጸንቶ ሊኖር እወዳለሁ ማለቱ እንደሆነ አልተረዱ ይሆን? ፩ቆሮ.፯፥፯።

ዳሩ ግን ይህ ለሁሉ አይቻልም። ለተመረጡ እንጂ። ጌታም «ይህ ነገር ለተሰጣቸው እንጂ ለሁሉ አይደለም። በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ። ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ። ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ።» በማለት አስተምሯል። ማቴ.፲፱፥፲፩—፲፪።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጥያቄ በገዳም ድምፀ አራዊትን ፀብዐ ጋንንትን ታግሰው በተጋድሎ የሚኖሩ ባህታውያን ከእግዚአብሔር ጸጋ ርቀው በራሳቸው ተጋድሎ ሊጸድቁ የሚሹ በመሆናቸው ከእግዚአብሔር ቃል የወጡ ናቸው የሚለው አባባል ነው። ይህ ፍጹም

ከእውነት የራቀና የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚቃረን ነው። ሰዎች ሥጋቸውን ጎስመው ለንፍሳቸው ለማስገዛት የሚያደርጉትን ሁሉ እግዚአብሔር አይቃወምም። እንኳንስ ራሱ አብነት የሆነበትን ገዳማዊ ሕይወት ቀርቶ ሌላውንም ቢሆን አይነቅፍም።

በገዳም መወሰንና ራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛት እንደሚገባ አብነት የሆነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እንደ ተጠመቀ ልዋል ልደር ሳይል ወዲያው ገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ ከዘረጋበት ሳያጥፍ ከቆመበት ሳይቀመጥ ዐርባ መዓልትና ዐርባ ሌሊት በጦም በጸሎት ተወስኗል።

አባቶቻችንም ይህንን የጌታን ምሳሌነት ተከትለው በገዳም ቦታ ወስነው በጾም በጸሎት ተጠምደው ከእኩያን አጋንንት ጋር ሲፋለሙ ይኖራሉ። ማር.፩፥፲፪–፲፫።

ስለዚህ በብህትውና ጸንቶ መኖር ከፍ ያለ ዋጋ የሚያሰጥ እንጂ ዓለምንና የዓለምን ፍላጐት ወደው ሆዳችን ይሙላ፣ ደረታችን ይቅላ የሚሉ ሥጋውያን እንደሚያናፍሱት አይደለም።

እንዲህማ ቢሆን ኖሮ ከዓለም ርቀው ንጽሕ ጠብቀው በደብር ቅዱስ ይኖሩ የነበሩ ደቂቀ ሴት የእግዚአብሔር ልጆች ባልተባሉ ነበር። ዘፍ.፮፥፩–፬። መጽ.ሄኖክ.፪፥፩።

ከዓለማዊ ግብር ተለይተው ሃይማኖትን ከምግባር ጋር አስተባብረው ይዘው ከተገኙ ባይመነኵሱም ፍጹምነት በጋብቻ ላሉትም ይሰጣል። ለዚህም አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ኢዮብ፣ ዓይነተኛ ምሥክር ናቸው።

ስለሆነም በምንኵስናም ሆነ በጋብቻ የተወሰኑ ሁለቱም በገድል ውስጥ ያሉ ናቸው። በመነኮሳት ላይ ግን ይበልጥ ይጸናል።



ምዕራፍ አራት

# የምግባር አስፈላጊነት

«ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ ሁሉ ከሥራ የተለየ እምነትም የሞተ ነው።» ያዕ.፪፥፳፮። እምነት አለኝ የሚል እምነቱን ግን በሥራ የማይገልጥ ሰው ከንቱ ነው። እምነቱ ለድኅነት አያበቃውም። «መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል።» ማቴ.፫፥፲። እንደ ተባለው ሁሉ እርሱም ፍሬ– ምግባር አፍርቶ አልተገኘምና ከፈጣሪው አንድነት ተለይቶ ወደ ዘላለም እሳት ባሕር ይጣላል።

## በክፉ አድራጊዎች ላይ ይፈረድባቸዋል

እምነት አለኝ በማለት ምግባረ ቢስ ሆኖ ባዶ ጩኸት ማሰማት ለምንም አይጠቅምም። «የአብርሃም ልጆች ነን» እያሉ ይመጻደቁ ለነበሩት አይሁድ ልዑለ ባሕርይ አምላክ «የአብርሃም ልጆችስ ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር» የሚል መልስ ነው የሰጣቸው። ዮሐ.፰፥፴፱።

ክፉ ሥራ የሚሠራ ሁሉ የክፋት ምንጭ የሆነው የዲያብሎስ የግብር ልጅ ነው። ዲያብሎስ በክፉ ሥራው እንደ ተፈረደበት ሁሉ ክፉ አድራጊዎችም ንስሐ እስካልገቡ ድረስ ከእግዚአብሔር ፍርድ አያመልጡም።

ሥራቸው ክፉ የሆነ ሰዎች የመጨረሻ ዕጣ ምን እንደሆነ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስተምር:-

- «ይህን እወቁ አመንዝራም ቢሆን ወይም ርኵስ ወይም የሚመኝ እርሱም ጣኦትን የሚያመልክ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም። ከዚህ የተነሣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣልና።» ኤፌ.፭፥፭–፮።
- «ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግስት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፣ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን

የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።» ፩ቆሮ.፮፥፱–፲፩። «የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው። እርሱም ዝሙት፣ ርኵሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ ይህንንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፣ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።» ገላ.፭፥፲፱–፳፩።

- «ሴሰኞችንና አመንዝሮችን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።» ዕብ.፲፫፥፬።
- «እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል። በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለም ሕይወት ይሰጣቸዋል። ለዓመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በአድመኞች ላይ ግን ቁጣና መቅሠፍት ይሆንባቸዋል። ክፉውን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል። ሮሜ.፪፥፮–፲፩። «ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል። በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉም።» ሮሜ.፪፥፲፪–፲፮።
- «እንግዲህ በምድር ያሉትን ብልቶቻችሁን ግደሉ፣ እነዚህም ዝሙትና ርኵሰት፣ ፍትወትም፣ ክፉ ምኞትም፣ ጣዖትንም ማምለክ የሆነ መጐምጀት ነው። በእነዚህም ጠንቅ የእግዚአብሔር ቁጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ ይመጣል።» ብሏል። ቆላ.፫፥፭–፲፩።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም ትዕዛዘ እግዚአብሔርን በሚተላለፉ ሰዎች ላይ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ ሲያስረዳ:-

- «ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ተነሥቶ የሚጀምርበት ጊዜ ደርሶአልና። አስቀድሞም በእኛ የሚጀምር ከሆነ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን? ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመፀኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው?» ፩ጴጥ.፬፥፲፯–፲፱።



- «እግዚአብሔር ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት ሳይራራላቸው ወደ ገሃነም ጥሎ በጨለማ ጉድጓድ ለፍርድ ሊጠበቁ አሳልፎ ከሰጣቸው፣ ለቀደመውም ዓለም ሳይራራ ከሌሎች ሰባት ጋር ጽድቅን የሚሰብከውን (በምግባሩ) ኖኅን አድኖ በኃጢአተኞች ዓለም ላይ የጥፋትን ውኃ ካወረደ፣ ኃጢአትንም ያደርጉ ዘንድ ላሉት ምሳሌ አድርጎ ከተማዎችን ሰዶምንና ገሞራን አመድ እስኪሆኑ ድረስ አቃጥሎና ገልብጦ ከፈረደባቸው፣ ጻድቅ ሎጥም በመካከላቸው ሲኖር እያየና ጻድቅ ነፍሱን አስጨንቆ ነበርና። በዓመፀኞች ሴሰኛ ኑሮ የተገፋውን ያን ጻድቅ ካዳነ፣ ጌታ እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን (ሕጉንና ትዕዛዙን በመጠበቅ) ከፈተና እንዴት እንዲያድን፣ በደለኞችንም ይልቁንም በርኵስ ምኞት የሥጋን ፍትወት እየተከተሉ የሚመላለሱትን ጌትነቱንም የሚንቁትን እየቀጣቸው ለፍርድ ቀን እንዴት እንዲጠብቅ ያውቃል።» ፪ጴጥ.፪፥፬–፲።

ባለቤቱም በሥጋ ተገልጦ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ እምነት አለን እያሉ ፍሬ ምግባር የሌላቸው ሰዎች እንደማይድኑ ሲያስተምር «መልካም ፍሬ የማያደርግ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል...በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።» ማቴ.፯፥፲፱–፳፩። ብሏል።

«የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፣ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፣ ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል። በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።» ማቴ.፲፫፥፵፩።

በመጨረሻው የፍርድ ቀን ጌታ ለፍርድ ሲመጣ መልካም ሥራ ያልሠሩትን እንዲህ ሲል ይፈርድባቸዋል። «እናንተ ርጉማን፣ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ። ተርቤ አላበላችሁኝምና፣ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፣ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፣ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፣ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና።» ማቴ.፳፭፥፵፩–፵፫።

## መልካሙም ሆነ ክፉ ሥራችን እስከ መጨረሻው ይከተለናል

ሁሉም የዘራውን ያጭዳል። ሳይሰሩ መከበርም አይቻልም። ጌታም ለእያንዳንዱ እንደሥራው ዋጋውን ይከፍለዋል። «እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።» ብሏልና። ራእይ.፳፪፥፲፪።

ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊትም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት «አንተ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ፍዳውን ትሰጣለህና» በማለት ጌታ ለሁሉም የሥራውን ዋጋ እንደሚሰጥ ተናግሯል። መዝ.፷፩(፷፪)፥፲፪።

ጌታም በዘመነ ስብከቱ «የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና። ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል።» በማለት አስተምሯል። ማቴ.፲፮፥፳፯።

«በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል። መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ፤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ።» በማለትም አስገንዝቧል። ዮሐ.፭፥፳፰ና ፳፱።

መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን ሁሉም የሥራውን ውጤት እንደሚያገኝ ሲያስረዳ «እግዚአብሔርን ፍራ ትእዛዙንም ጠብቅ። እግዚአብሔር ሥራን ሁሉ የተሰወረውንም ነገር ሁሉ፤ መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን ወደ ፍርድ ያመጣዋልና።» ብሏል። መጽ.መክ.፲፪፥፲፫ ና ፲፬።

ስለዚህ ክፉዎች እንደ ሥራቸው ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቅጣትን ሲቀበሉ በጎ አድራጊዎች ደግሞ የዘላለም ሕይወትን ያገኛሉ። «እናንተ የአባቴ ቡሩካን፤ ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ። ተርቤ አብልታችሁኛልና፤ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፤ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፤ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና...» ማቴ.፳፭፥፴፭–፴፮።

«ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ። መጻሕፍትም ተከፈቱ። ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ። እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው። ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ።» ራእይ.፳፥፲፪–፲፫።



«በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው። መንፈስ አዎን ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ ሥራቸውም ይከተላቸዋል ይላል» ራእይ.፲፬፥፲፫።

## የሃይማኖት መግለጫ ምግባር ነው

የቤተ ክርስቲያን የአጥቢያ ኮከብ ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈስ ልጁ ቲቶ በላከው ክታቡ «እግዚአብሔርንም የሚያምኑት በመልካም ሥራ በጥንቃቄ እንዲጸኑ፤ እነዚህን አስረግጠህ እንድትናገር እፈቅዳለሁ» በማለት የክርስቲያኖች መለያ መታወቂያቸው መልካሙ ሥራቸው መሆኑን አስገንዝቦታል።ቲቶ ፫፥፰።

ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ እንደሆነ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ሲያስረዳ «እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን?...ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።» ብሏል። ያዕ.፪፥፲፬–፳፮።

እምነት አለን እያሉ በክፉ ሥራ ተጠምደው የሚገኙ የእምነትን ካባ ለብሰው የሚያታልሉ አጭበርባሪዎች መሆናቸውን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል ተናግሯል። «የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን፤ ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል (ሃይማኖት ያለውም ሰው መልካም ምግባር ይኖረዋል)። ክፉም ዛፍ– ክፉ ፍሬ ያደርጋል። መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም።» ማቴ.፯፥፲፭–፳።

## ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ መልካም ሥራን ያደርጋል

ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ– ከማኅፀነ ዮርዳኖስ የተወለዱ ክርስቲያኖች ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና የአባታቸውን ትዕዛዝ ሊያከብሩና ሊጠብቁ ይገባቸዋል።

«በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።» ተብሎ እንደ ተጻፈ። ሮሜ.፰፥፲፬። እግዚአብሔር

የሚወደውን የሚያደርጉ ሁሉ በሥራቸው የማን ልጆች እንደሆኑ ይመሰክራሉ።

«ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፤ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔር ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም።» እንደተባለው በሃይማኖት ውስጥ ያለ ሰው ክፉ ሥራ ሊሠራ አይገባውም።

«...የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው» እንዳለው በወልድ ውሉድ፣ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኙ ሁሉ በመልካም ሥራቸው ክፉ ከሚያደርጉ ከዲያብሎስ ልጆች ይለያሉ።

«...ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤» 1ዮሐ.፫፥፱።

በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ እያለ መልካም ሥራ የማይሠራ ሁሉ በአይሁድ ይመሰላል። እነርሱ የአብርሃም ልጆች ነን እያሉ በከንቱ ይመጻደቁ ነበርና። ጌታ ግን «የአብርሃምስ ልጆች ከሆናችሁ የአብርሃምን ሥራ «ሥሩ» ነበር ያላቸው።» ዮሐ.፰፥፴፱። ከእግዚአብሔር በመንፈስ የተወለደም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይጠብቃል። «ብትወዱኝስ ትዕዛዜን ጠብቁ» ብሏልና። ዮሐ.፲፬፥፲፭።

ክፉ አድራጊዎች ግን «እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ። የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ።» ተብለዋል። ዮሐ.፰፥፵፬።

«ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም» እንደተባለው ፩ዮሐ.፫፥፲። በወንድሙ ላይ ክፋትን የሚያስብና የሚያደርግ የእግዚአብሔር ልጅ ሊሆን አይችልም።

ምግባራቸው መጥፎ ሆኖ በሃይማኖት እንኖራለን የሚሉትን ሰዎች መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ከፈሪሳውያን ጋር ደምሮ «እናንተ የእፉኝት ልጆች» ብሏቸዋል። ማቴ.፫፥፯።

## ሃይማኖት በምግባር ፍፁም ይሆናል

«አንተ ከንቱ ሰው፣ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን? አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን



በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ፤ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን? መጽሐፍም አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ። ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ» ያዕ.፪፥፳-፳፬።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ እንዳስተማረን እምነት ፍጹም የሚሆነው በምግባር ነው። ሃይማኖትና ምግባር ሊለያዩ አይችሉምና።

ከመልካም ምግባር ጋር የተዋሐደ ሃይማኖት ሰውን ለጽድቅ እንደሚያበቃው ሲያስረዳም:- «አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሚመስለው ማንም ቢኖር የእርሱ አምልኮ ከንቱ ነው። ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው። ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፤ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነትን መጠበቅ ነው» ብሏል። ያዕ.፩፥፳፮-፳፯።

ሐዋርያው የምግባርን አስፈላጊነት በአጽንኦት ሲያስገነዝብም «እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው።» ብሏል። ያዕ.፬፥፲፯።

## በጎ ሥራ የሚሠሩ በብርሃን ይመላለሳሉ

የጌታ ወዳጅ የሚባለው ዮሐንስ «እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም።» በማለት በዘመኑ የነበሩ መናፍቃን «አንድ ጊዜ ካመኑ ከተጠመቁ ሌላ ምን ምግባር ያስፈልጋል?» እያሉ ምእመኑን ግራ ያጋቡት ስለ ነበር ለእነዚህ መናፍቃን ምላሽ ሲሰጥ ከላይ የተጠቀሰውን ተናገረ።

የእግዚአብሔር ነን እያሉ መጥፎ ሥራ መሥራት እንደማይገባም ሲያስገነዝብ «ከእርሱ ጋር አለን ብንል በጨለማም (በመጥፎ ምግባር) ብንመላለስ እንዋሻለን፤ እውነትንም አናደርግም፤ ነገር ግን እርሱ በብርሃን (በጽድቅ) እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ፤ ለእያንዳንዳችን

አንድነት አለን። የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።» ፩ዮሐ.፩፥፫–፯።

ሐዋርያው እንዳስተማረን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን የሚያነጻን ከመጥፎ ምግባር ተላቀን ንስሐ ገብተን በመልካም ሕይወት ውስጥ ስንኖር ነው። እርሱ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥራው ሁሉ ጻድቅ እንደሆነ በእርሱ የምናምን ክርስቲያኖችም በሃይማኖትና በምግባር ልንኖር ይገባናል።

በብርሃን (በኢየሱስ ክርስቶስ) ፈቃድ የሚኖሩ እንደ ሥጋ ፈቃዳቸው አይመላለሱምና። በፈቃደ እግዚአብሔር ይኖራሉ እንጂ። «የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ» እንዳለ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ። ገላ.፭፥፳፬።

## ማጠቃለያ

- እግዚአብሔርን የሚወድ በእርሱም የሚታመን ትዕዛዛቱን ይጠብቃል። «ብትወዱኝ ትዕዛዜን ጠብቁ» ብሎ ባለቤቱ እንደ ነገረን። ዮሐ.፲፬፥፲፭።
- ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም በመልእክቱ «እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚህ እናውቃለን። ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና። ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም።« ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና» ፩ዮሐ.፭፥፪–፬።

«ትእዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን። አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው። እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም።» ፩ዮሐ.፪፥፫ና፬።

- ጌታም «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል...የማይወደኝ ቢኖር ቃሌን አይጠብቅም።» በማለት ትእዛዙን የሚጠብቁት የሚወዱት መሆናቸውንና ጸጋውንም የሚያድለው ለእነርሱ እንደሆነ ተናግሯል። ዮሐ.፲፬፥፳፫ ና ፳፬።



- አንድ ሕግ አዋቂ ወደ ጌታ ቀርቦ «መምህር ሆይ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ?» ሲል ጠየቀው። ጌታም ሲመልስለት «ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ትዕዛዛትን ጠብቅ» አለው። ሰውየውም መልሶ «የትኞቹን?» ሲል ጠየቀው። ጌታም «አትግደል፤ አታመንዝር፤ አትስረቅ፤ በሐሰት አትመስክር፤ አባትህንና እናትህን አክብር፤ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ።» በማለት የዘላለም ሕይወትን የሚያገኘው በእምነት ብቻ ሳይሆን ሕግጋትን በመጠበቅም እንደሆነ አስረድቶታል። ማቴ.፲፱፥፲፮–፳።

ለእኛስ ከዚህ የተለየ መመሪያ ተሰጠን? አይደለም። የተጻፈው ሁሉ ለምክርና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት ለሁላችን ተጻፈ እንጂ።

ስለሆነም ሰው ሁሉ በእውነተኛይቱና በቀናችይቱ ሃይማኖት አምኖ ሕግጋትን በመጠበቅ የዘላለም ሕይወትን እንደሚያገኝ ተገንዝበናል። ከዚህ አልፎ ከሕግ አንዲቱን ትንሽ ናት ለጽድቅም አታስፈልግም ብሎ የሚያስተምር ቢኖር በመንግሥተ ሰማይ የሁሉ ታናሽ ይባላል። ማቴ.፭፥፲፱።

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሐንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

# መጽደቃችንን በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን?

ነገ የሚሆነውን የማያውቅ ሰው ስለ መጽደቁ በእርግጠኝነት መናገር እንዴት ይቻለዋል? ዛሬ ቅዱስ የተባለው ነገ ርኩስ ሊባል ይችላል። ቀን የሚያመጣውን አታውቅምና ዛሬ በሆነው ነገር አትመካ የሚለው ቃልም የሚያስገነዝበን ይህን እውነታ ነው።

ክርስትና የትሕትና ሕይወት ነው። ትሕትናን ገንዘብ ያደረገ ሰው ደግሞ ስለ ራሱ አይናገርም አይመጻደቅም። እንኳን ስለ ዘላለማዊው መንግስት ስለ ምድራዊ ሕይወቱም በእርግጠኝነት አይናገርም። ስለ ራሱ የሚናገረው ቢኖር ደካማነቱን ብቻ ነው። ለዚህም ነው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «እኔ ትል ነኝ» ያለው።

ዛሬ ግን በዓለም የፍትወት ማዕበል ተውጠው የሚዳክሩ ሥጋውያን የጽድቁን መንገድ ገና ሳይዙ «ጸድቀናል የእግዚአብሔርን መንግሥት እጅ አድርገናል» እያሉ ያለ ምንም እፍረት በድፍረት ሲናገሩ እየሰማን ነው።

ለመሆኑ አንድ ሰው በዚህ ምድር ላይ እያለ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረሱ እርግጠኛ ሊሆን ይችላልን? መልሱ አይችልም ነው። ነገር ግን የዘመናችን ቢጽሐሳውያን በትዕቢት መንፈስ ተወጥረው «ድነሃል ወይስ አልዳንክም?» የሚል መጠይቅ ማቅረብ ከጀመሩ ዋል ከረም ብለዋል። ለዚህ የኦርቶዶክሳውያን መልስ ምንድር ነው?

መልሳችን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ የቅዱሳንን ሕይወትና የሰውን ልጅ ደካማ ባሕርይ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል።

## ድነሃልን?

ያለምንም ማመንታት በእርግጠኝነት «የመጀመሪያውን ድኅነት» እንዳገኘን እንናገራለን። የመጀመሪያው ድኅነት የቱ ነው?



የሁላችን አባትና እናት አዳምና ሔዋን በምክረ ከይሲ ተታለው ትእዛዘ እግዚአብሔርን ጣሱ። በለስም በሉ። በዚህም የተነሣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ጽኑ የጠብ ግድግዳ ተጋረደ። አዳምና ሔዋንም ጸጋቸው ተገፎ ከርስታቸው ከገነት ተባረሩ። የዘላለም ሞትም ተፈረደባቸው።

ይህ በአዳምና በሔዋን ላይ የተፈረደው ፍርድ ከአዳም አብራክ ተከፍለው ለሚወለዱ ሁሉ የሚተላለፍ ሆነ። ስለዚህ የሰው ልጅ ሁሉ በደለኛ ኃጢአተኛ ሆነ። የጉስቁልናን ሕይወትም ለ፭ሺህ፭፻ ዘመን ገፋ።

ቸር ፈጣሪያችን አዳምና ልጆቹን ከዚህ ሕይወት ሊያወጣ አምላካዊ ጉዞ አደረገ። አዳም በበደለው ሁሉ ካሳን ይክስ ዘንድ ከድንግል እናታችን ከቅድስት ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ተዋሕዶ ሰው ሆነ።

ከድንግል መሬት ተፈጥሮ ለበደለው አዳም ይክስ ዘንድ በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከእመቤታችን ተወለደ። ከገነት የተሰደደውን አዳም ወደ ገነት ይመልስ ዘንድ ወደ ግብጽ ተሰደደ። በዮርዳኖስ የተጣለውን የአዳምን የዕዳ ደብዳቤ ይደመስስ ዘንድ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ። እርቃኑን የቀረውን አዳምን የጸጋ ልብስ ያለብሰው ዘንድ እርቃን ሥጋውን በመስቀል ላይ ዋለ። ዘፍ.፫፥፯። ማቴ.፫፥፲፫። ማቴ.፳፯፥፳፯–፴፩።

አዳምና ሔዋን የሰይጣንን ምክር በጆሮቻቸው ሰምተው፣ በዓይናቸው እፀ በለስን አይተው፣ በልባቸው ተመኝተው፣ በእግራቸው ተራምደው፣ በእጃቸው ቀጥፈው፣ በአፋቸው አላምጠው ባመጡት ኃጢአት፣ ጌታ ካሳን ይከፍል ዘንድ «ስቀለው፣ አስወግደው» የሚለውን የአይሁድ ጩኸት ሰማ። ዮሐ.፲፱፥፲፭።

በዓይኑም ግርማ አይሁድን ተመለከተ፣ እጅና እግሩን ተቸነከረ፣ በአፉ መራራ ሐሞትን ተጎነጨ፣ መዝ.፳፩፥፲፯–፲፰። ዮሐ.፲፱፥፴። ይህን ሁሉ ማድረጉ ለአዳም የገባውን ቃል ኪዳን እንዲሁም በነቢያት የተነገረውን ትንቢት ይፈጽም ዘንድ ነውና። ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ሕዝቡንም ከዲያብሎስ አገዛዝ፣ ከተያዝንበት የመርገም ቀንበር ያላቅቀናል ብለው የተናገሩት ትንቢት እነሆ በዚህች ሰዓት «ተፈጸመ»። ነፍሱንም በገዛ ፈቃዱ ሰጠ። ዮሐ.፲፱፥፴።

እርቅን ፈጸመ፣ የጠብ ግድግዳ ፈረሰ፣ ሰው ከፈጣሪው ጋር ታረቀ፣ የመርገም ድንጋይ ከላዩ ተነሣለት። ከባርነት ነፃ ወጣ። «በነፃነት እንኖር ዘንድ ክርስቶስ ነፃ አወጣን ዳግመኛ በባርነት እንዳትያዙ» ያለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለዚህ ነው።

ስለዚህ ከቀደመው (ከመጀመሪያው በደል) በክርስቶስ ቤዛነት ድነናል። ያለንበትም ዘመን የምሕረት ዘመን ነው። ዓመተ ፍዳ አልፏል። የዘላለም ሕይወት የሚገኝበት መንግሥቱን እንድንወርስ የመግቢያውን በር አሳይቶናል። በጥምቀት መንግስቱን የምንወርስበት የልጅነት ጸጋን አግኝተናል። የምንጸድቅበትን መንገድ አሳይቶናል። አሁን ለመጽደቅ የእኛን ፈቃድና ጽናት የሚጠይቅ ቢሆንም ለመጽደቃችን ግን እርግጠኛ ሆነን መናገር አንችልም። ሁሉም ነገር በቸርነቱ ብዛት እንጂ በእኛ ሥራ ብቻ የሚሆን ባለመሆኑ ነው።

ይህ ዓለም የጦርነት ቦታ ነው። እንደ ወርቅ በእሳት (በመከራ) ተፈትነን ነጥረን የምንወጣበት። መጋደላችን ደግሞ ከሥጋና ከነፍስ ጋር አይደለም። ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር እንጂ። ኤፌ.፮፥፲፪። «እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል አቀዳጅሃለሁ።» ራእይ.፪፥፲፩።

እስከ መጨረሻዋ የሕይወታችን ፍጻሜ የታመን እንደምንሆን ምን ያህል እርግጠኞች ነን? ይህ በአምላካችን እንጂ በእኛ አይታወቅም። ምክንያቱም ጉዞውን ጀምሮ በመንገድ ላይ የሚያቋርጥ ይኖራልና። ለዚሁም የዴማስን ታሪክ ዓይነተኛ ምስክር አድርገን ልንወስድ እንችላለን። ፪ጢሞ.፬፥፲።

ይህች ዓለም እንደ ዴማስ ማርካው ሆዴ ይሙላ ደረቴ ይቅላ ብሎ የድኅነትን መንገድ ለቆ የጥፋትን ጐዳና የሚመርጥ ሊኖር ይችላል? ማን የወደፊቱን ሊያውቅ ይችላል?

ዛሬም ቢሆን «ድኛለሁ:- የእግዚአብሔርን መንግስት እጅ አድርጌያለሁ» እያሉ ይፎክሩ የነበሩ ብዙ ሰዎች በሥጋ ፍላጐት ተጠላልፈው የዲያብሎስ ምርኮኛ ሆነው በዓለም በረሃ ላይ ወድቀው አስተውለናቸዋል። «ሳይገሉ ጐፈሬ...» እንዲሉ አስቀድመው ስለራሳቸው የተናገሩትን ገና በዚህችው ምድር አየንላቸው።



እንዲህ ዓይነቱ ትምክህት ከዲያብሎስ እንጂ ከእግዚአብሔር የተገኘ ባለመሆኑ ማንም ሰው ሊከተለው አይገባም። ኃጢአት በሰፈነበት ዓለም እየኖሩ የኃጢአት ተገዢም ሆኖ «ድኛለሁ...» እያሉ መናገሩ ትዝብት ላይ ይጥላል። «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም» ፩ዮሐ.፩፥፱።

በኃጢአት ውስጥ ካለን ደግሞ በደለኞች ነን። በደለኛ ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም። ምክንያቱም «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና» ታዲያ በየትኛው ብቃታቸው ነው ጸድቀናል የሚሉት። እንዲህ ሲሉ ኃጢአት የለብንም፣ አንሰራም የበቃን የነቃን ነን ማለታቸው ይሆን? ይህን ይሉስ ዘንድ እነርሱ እነማን ናቸው? እንኳን እውነተኛዋን ሃይማኖት ያልያዙ እነርሱ ቀርተው በእውነተኛዋ ሃይማኖት የነበሩ ከመንፈስ ቅዱስም ጸጋ ተካፋዮች የሆኑ መሳታቸውን ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ገልጾታል። «አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን፣ ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን፣ ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን፣ መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን በኋላም የካዱትን...» ዕብ.፮፥፬–፮።

አንተስ እውነተኛው ብርሃን እንኳን ቢበራልህ ልትስትና ልትክድ፣ ከጸጋው ልትወጣ እንደምትችል አስተዋልክን? «የእውነትን መንገድ በቀና ልቡና ሆነህ ፈልግ እንጂ አትታበይ። ትዕቢት ዲያብሎስንም ከክብሩ አውርዶታልና።»

የእግዚአብሔርን ምኅረት ተስፋ የምናደርግ ኦርቶዶክሳውያን ስለ ወደፊቱ ሕይወታችንም በራሳችን ማስተዋል አንደገፍም። ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር ነውና። ዳሩ በእርግጠኝነት አንናገርም። ሁሉን የሚያውቅ እግዚአብሔር ነውና። ዳሩ ግን ለጽድቅ የሚያበቃውን ሁሉ እንደአምላካችን ትእዛዝ እንፈጽማለን «የሚያጸድቅ የሚኮንን እርሱ» ሁሉን እንደፈቃዱ ያከናውነዋል።

ወደ ተስፋይቱ ሀገር ወደ ከነዓን ይገቡ ዘንድ ከግብጽ የተነሱትን ከስድስት መቶ ሺ በላይ የሆኑ እስራኤልን እናስታውሳለን። ሲነሱ ሁሉም ማርና ወተት ታፈልቃለች የተባለችውን ተስፋይቱን ሃገር ለመውረስ ነበረ። ዳሩ ግን ከግብጽ ከተነሱት ከ፮ መቶ ሺዎቹ ውስጥ ለተስፋይቱ

ሃገር የበቁት ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ። ኢያሱና ካሌብ። ሌሎቹም በቃዴስ በረሃ ላይ በጥፋታቸው ወድቀው ቀሩ።

ዛሬም ወደ ተስፋይቱ ሃገር ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ለመግባት ብዙዎቻችን ጉዞ ጀምረናል በዓለም በረሃ ላይ ወድቀው የሚቀሩትንና ለተስፋይቱ ሃገር ለመንግሥተ ሰማያት የሚበቁትን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

እና «ጸድቂያለሁ» በሚል የትዕቢት ገመድ የተወጠርክ አንተ ትጠራ ዘንድና በመንገዱ ትጓዝ ዘንድ አስቀድመህ ሃይማኖትን ያዝ ከዚያም ጉዞህን በማስተዋልና በትህትና ተጓዝ:- አምላክህን ብቻ ተስፋ አድርግ እንጂ መንግስቱን ለመውረስህ እርግጠኛ ሆነህ አትናገር:- የተመረጠው ሙሴ እንኳን ተስፋይቱን ሃገር እንዳልገባባት አስተውል። ዘዳ.፴፪፥፵፰–፶፪።

ምሕረቱንና ቸርነቱን እየተናገርህ እርሱን ደጅ ጥና እንጂ የትእቢትን ነገር ከቶ አትናገር። ይህን ሁሉ ንቀህ በራስህ ማስተዋል ተደግፈህ «የምትመጻደቅ ከሆንህና ትእቢትና መታጀርን ገንዘብ እንድታደርግ በሚያስታጥቅህ በዲያብሎስ መንገድ መጓዝን ከመረጥክ «እሾህንና ኩርንችትን በልቡናህ እያበቀልክ ነውና የተጠላህ ለመርገምም የበቃህ ትሆናለህ መጨረሻህም መቃጠል ነው። ዕብ.፮፥፰።

## ሐዋርያው እርሱን እንድንመስለው አስተምሮን የለምን?

«ጸድቀናል› የሚሉ ክፍሎች ለዚህ የትዕቢት አነጋገራቸው አብነት አድርገናል የሚሉት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን ነው። ቅዱስ ጳውሎስ የዚህችን ዓለም ሩጫ በድል አድራጊነት በፈጸመባት በመጨረሻዋ ሰዓት ይህን ተናግሮ ነበር «ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ይህንንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል» ፪ጢሞ.፬፥፰።

ይህን መነሻ አድርገው እኛስ «ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልናል» እንል ዘንድ የሚያሳፍረን ምንድር ነው? ይላሉ።

ነገር ግን ይህን ስለተናገረው የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ልንጠይቅና ልናውቀው የሚገባን ነጥቦች አሉ።



### ሀ. ይህን የተናገረው ማን ነው?

ተናጋሪው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ምን ዓይነት ሰው ነበር? ማንነቱን ማወቅ ራሳቸውን ከእርሱ ጋር ላስተካከሉ ሰዎች ትምህርት ይሰጣልና የእርሱን ማንነት ማስተዋል ቅድሚያ ይሰጠዋል። ቅዱስ ጳውሎስ:- የክርስቶስን መከራ መስቀል በአፍ ሳይሆን በተግባር የተሸከመ ነው። ሞት ቢሆን ሕይወት ቢሆን ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ምንም ነገር የለም በማለት በመንፈሳዊ ተጋድሎ ሥጋውን እየጎሰመ ለፈጣሪው ያስገዛ:- አንገቱን ለሰይፍ ለስለት አሳልፎ የሰጠ ታላቅ መንፈሳዊ አርበኛ ነው። ገላ.፪፥፳፤ ሮሜ.፰፥፴፰።

- የበቃ የነቃ ከብቃቱ የተነሣ ዓለመ መላእክትን በመንፈስ ተነጥቆ የጎበኘ በዚያም ያለውን ሰማያዊ ምሥጢር፤ ሰው ሊናገር የማይገባውን የማይናገረውንም ቃል የሰማ ፍጹምነት ደረጃ ላይ የደረሰ ነው። ፪ቆሮ.፲፪፥፫።
- መንፈስ እግዚአብሔር ያደረበት መንፈስ ቅዱስ በጸጋው የጎበኘው ረቂቁንና ግዙፉን ዓለም፤ የተሰወረውንና የተደበቀውን ሁሉ የሚያውቅ። መጻዕያትን (ወደፊት የሚሆነውን) ያውቅ ዘንድ ሀብተ ትንቢት የተሰጠው ሐዋርያ ነው።

ይህን ሁሉ መንፈሳዊ ሀብት ገንዘብ ካደረገ ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ራሱን የሚያስተካክል ምን ዓይነት ሰው ነው? መንገዱን ያላወቀ ሩጫውን ያልጀመረ በግብዝነት ሕይወት የተሞላ ሰው «እኔም እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ነኝ ሊል ይቻለዋልን?

### ለ. ይህን የተናገረው መቼ ነው?

ሐዋርያው ይህን ቃል የተናገረው ገና በተጋድሎ ላይ እያለ አይደለም ሐዋርያው ይህን ቃል የተናገረው ገና በተጋድሎ ላይ እያለ አይደለም በዚያን ጊዜማ:- «አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን እንደተፈጸምሁ አይደለም፤ ነገር ግን ስለዚያ በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም የተያዝሁ ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ። ወንድሞች ሆይ እኔ ገና እንዳልያዝሁ እቆጥራለሁ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴም ወዳለው እየተዘረጋሁ፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ» ፊል.፫፥፲፪–፲፭።

ገና ለማግኘት ለመጽደቅ የሚሮጥ መሆኑን በግልጽ አስቀምጦልናል። እንግዲህ ምን ይለሉ ፍጹሙን ሃይማኖት በመያዝ በተጋድሎ የጸናው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ካለ ከምንም የማይቆጠሩት እነርሱ ራሳቸውን ሊያልታመጻድቁ ይቻላቸዋልን?

ፍጹማን ሁሉ በዚህች ምድር ላይ ሳሉ ራሳቸውን አያመጻድቁም ለመጽደቅ ይሮጣሉ እንጂ፣ አክሊሉን ተቀዳጅቸዋለሁ አይሉም። ሐዋርያውም «እንግዲህ ፍጹማን የሆንን ሁላችን ይህን እናስብ» በማለት ያስትምረናል። ዕብ.፫፥፲፫።

ጌታም «አቤቱ ወደ ፈተናም አታግባን» ብላችሁ ጸልዩ ያለውም ለዚህ ነው። ፍጹማን ከበቁ በኋላ ይህን ጸሎት ይጸልያሉ ገና ድል አላደረጉምና። ብቃታቸው ከእግዚአብሔር እንጂ ከእነርሱ አይደለምና። ፪ቆሮ.፫፥፭።

ዳሩ ግን ተጋድሎውን በእግዚአብሔር ቸርነት በድል አድራጊነት ከፈጸመ በኋላ እንደ ንጹሕ የመገበሪያ ስንዴ ራሱን ለክርስቶስ መስዋዕት አድርጎ ሊያቀርብ ወደ መሰዊያው ስፍራ ሊሄድ ሲል «መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫዬንም ጨርሻለሁ ሃይማኖቴን ጠብቂያለሁ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል» አለ። በሰማእትነት እንደሚያልፍ በማወቁ ነው «በመሥዋዕት እንደሚደረግ፣ የእኔ ሕይወት ይሰዋልና፣ የምሄድበትም ጊዜ ደርሶአል» በማለት አስቀድሞ የሚደርስበትን በተሰጠው ኃብተ ትንቢት አውቆት ተናግሯል። ፪ጢሞ.፬፥፮።

ቅዱስ ጳውሎስን አብነት አድርገን ነው የሚሉ እነርሱ እርሱን አብነት ያደርጉ ዘንድ እንደ እርሱ

- «እውነተኛዋን ሃይማኖት ይዘዋልን? እርሷንስ ጠብቀዋልን?
- መልካሙን ገድል ተጋድለዋል?
- ሩጫቸውንስ ጨርሰዋል?
- የወደፊቱ ክብራችውስ ተገልጦላቸዋል?! ሀብተ ትንቢት ተሰጥቸዋል?
- ይህን ለማለትስ ብቃቱ አላቸው?



እንግዲህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዘመኑ ፍጻሜ የተናገረውን ምሳሌ አድርገው እየጠቀሱ በከንቱ አይታበዩ እንኳን ሩጫቸውን ሊጨርሱ ገድልንም ሊጋደሉ ቀርቶ ሃይማኖትን እንኳን ገና አልያዙም። ሃይማኖትን ይያዙ ሩጫችውንም ይጀምሩ።

ደግሞም ሐዋርያው የእግዚአብሔርን ቸርነቱን መሠረት አድርጎ «ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል» አለ እንጂ ጸድቂያለሁ አለማለቱን ያስተውሉ።

«ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን...» ዕብ.፲፥፳ የሚለውን በመጥቀስ። «ጸድቀናል ብለን እናገር ዘንድ ድፍረቱ አለን ስለሚሉት።

እርግጥም ነው የሐዲስ ኪዳን ካህናት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ደም ይዘው ወደ መቅደስ የመግባት ባለሟልነት ተሰጥቷቸዋል። ይህንን ነው ድፍረት ያለው።

ኧረ ለመሆኑ «ጸድቀናል ለማለት ድፈረቱ አለን ሲሉ ምንን መሠረት አድርገው ነው? ድፍረቱ አለኝ የሚል ሁሉ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል።

## ፩. ከኀሊና ወቀሳ ነፃ መሆን።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እንዲህ ይላል «ወዳጆች ሆይ፣ ልባችንስ ባይፈርድብን በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት አለን» ፩ዮሐ.፫፥፳፩።

ልባችንስ ባይፈርድብን ሲል ኅሊናችን ከወቀሳ ነፃ ከሆነ ማለቱ ነው። ከኅሊና ወቀሳ ነፃ መሆን የሚቻለው ደግሞ ስህተትን ያልፈጸምን እንደሆነ ነው ስህተት እንኳን ብንፈጽም በንስሐ የተመለስን እንደሆነ ብቻ ነው። ከበደል የማይርቅ ሰው ከኅሊና ወቀሳ ነፃ እንደሚሆን ሊናገር እንዴት ይችላል። ይህ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ለመጽደቁ ምን ያህል እርግጠኛ ይሆናል? «ልባችንስ ባይፈርድብን በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት አለን» ግን ከኅሊና ወቀሳ ነፃ እንሆንም። ከህሊና ወቀሳ ነፃ የምንሆነው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ስንፈጽምና በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን ብቻ ስናደርግ ነው። ፩ዮሐ.፫፥፳፪።

እንግዲህ «ድፍረቱ አለን» የሚሉ ከሆነ ከትእዛዙ ውልፍት ያላሉ መሆኑን ያረጋግጡ በእግዚአብሔር ፊትም ሁል ጊዜ የቅድስና ሥራ

እየሰሩ መሆኑን ልብ ይበሉ። ምንም እናንተ በአፋችው ድነናል ቢሉ እንኳን ልባችው ግን አለመዳናቸውን ይመሰክርባቸዋል።

## ፪. በክርስቶስ መኖር

«አሁንም ልጆች ሆይ፣ በሚገለጥበት ጊዜ እምነት እንዲሆንልን (እርግጠኞች እንድንሆን) በመምጣቱም በእርሱ ፊት እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ።» ፩ዮሐ.፪፥፳፰–፳፱።

መጽደቃችንን ለመናገር ድፍረቱ አለን የሚሉ ከሆነ በእርሱ (በክርስቶስ) ሊኖሩ ይገባቸዋ። በእርሱ መኖር ማለት ደግሞ ወልድ ዋሕድ በምትል ሃይማኖት ተመሥርቶ የሚከተሉትን ማድረግ ነው።

- በኃጢአት ቀንበር አለመያዝ፣ «በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም አላወቀውምም» ፩ዮሐ.፫፥፮። በክርስቶስ የሚኖር የኃጢአት ሎሌ አይደለምና።

«በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ» ገላ.፭፥፩።

- ትእዛዙን መጠበቅ ነው «ትእዛዙንም የሚጠብቅ በእርሱ ይኖራል እርሱም ይኖርበታል በዚህም በእኛ እንዲኖር ከሰጠን ከመንፈሱ እናውቃለን» ፩ዮሐ.፫፥፳፬።

የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ደግሞ ዓለምንና በዓለም ያሉትን መጥላት ነው «በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፣ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል» ፩ዮሐ.፪፥፲፭–፲፯።

- ሥጋውን መብላት ደሙን መጠጣት «ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ» ዮሐ.፮፥፶፮።

ሥጋውና ደሙ የዘላለም ሕይወትን የሚሰጥ መሆኑን አምኖ የማይቀበል በእርሱ አይኖርም።

እንግዲህ ፍጹማን ነን «መንግሥቱን መውረሳችንን አረጋግጠናል» የሚሉ እነርሱ ከላይ በተገለጠው መሠረት በክርስቶስ እየኖሩ ነው?



ከኃጢአት ራሳቸወን ከልክለዋል? ትእዛዙን ምንም ሳይቀር ጠብቀዋል? በዓለም ያለው የዓይን አምሮት የሥጋ ምኞት ሁሉ ጠፍቶላቸዋችኋል? ሥጋውና ደሙ አማናዊ የዘላለም ሕይወት የሚሰጥ መሆኑን አምነው ተቀብለዋል?

ፍጹም ፍቅርስ አላቸው? «ሁሉንም አስተካክለው ይወዳሉ? ሌላውን እንደራሳችው አድርገው ይወዳሉ? «እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል። በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ፍቅር በዚህ ከእኛ ጋር ተፈጽሟል» ፩ዮሐ.፬፥፲፮–፲፯።

እውነተኛ ፍቅር በትእዛዙ መኖር ነው። ሰውን መውደድ እግዚአብሔርን ማምለክ ትዕዛዛት ሁሉ በእነዚህ በሁለቱ ይጠቀለላሉ «ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ»

ፍቅረ እግዚአብሔር:- እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ ከኑፋቄ ነፃ ሆኖ ማመን ነው።

ፍቅረ ቢጽ – የሰውን ፍጥረት መውደድ:- በሰው ላይ በደል አለመፈጸም ለሁሉም ያለ አድልዎ ማዘንና መርዳት ነው። በእግዚአብሔር ፍቅር መኖር ማለት ይህ ነው «እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ» ይለናል። ዮሐ.፲፭፥፲።

ከትእዛዙ አንዱን እንኳን ከሳትን በፍቅሩ አንኖርም። ድፍረቱም የሚኖረን በፍጹም ፍቅር ውስጥ ስንኖር ነው «ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም» እንደተባለ። ፩ዮሐ.፬፥፲፰።

ድፍረቱ አለን የሚሉ ወገኖች ይህን ሁሉ በሕይወታቸው ፈጽመው ነው ወይስ ትእቢትን ገንዘብ አድርገው «አንድ ጥቅስ መዘው ባልሆነ መንገድ አጣመው በመተርጎም «ደነናል ይህን መስክሩ» ላሉ የሐሰት መምህራን የገደል ማሚቱ ሆነው እያገለገሉ ነው።

የክርስትና ሕይወት የማስተዋል ሕይወት ነውና። ወደ ኅሊናችው ይመለሱ ጌታ በምሳሌ ያስተማረውን የቀራጩን ሕይወት ያስታውሱ «አምላክ ሆይ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ» እያሉ ፈጣሪያቸውን ዘወትር ይለምኑ ከስህተት መንገድም ይውጡ። ሉቃ.፲፰፥፲፫ ከሐሰት መምህራንም ይለዩ።

# ለዚህ መጽሐፍ ረዳት የሆኑ ሌሎች መጻሕፍት (References)


1. መጽሐፍ ቅዱስ (በአማርኛ፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች)
2. ሐዲስ ኪዳን (በግእዝና በአማርኛ) በሊቃውንት ጉባኤ ታርሞ የተዘጋጀ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1975 ዓ.ም
3. ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ በ1966 ዓ.ም
4. መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት) የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ
5. መሐሪ ትርፌ (ሊቀ ሊቃውንት) መጻሕፍተ ሐዲሳት ሦስቱ ንባቡ ከነትርጓሜው በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1951
6. መዝሙረ ዳዊት ንባቡ ከነትርጓሜው አዲስ አበባ 1973 ዓ.ም
7. መጻሕፍተ ሰሎሞን ወሲራክ በንግድ ማተሚያ ድርጅት አዲስ አበባ 1988 ዓ.ም
8. አባ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1978 ዓ.ም
9. አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)፣ ኮኮሐ ሃይማኖት፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1949 ዓ.ም
10. ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ (ሊቀ መዘምራን)፣ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት፣ ኮከበ ጽባሕ ዘማኅበረ ሐዋርያት ፍ.ሃ. ማተሚያ ቤት አሥመራ 1969 ዓ.ም
11. አባ መልከ ጼዴቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጽሐፍ፣ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1984 ዓ.ም
12. ክንፈ ገብርኤል አልታዬ (ሊቀ ካህናት)፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን፣ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1984 ዓ.ም
13. አባ ቄርሎስ (ሊቀ ጳጳስ)፣ ፍሬ ሃይማኖት
14. ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት
15. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ፣ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1948 ዓ.ም እ.አ 1962 ዓ.ም)
16. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የተዘጋጀ አዲስ አበባ 1972 ዓ.ም
17. መዝገበ ሃይማኖት፣ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የድርስ ክፍል የተዘጋጀ አዲስ አበባ 1959
18. ዓሥራት ገብረ ማርያም፣ ትምህርተ መለኮት፣ በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1983 ዓ.ም
19. ብርሃኑ ጎበና፣ ዓምደ ሃይማኖት፣ በንግድ ማተሚ[የ ድርጅት አዲስ አበባ 1985 ዓ.ም
20. ብርሃኑ ጎበና፣ ፍኖተ ጽድቅ፣ በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1986 ዓ.ም
21. ሐመር መጽሔት፣ በማኅበረ ቅዱሳን የመዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት
22. መለከት መጽሔት፣ በዋናስ የሕትመትና የማስታወቂያ ድርጅት እየተዘጋጀ የሚወጣ ወርሐዊ መጽሔት
23. H.H, POPE SHENOUDA III, Comparative Theology
24. H.H POPE SHENOUDA III, Salvation in the Orthodox Concept
25. Rev. Marcos Daud, Church Sacraments 1952